አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃል ማለቱን አስታውሱ (ማቴዎስ 6:8ይመ)። የምትፈልጉትን ለእግዚአብሔር መንገር አያስፈልጋችሁም። ዋናው ጉዳይ የሚያስፈልጋችሁን ነገር ስትነግሩት እንደምታገኙ እርግጠኛ እስክትሆኑ ድረስ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላችሁ መሆኑ ነው።

ለአሥር ዓመት ያህል ስጸልይባቸው የነበሩ ነገሮች አሉ። አሁንም ቢሆን ገና አልሆኑም። እንደዚያ በሚሆንበት ጊዜ እየጸለያችሁ ያለው በእምነት መሆን አለመሆኑን ትረዳላችሁ። ባለ ማመን እየጸለያችሁ ከሆነ፣ ‹‹ዐሥር ዓመት ሙሉ ጸለይኩ፣ ግን ምንም የሆነ ነገር የለም›› ትላላችሁ። በእምነት እየጸለያችሁ ከሆነ፣ ‹‹መጸለይ ከጀመርኩበት ጊዜ ይልቅ አሁን አሥር ዓመት ያህል ወደ መልሱ ቀርቤአለሁ›› ትላላችሁ።

ይህ የተለያዩ መሣሪያዎች የመጫወት ፍላጎትን በእናንተ ውስጥ እንዳሳደረ ተስፋ አደርጋለሁ። መለኮታዊ የጸሎት ሲምፎኒ /ስምረት/ አካል መሆን በጣም ደስ የሚል ነው። በመሪው በመንፈስ ቅዱስ ሥር ሆናችሁ በቃሉ በተገለጸው መሠረት ከሌሎች ጋር ተስማምታችሁ ስትጸልዩ ጸሎታችሁ መልስ እንደሚያገኝ ኢየሱስ ተናግሮአል። አሁን ደግሞ ለጸሎታችን የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንዴት እንደምናውቅ የበለጠ እንማር።

For more spiritual book join our official telegram channel
https://t.me/amharicspritualbooks



# 5

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ

**የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነውና፤ በሁለት በኩል ስለት ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ ስለታም ነው።**

**ዕብራውያን 4:12**

በምድር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድራጊ ሰዎች እነማን ናቸው ብላችሁ ትገምታላችሁ?›› በማለት ሰዎችን ብትጠይቁ የተለያዩ መልሶች እንደሚሰጡ አስባለሁ። ምናልባትም የፖለቲካ መሪዎችን ያስባሉ። ወይም ደግሞ ሳይንቲስቶችን ወይም የመከላከያ አዛዦችን ያስባሉ።

እነዚህ ሰዎች በእውነት ተጽእኖ አድራጊ ናቸው ብዬ አላምንም። እኔ እንደምረዳው በዚህ ዘመን በምድር ላይ በጣም ተጽእኖ አድራጊዎች የጸሎታቸውን መልስ የሚያገኙበትን መንገድ የሚያውቁ ናቸው። ለዚህ ምክንያቱ እጅግ ጥበበኞች ወይም በጣም ብርቱ ሰዎች ማድረግ ከሚችሉት በላይ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ወደ ሁኔታዎቹ እንዲለቀቅ ማድረግ ስለሚችሉ ነው። በዓለማችን ማንኛውም አስደናቂ መልካም ለውጥ ለምሳሌ፣ የጨቋኝ አገሮች ያኖሩት ገደብ መፍረስ ወይም በሶቪየት ዩኒየን ውስጥ የፖለቲካ ነጻነት መስፈን የእግዚአብሔር ሕዝብ - የካህናት መንግሥት ጸሎት ውጤቶች እንጂ፣ የፖለቲከኞች ውሳኔ ውጤቶች እንዳልሆኑ አምናለሁ።

እንግዲህ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ያን ያህል ሥልጣን ከተሠጠን ያንን የማናደንቅና የማንጠቀምበት ከሆነ በእውነትም ቸልተኞች ነን ማለት ነው። እንደ ካህናት መንግስት ምድርን መግዛት የእኛ ኃላፊነት ነው። የታሪክን አካሄድ መለወጥ እንችላለን፤ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅን ማዕከል ያደረገ ነው።

‹‹እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ››

የተራራውን ስብከት ብንመለከት ማቴዎስ 6 ላይ ያለውን በምድር ባሉ ክርስቲያኖች የጌታ ጸሎት በመባል የሚታወቀውን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል እናገኛን። ኢየሱስ፣ ‹‹እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ›› ሲል ምንም እንኳ ውብ ቃሎች ቢሆኑ እንኳ ሁልጊዜ ቃል በቃል ቀጥሎ ያሉ ቃሎችን መከተል እንዳለብን መናገሩ ነበር በማለት አላምንም ይልቁንም እንዴት መጸለይ እንደሚገባን እጥር ያለ ሆኖም የተሟላ ምሳሌ መስጠቱ እንደ ነበር ነው የማምነው።

እስቲ ከቁጥር9-10 ያሉትን፣ ‹‹በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን›› የሚሉትን ውጤታማ የመጸለይ መንገዶች፣ እንመልከት። እነዚህ ቃሎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማግኘት ቁልፍ ይዘዋል። ይህን ቁልፍ በእጃችሁ ማኖር እንደምንችልና ሁሉን ቻይ የእግዚአብሔር ኃይልን ለመክፈት እንደሚረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

## በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ

ከሁሉም አስቀድሞ፣ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ በማለት እንደ አባት እግዚአብሔርን እንጠራለን። የምንጸልየው በሩቅ ላለ የማይታወቅ አምላክ ወይም አንድ ዓይነት ሰብዕና የለሽ ኃይል አይደለም። የምንጸልየው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ራሱን አባታችን ላደረገ ሰብዕና ላለው አምላክ ነው።

ሜካኒካዊ የአጽናፈ ዓለም ዕይታ - ማለትም አጽናፈ ዓለም ተከታታይ የቁሳዊ ነገሮች ፍንዳታ ውጤት ነው የሚለው ሐሳብ አንድን ሰው ብቸኛ መረዳትና መቆጣጠር በማይችለው ግዙፍ አጽናፈ ዓለም ወደ የጠፋ አድርጎ እንዲያስብ ያደርገዋል።

ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሳስብ፣ ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ላይ ንግግር በማድረግ የሚታወቅ በጣም የታወቀ አንድ ካቶሊካዊ ጓደኛዬን አስባለሁ። ይህ ጓደኛዬ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ባለ አንድ ትልቅ ከተማ



ቆሻሻ ሰፈር ይኖር እንደ ነበር አጫውቶኛል። ወደ ምሽት አካባቢ ነበር፤ መጨላለም ጀምሮ ነበር። ቀዝቃዛው ነፋስ ዙሪያውን ቀጥ ብሎ የሚቆይ አቧራ እያስነሣ ነበር። አውራ መንገዱ ኩርባ ላይ ቆሞ እያለ ከባድ ብቸኝነትና ደካማነት ተሰማው። ከዚያም ድንገት አንድ ቃል ለእግዚአብሔር እንዲናገር ወደ እርሱ መጣ፤ ‹‹አባቴ፣ አባቴ፣ አባቴ›› በማለት ደጋግሞ መናገር ጀመረ። አባቴ የሚለውን ቃል በደጋገመ ቁጥር የበለጠ ብርታትና መረጋጋት እየተሰማው ይሄድ ጀመረ። እንደ አባቱ ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር ግንኙነቱን በማጥበቁ በዚያ ወቅት ለነበረበት ሁኔታ ያለውን አመለካከት ለወጠው።

ወጣት በነበርኩ ጊዜ ስለ አጽናፈ ዓለሙ መገኘት የተለያዩ ንድፈ ሐሳቦችን ለብዙ ዓመቶች አጥንቻለሁ። ሆኖም፣ በአእምሮ የሚያረካኝ አንድ እንኳ አላገኘሁም። ሌላው ቢቀር ከሰማሁዋቸው ሌሎች ከንቱ ሐሳቦች የባሰ አይሆንም በሚል ብቻ የማደርው ባጣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጀመርኩ። እስትንፋስ መለኮት ያለበት ወይም የተለየ መሆኑን አላምንም ነበር፤ እንደማንኛውም ተራ መጽሐፍ ነበር የማየው፤ በዚሁ ሁኔታ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ላነበው ወሰንኩ።

ያን ውሳኔ ያደረግሁት በ1940 መከላከያ ሠራዊቱን በተቀላቀልኩበት ጊዜ ነበር። በካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ የፍልፍስፍና ፕሮፌሰርነት ደረጃዬ ነበር። በሁለኛው የዓለም ጦርነት የብሪታንያ መከላከያ ሠራዊት እንድቀላቀል የተጠራሁት፤ ከሠራዊቱ ጋር በማሳልፈው ጊዜ ሁሉ ለማንበብ አቅጄ መጽሐፍ ቅዱሴን ይዤ ነበር የሄድኩት። በሠራዊቱ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ፣ በራሴ ምርጫ ሳይሆን በጣም ብዙ ጊዜ ነበረኝ፤ በዚያ ሁኔታ የሚቀጥሉትን አምስት ተኩል ዓመቶች አሳለፍኩ። ከሌሎች 24 አዲስ ምልምሎች ጋር በሠራዊቱ ክፍል ባሳለፍኩት የመጀመሪያ ሌሊት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበቤ ያሳደረውን መገረም ሁሌም ትዝ ይለኛል። ቁጭ ብዬ መጽሐፍ ቅዱስ ገልጬ አነበብኩት እንጂ ስለ መጽሐፉ የተለየ ሐሳብ አልነበረኝም። ሌሎች ወታደሮች ይመለከቱኝ ጀመር፣ እያነበብኩ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ሲረዱ ደስተኛ ያልሆነ ድባብ ክፍሉ ሁሉ ላይ አሳደረ። አንድ መጽሐፍ ያንን ያህል ተፅዕኖ ያሳድራል ብዬ በፍጹም አላሰብኩም ነበር እንደማስበው በጣም ያስገረማቸው

ነገር በጥቂቱ ም ቢሆን እንኳ ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያነብ ሰው አለመኖሬ ነበር።

ይሁን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሳነብ ከጸሐፊውም ጋር ተገናኘሁ። እንዴ ከጸሐፊው ጋር ከተገናኘሁ ወዲህ መጽሐፉ እጅግ አስደናቂ ስሜት እያሳደረብኝ ሄደ። ከፍልስፍና ያላገኘኋቸውን መልሶች እዚያ ውስጥ አገኘሁ። እኔኑ ለራሴ የሚገልጽ ስለ ነገሮች አጀማመር ገለጻ አገኘሁ። ስለ ሰው አፈጣጠር ታሪክ ከዘፍጥረት 1-3 ሳነብ ውስጤ እየተከናወነ ያለ ነገርን ተረዳሁ።

የምወደውና በስፋት ያጠናሁት ፈላስፋ ፕሌቶ ነበር። እርሱ የጻፈውን እያንዳንዱ ቃል በግርክ ቋንቋ ነበር ያነበብኩት። ፕሌቶ የሰው ልጅን ነፍስ አንዱ ጥቁር ሌላው ነጭ በሆኑ ሁለት ፈረሶች በሚጎተት ሠረገላ ይመስለዋል። ነጩ ፈረስ ሁሌም ወደ ላይ መሄድ ይሞክራል፤ ጥቁሩ ፈረስ ሁሌም ሰረገላውን ቁልቁል ይጎትታል። የእኔን ልምምድ በተመለከተ ይህ ምሳሌ እውነት መሆኑ ተሰማኝ።

የዘፍጥረትን ታሪክ ሳነብ ሰው ከሁለት ነገሮች መፈጠሩን ተገነዘብኩ። ከታች ከምድር ዐፈር ነው፤ ሁሉን ከሚችል አምላክ እስትንፋስም ከላይ ነው። በእያንዳንዳችን ውስጥ ከላይ በሚመጣውና ከምድር በሚመጣው መካከል ውጥረት መኖሩን አየሁ። ይሁን እንጂ ያንን ውጥረት እንዴት ማርገብና ሕይወታችንን ወደ ስምምነት ማምጣት እንደሚቻል እግዚአብሔር ቃሉ ውስጥ አሳይቶናል። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ስለ አጽናፈ ዓለሙ ፍጹም የተለየ ዕይታ ያዝኩ። ከመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር ስገናኝ አባት መኖሩንና ከማንኛውም ነገር በስተጀርባ ያለ እውነተኛ ኃይል የእርሱ ፍቅር መሆኑን ወደ መረዳት መጣሁ። አጽናፈ ዓለም ውስጥ አንድ ሊገለጽ የማይቻል ሀቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው።፤ እግዚአብሔር እንደሚወደን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፤ ለምን እንደ ሆነ ግን አይነግረንም። እንዲሁ ብቻ ከአእምሮአችን በላይ ነው። መልካሙ ዜና ግን የሚወደን መሆኑ ነው። ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ስንጀምር መጀመሪያ የምንጠቀምበት ቃል አባታችን የሚል እንደሆነ ኢየሱስ ይናገራል።



በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንደ አባት እግዚአብሔርን የምናውቅ ከሆነ ስንጸልይ አንድ የምናደርገው ነገር እንደ አባት ወደ እርሱ መቅረብ ነው። በብዙ ቁጥር አባታችን ማለቱ በጣም ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም ብዙዎቻችን ሲበዛ ራሳችን ላይ የምናተኩር በመሆኑ ነው። ስንጸልይ፣ ‹‹እግዚአብር ሆይ ባርከኝ፤ እርዳኝ፤ ፈውሰኝ›› ወደ ማለት እናጋድላለን። ኢየሱስ ግን፣ ‹‹እናንተ ብቻኛ የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም። ሌሎች ብዙ ልጆችም አሉት፤ ሁሉም ለእርሱ አስፈላጊ ናቸው። ለወንድሞቻችሁና እኅቶቻችሁም አስቡ›› በማለት ያሳስበናል።

## ስምህ ይቀደስ

ስምህ ይቀደስ የሚለው ቀጣዩ ሐረግ የአክብሮትና የአምልኮ ዝንባሌን ይገልጻል። እግዚአብሔርን እንደ አባት ከተቀበልን በኋላ የአክብሮት ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል። በዚህ ዘመን በአብዛኞቹ ቤተክርስቲያኖች ሁሉን የሚችል አምላክን በአክብሮት የመቅረቡ ጉዳይ በሚያሳዝን ሁኔታ እየጠፋ መሆኑን መናገር እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር በፍርሃት እንድንርበተበት አይፈልግም፤ አክባሪዎች እንድንሆን ግን ይፈልጋል። ያ አክብሮት በጸሎታችን ራሱን እንዲገልጽ ስንፈቅድ መንፈሳችን ውስጥ አንዳች ነገር ይሆናል።

## መንግስትህ ትምጣ

ቀጥሎ፣ ‹‹መንግስትህ ትምጣ›› እና፣ ‹‹ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን›› ወደ ተሰኙት መጀመሪያዎቹ ሁለት ልመናዎች እንመጣለን። ጸሎት የምንጀምረው ለሚያስፈልገን ነገር በመለመን አለመሆኑን ልብ አድርጉ። ያ፣ ‹‹የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤ በደላችንን ይቅር በለን›› በማለት ይከተላል። ሆኖም፣ የምንጀምረው እዚያ አይደለም። የምንጀምረው በእግዚአብሔር ዓላማ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ በሆነ ጉዳይ ነው።

ከውድቀት በኋላ የሰው ልጅ እኔነት በሚባል ትንሽ እስር ቤት ውስጥ ሆኗል። ተፈጥሮአዊ ሰው ራስ ተኮር ነው፤ ሕይወቱ ራሱ ላይ ብቻ ያተኩራል። የምፈልገውን የማገኘው እንዴት ነው? የሚረዳኝ ማን ነው? ከዚህ የሚገኘው ጥቅም ምንድን ነው? ይላል። ይህ እስር ቤት ነው።

በአዲሱ ልደት አማካይነትና በእግዚአብሔር ጸጋ እኔነት ላይ ከማተኮር እስር ቤት ተፈትተን እኛ ከምንፈልገው ይልቅ እግዚአብሔር የሚፈልገው ወደሚበልጥበት ከእርሱ ጋር ወደ መገናኘት እንገባለን። በዚያ መንገድ መጸለይ ስትማሩ ክንፍ እያበቀላችሁ ነው ማለት ይቻላል። ከተፈጥሮአዊ ደረጃ በላይ ከፍ ብላችሁ መብረር ትችላላችሁ።

ስለሆነም መጀመሪያ የተመራነው፣ ‹‹መንግስትህ ትምጣ እንድንል ነው።›› ይህ በጣም ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በምድር ላይ ማድረግ ከሚፈልገው ነገር ጋር ራሳችንን እያሰለፍን ነው። በዚህ ዘመን የመጨረሻው የእግዚአብሔር ዓላማ በጣም ቀላል ነው። ዝርዝሩ በጣም የተንዛዛ ሊሆን ይችላል፤ መሠረታዊው የእግዚአብሔር እቅድ ግን ይህ ነው - መንግስቱን በምድር መመሥረት። ይህ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቀዳሚ ሐሳብ ነው። ኢየሱስ ሞቶ ከተነሳ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዘመናት ሁሉ እግዚአብሔር ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር አልተለወጠም። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በየዕለቱ የጌታን ጸሎት ይጸልያሉ፤ ስለ ምን እየጸለዩ እንደ ሆነ ግን በፍጹም አልተገነዘቡም። ‹‹መንግስትህ ትምጣ›› ስንል አደርጋለሁ ያለውን ነገር እንዲያደርግ እየጠየቅን ነው ማለት ነው።

የኋላ ኋላ የሰው ልጆች ችግር መፍትሔ የሚሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት መመስረት ነው። በዚህ ዘመን ስለ ማኅበረሰባዊ ወንጌል ማለትም ለሰው ልጅ አካላዊና ቁሳዊ ችግሮች ማሰብ እንዳለብን ብዙ ሲባል እንሰማለን። ክርስቲያኖች ሁሉ ለሌሎች ሰዎች አካላዊና ቁሳዊ ችግሮች ማሰብ አለብን። ያን ማድረግ የፍቅር መገለጥ እንደሆነ አምናለሁ። ሰዎችን የምትወዱ ከሆነ ስላለባቸው ችግርም ታስባላችሁ። ሆኖም ጠቅላላ የሰው ልጅን ችግር መፍታት በእኛ አቅም የሚቻል ነው ብዬ ግን አላምንም።

ቤተክርስቲያን ለሁለት ሺህ ዓመት በዚህ ምድር አለች፤ ከየትኛውም ሰው ልጅ ታሪክ ዘመን ይልቅ በብዙ መልኩ አሁን ችግሮቹ በዝተዋል።



ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሃያ አምስት ሺህ ልጆች በአብዛኛው ከአመጋገብ ጉድለትና ንጽሕና ጉድለት የተነሣ ይሞታሉ። ያም ሆኖ መንግሥታት ለጦር መሣሪያ የሚያውሉት ገንዘብ ሁሉ በምድር ባሉ አገሮች ሁሉ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮችና ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ለማግኘት ይበቃ ነበር። ችግሩ በቂ ምንጭ አለመኖሩ አይደለም፤ ችግሩ የሰው ልጅ ስግብግብነት እንዲሁም ፍርሃትና ጥላቻ ምንጮቹ ለተሳሳተ ዓላማ እንዲውሉ ማድረጉ ነው።

እዚህ ላይ በተሳሳተ መንገድ እንድትረዱኝ አልፈልግም፤ አጉል ሰላም ወዳድነትን እየሰበክሁ አይደለም። የችግሩ ሥረ መሠረት የሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ መሆኑን እያመለከትኩ ነው። የሰው ልጅ ብቻውን ወይም ቤተክርስቲያን ብቻዋን የሰው ልጅን ቁሳዊና ተግባራዊ ችግሮች መፍታት አይችሉም። ያንን ማድረግ የሚችል አንድ ነገር ብቻ ነው - የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር መመሥረት።

ተግባራዊ ሰው እንደሆንኩ አስባለሁ። ባለ ራእይ ወይም ሕልመኛ ብቻ መሆን አልፈልግም። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን በምድር ካለ ማንኛውም ሰው የበለጠ ተግባራዊ መሆኑን ለሰዎች እናገራለሁ። አንድ ነገር ተግባራዊ ካልሆነ መንፈሳዊ አይደለም። የእግዚአብሔር መንግሥት መመሥረት ብቸኛ የሰው ልጅ ተግባራዊ ችግር መፍትሔ ነው። ማኅበረ ሰባዊ ወንጌል እየሰበኩ ያሉ ሰዎች ሕልም እየተናገሩ ነው። ዓላማቸው መልካም ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ ቁሳዊ ችግሮች ላይ ብቻ በማተኮር እንደሚፈቱ መናገር ግን እውነት አይደለም። ለሰው ልጅ አንድ ተስፋ ብቻ አለው።

በስፋት ተጉዤአለሁ፤ ሰዎች እጅግ ድሀ ወደ ሆኑባቸውና በከፍተኛ ችግርና ድንቁርና ውስጥ ባሉባቸው ብዙ አገሮች ነበርኩ። በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ፣ ብዙ አገሮች ጨኸት ክርስቲያኖች ያላቸው ምስል በጣም ደብዛዛ ሊሆን ይችላል። አሁንም ችግሮቹ እንዳሉ ናቸው። በብዙ መልኩ ድህነት፣ ጉስቁልናና ረሃብ ጨምሯል።

መፍትሔ አለ - የእግዚአብሔር መፍትሔ። እግዚአብሔር ታላቅ ባለ እውነታ ነው፤ ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር የክርስቶስን መንግሥት በዚህ ምድር በመመሥረት የሰው ልጆችን ችግር ማስወገድ ቁጥር አንድ ተቀዳሚ እንዲያደርግ ያደርገዋል።

## መንግሥቱ እንዴት እንደሚመሠረት

መንግሥቱ የሚመሠረተው እንዴት እንደ ሆነ እዚህ ላይ ጥቂት ገለጻ ሊኖረን ይገባል። ጳውሎስ የዚህን መንግሥት መሠረታዊ ባሕርይ ገልጾአል። «የ እግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ጽድቅ፣ ሰላምና ሐሤት ነው እንጂ፣ የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደለም» (ሮሜ 14:17)። ጽድቅ ቀድሞ ይመጣል። ያለ እውነተኛ ጽድቅ እውነተኛ ሰላም አይኖርም። ዛሬ ዓለም ስለ ሰላም ብዙ ያናገራል። ብዙ ቤተክርስቲያኖችም ስለ ሰላም ይጸልያሉ። ያ መልካም ጸሎት ነው፤ ነገር ግን ያለ ጽድቅ ሰላም እንደማይመጣ በአእምሮአችን እንያዝ። ለክፉዎች ሰላም እንደማይኖራቸው እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል ሁለቴ ተናግሮአል (ኢሳይያስ 48:22፤ 57:21 ይመ)።

ሰላምና ደስታ የሚፈልጉ ብዙ ክርስቲያኖች አግኝቻለሁ፤ ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ሰላምና ደስታ የጽድቅ ውጤቶች የመሆናቸውን ሐቅ ችላ ማለታቸውን ተረድቻለሁ። ጽድቅ የመንግሥቱ የመጀመሪያ መገለጽ ነው። ያለጽድቅ ሰላም ለማግኘት የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ ወደ ተስፋ መቁረጥ ያደርሳል።

ባለኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት መረዳት መሠረት ወደ ፊት የክርስቶስ ተቃዋሚ በሰይጣናዊ እስትንፋስ የተነሣሣ መሪ ይመጣል። ሰላም እንደሚኖር ተስፋ ይሰጣል፤ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ተስፋው የተፈጸመ ይመስላል። ጳውሎስ ግን «ሰዎች ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ፣ ምጥ እርጉዝ ሴትን እንደሚይዛት እንዲሁ ጥፋት በድንገት (ያለ ማስጠንቀቂያ) ይመጣባቸዋል፤ ከቶም አያመልጡም» በማለት ትንቢት ተናግሮአል (1 ተሰሎንቄ 5:3)። በእውነተኛ ባሕርያቸው ጽድቅን፣ ሰላምንና ደስታን የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው።



መንግሥቱ የሚመጣበት የመጀመሪያ መንገድ ውስጣዊ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት በውጫዊ መጠባበቅ እንደማትመጣ ኢየሱስ በዘመኑ ለነበሩ ፈሪሳውያን ተናግሮአል። የ እግዚአብሔር መንግስት በእናንተ ውስጥ ወይም በመካከላችሁ ናት አለ(ሉቃስ 17:21ይመ)።

ያለ ንጉሥ መንግሥት የለም። ንጉሡ ሲመጣ መንግሥቱን ይዞ ይመጣል። ስለዚህ ኢየሱስን የሕይወቱ ንጉሥ ያደረገ ማንኛውም እውነተኛ አማኝ በግለ ሰብ ደረጃ የመንግሥቱ ልምምድ ይኖረዋል። ያ ማለት፣ «እኔነትን» ከልቡና ዙፋን አውርዶ ኢየሱስን በዚያ ዙፋን ማድረግ ማለት ነው። ያንን ያደረገ ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ከጽድቅ፣ ከሰላምና ከደስታ ጋር እንደሚመጣ ይረዳል።

ሆኖም፣ የኅብረት የመንግሥቱ መገለጫ መኖሩንም አምናለሁ። ይህም ቤተክርስቲያን በሚባለው እውነተኛ የአማኞች ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። ይህ በልባቸውና በሕይወታቸውን ኢየሱስን ንጉሥ ያደረጉና፣ በዚያ መሠረት ላይ እርስ በርስ የሚቀራረቡ ሰዎች ኅብረት ነው። ባለን ግንኙነት፣ በምንኖርበት መንገድ በጨረፍታም ቢሆን መንግሥቱን በማንጸባረቅ ዓለምን መገዳደር በየትኛውም ቦታ የመንግሥቱ አርዓያ መሆኗ የቤተክርስያን ኃላፊነት ነው። ሰዎች ቤተክርስቲያንን አይተው፣ «ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ይህን ይመስላል» ማለት መቻል አለባቸው። ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ጽድቅን፣ ሰላምንና ደስታን በውስጧ ማየት አለባቸው። ቤተክርስቲያን እነዚህ ነገሮች በምታሳይበት ቦታ ሁሉ የወንዶችና ሴቶች ልብ ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ ለወንጌል እውነት የተከፈተ እንደሚሆን እነግራችኋለሁ። ዓለም ቤተክርስቲያን ውስጥ መንግሥቱን ማየት ነው። ካላየ ምናልባት መልእክታችንን ላይቀበል ይችላል።

የመንግሥቱን አርዓያ ማሳየት ስለምንችልበት መንገድ አንድ በጣም ጠቃሚ ሐሳብ ልንገራችሁ፤ ያ ግን ያለ ምንም ግጭት የሚሆን አይደለም። ሐቁ በዚህ ዘመን እውነት ግራ እጋቢ መሆንዋ ነው። ኢሳይያስ እውነት መንገድ ላይ ስለሚወድቅበት፣ ጽድቅም ስለማይገባበት ጊዜ ጽፏል። በአብዛኛው የሰው ልጅ ማኅበረሰብ ውስጥ ከእንደዚያ ዓይነቱ ጊዜ ሩቅ አይደለንም።

ሆኖም፣ እዚህ ላይ የመልእክታችን አርዓያ መሆን የሚችል አንድ መንገድ አለ።

ባልና ሚስትን በተመለከተ ጳውሎስ ለክርስቲያኖች ይህን ብሏል፤ ‹‹ባሎች ሆይ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደ ወደዳት ...እናንተም ሚስቶቻሁን ውደዱ›› (ኤፌሶን 5:25)። ባሎችን፣ ‹‹ይህ አስተያየት አይደለም፤ ይህ ትእዛዝ ነው። ሚስቶቻችሁን እንድትወዱ ታዛችኋል። በተጨማሪም ያንን ስታደርጉ ብዙ መልካም ነገር ይሆንላችኋል›› እላቸዋለሁ። የዚያ ሌላው ወገን ደግሞ፣ ‹‹ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ ሁሉ፣ ሚስቶችም በነገር ሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ›› የሚል ነው(ኤፌሶን 5:24)።

ዓለም ክርስቲያን ሚስትን ሲያይ፣ ‹‹ያ ሰዉዬ ሚስቱን የሚወድበት መንገድ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የወደደበት መንገድ መሆኑን ተረድቻለሁ። ያቺ ሴት ለባልዋ የምትገዛበት መንገድ ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ የምትገዛበት መንገድ ነው›› ማለት አለበት። አንዳቸው ለሌላው የተሰጡ ክርስቲያን ጥንዶች ለዓለም መልእክት መሆን ይችላሉ። የእግዚአብሔር መንግሥት ይህን ይመስላል።

ከምንም ነገር ይልቅ የእግዚአብሔር መንግሥት መጀመሪያና ከሁሉም በልጦ መታየት ያለበት ቦታ ቢኖር የአማኝ ቤተ ሰብ ነው። በዚህ ዘመን ሰይጣን እያጠቃ ያለው አንድ ነገር ቢኖር ቤተሰብን ነው። ቤተሰብ መንግሥቱን እንዲወክል እግዚአብሔር ወስኗል፤ ሰይጣን የመንግሥቱን መልእክት ማደብዘዝ፣ መሸፈንና ማስወገድ ይፈልጋል። የመንግሥቱ መመሥረት የእርሱ ኃይል ፍጻሜ በመሆኑ፣ መንግሥቱን ይፈራል።

## በመጨረሻ ንጉሡ ይመጣል

በግል በአማኞች ልብ ውስጥም ሆነ በእውነተኛ ቤተክርስቲያን ኅብረት መንግሥተ በማይታይ መልኩ ሊመጣ ይችላል። ያ ግን የመጨረሻው አይደለም። መጨረሻው በሚታይ መልኩ የእግዚአብሔር መንግሥት መመስረት ነው። የማይታይ መንግሥት ንጉሥ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፣ ለሚታየውም ያስፈልገዋል። እውነተኛ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር የሚመሠረተው ንጉሡ በግልጽ በአካል ሲመለስ ብቻ ነው። በበኩሌ ሥራውን ያለ ኢየሱስ ብቻችንን መሥራትና መጨረስ እንችላለን በማለት ለቤተክርስቲያን



መናገር አጉል ድፍረት እንደሚሆን አስባለሁ። መጽሐፍ መገለጡን አጥብቀን መናፈቅ እንዳለብን ይናገራል።

አንድ የወንጌል ሰባኪ ጓደኛዬ ራሱን የሚገልጥበት አስቂኝ መንገድ አለው። ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን፣ ‹‹እንኳን ደኅና መጣህ!›› ከማለት የበለጠ ነገር ማድረግ አለባት ይላል። ወዳጆቼ፣ በዚህ ጊዜና በዚያ ጊዜ መካከል እርሱ ተመልሶ ስናየው በጣም የሚያጓጉ ነገሮች በምድር መሆን ጀምረዋል። እግዚአብሔር ያንንም ያስተካክላል።

የእግዚአብሔር ዋናው ዓላማ ይህ ነው - የሚገዛው የሚታይ ንጉሥ ያለው የሚታይ መንግሥት በምድር ላይ መመሥረት። እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሁሉ እዚያ ላይ ያነጣጠረ ነው። ያንን የእኛም ተቀዳሚ ጉዳይ እስክናደርግ ድረስ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ጋር በእውነት አልተጣጣምንም ማለት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት እንድትመጣ እንድትጸልዩ ኢየሱስ የነገረን ለዚያ ነው። ከዓላማው ጋር ራሳችንን ማስተካከል ይጠበቅብናል።

ጸሎት እግዚአብሔር የምንፈልገውን እንዲፈጽምልን የምናደርግበት መንገድ አይደለም። ብዙ ክርስቲያኖች እንደዚያ እንደ ሆነ ያስባሉ። በዚያ መንገድ ይሠራ ይሆናል፤ ዓላማው ግን ያ አይደለም። ጸሎት እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገውን እንዲያደርግ መሣሪያዎች የምንሆንበት መንገድ ነው። ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር መስመር ስንይዝ ማንም የማይቋቋመው ጸሎት እንጸልያለን። ሰብዓዊም ይሁን ሰይጣናዊ የጸሎታችንን ተግባር መቋቋም የሚችል ኃይል አይኖርም።

## ፈቃድህ ይፈጸም

ኢየሱስ በጸሎቱ፣ ‹‹ፈቃድኅ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን›› አለ። እንዲህ ማለት በምድር ሁሉም ነገር ፍጹም ነው ማለት ሳይሆን በማንኛውም ሁኔታ የእግዚአብሔር ዓላማና መፍትሔ ፍጹም በሆነ መልኩ ይሠራል ማለት ነው። ያንን ታምናላችሁ? አያችሁ፣ ያ እውነት መሆኑን ራሳችሁን ካሳመናችሁት በተለየ ሁኔታ ትጸልያላችሁ።

ግን ይህን አስታውሱ፣ ለእግዚአብሔር ‹‹ፈቃድህ ይፈጸም›› ካላችሁ፣ ‹‹የእኔ ፈቃድ አይሁን›› ማለታችሁ ነው። ይህን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ የበለጠ ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድንፈራ ብዙዎቻችንን ሰይጣን አሳምኖናል። ‹‹የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከተቀበልኩ መከራ ማለት ሊሆን ይችላል። ጥቅሜን መተው ማለት ሊሆን ይላል። ያሉኝን ነገሮች ሁሉ አተዋለሁ›› እንላለን። ምናልባት እንደዚያ ሊሆን ይችላል፤ ግን ራእይ 4፡11 የሚለውን ተመልከቱ፣ ‹‹አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤ በፈቃድህም ተፈጥረዋልና፤ ሆነዋልምና›› በዚያ ጥቅስ ብዙ ጊዜ አስቤበታለሁ፤ ከእግዚአብሔር ፈቃድ የተሸለ ነገር ሊኖር እንደማይችልም ወደ መገንዘብ መጥቻለሁ። በማንኛውም ጊዜ ለሚሆን ማንኛውም ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ የተሻለ ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቀበል መፍራት የለብንም። ያንን የምናደርገው ውስጡ ምን እንዳለ ሳናውቅ ነው።

አንድ ጊዜ እኔና ሩት ንግግር ለማድረግ ዝግጅት ላይ እያለን በሐሳብ ደረጃ ሐዋይ ነበርን። ከሰይጣናዊ ኃይሎች ጋር ውጊያ ላይ ነበርን። ሁለታችንም መሬት ላይ የተዘረርንበት ደረጃ ላይ ደርሰን እያለ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ያለ ምንም ማመንታት ፈቃድህን እንቀበላለን። አንተ የምትፈቅደውን አሜን በማለት እንቀበላለን›› አልን። እንደማስበው ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ፈቃድ የምንሸነፍበት ደረጃ ላይ እግዚአብሔር ጫና እና ውጥረት እንዲደርስብን አድርጎ ነበር። ምንጊዜም ቢሆን እንደዚያ ስታደርጉ እፎይታ ይኖራል። ስለ ምን እየጸለያችሁ እንደ ሆነ በትክክል ላታውቁ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን ሁሉን ቻይ የሆነ፣ ሁሌም ለእናንተ መልካምን የሚያስብ የሚወዳችሁ አባት እንዳላችሁ ታውቃላችሁ።

ከጌታ ጋር ያሳለፍኩዋቸው ዘመኖችን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ስመለከት በራሴ መንገድ እንድሄድ ስላልፈቀደባቸው ጊዜዎች ደግሜ ደጋግሜ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እኔ በምፈልገው መንገድ ነገሮችን አድርጌ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ አደገኛ ይሆን እንደ ነበር ከተለያዩ ሁኔታዎች ማዬት ችያለሁ።



መንግሥታትን የሚለውጥ ዓይነት ጸሎት እንድጸልይ እኔን የመራበትንም ጊዜዎች አስታውሳለሁ። በእኔና በአንድት ተሰብስበው በነበሩ አማኞች ጸሎት ታሪክ የተለወጠባቸው በርካታ ጊዜዎችን ለእግዚአብሔር ክብር መናገር እችላለሁ። በእናተም ጸሎት ሊለወጡ ይችላሉ። እስቲ ሁለት ምሳሌዎች ልስጣችሁ።

በብሪታንያ መከላከያ ሠራዊት ከተጠራሁና በሚገርም ሁኔታ ከጌታ ጋር ከተገናኘሁ አንድ ዓመት በኋላ፣ እኔ የነበርኩበት ክፍል ወደ ሰሜን አፍሪካ ተላከ፤ በዚያ ቦታ እንደ ሆስፒታል ሠራተኛ ማገልገል ጀመርኩ። በብሪታንያ መከላከያ ሠራዊት ታሪክ ውስጥ በጣም ረጅም በሆነ ሽሽት ማለት ሊቢያ ካለው አላጋላ እስከ ካይሮ መግቢያ ድረስ ሰባት መቶ ማይሎች በላይ ሠራዊቱ ሲሸሽ እኔም የዚያ ሽሽት ተካፋይ ሆንኩ። ሰባት መቶ ማይሎች መሸሽ በተለይም በበረሐ ውስጥ በጣም አታካችና ቅስምን የሚሰብር መሆኑን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ።

በዚያ ጊዜ የመካከለኛው ምሥራቅ ዕጣ ፈንታ አጠራጣሪ ሁኔታ ውስጥ ወድቆ ነበር። የአክሲስ ኃይሎች ወደ ፊት ገፍተው ካይሮን ከያዙ ስዊዝ ካናልን መቆጣጠርና የብሪታንያ መንግሥትን ዋና የሕልውና መስመር የሆነውን አንዱን መቁረጥና በዚህም ምክንያት ምድረ እስራኤልንና በመካከለኛው ምሥራቅ ያሉ የነዳጅ ምንጮች በሙሉ በእነርሱ እጆች ይሆኑ ነበር።

ለዚያ ሽሽት ብዙ ነገሮች በምክንያትነት ሊቀርቡ መቻላቸው ምንም ጥርጥር የለበትም፤ እኔን በጣም ያሳሰበኝ የነበረ አንድ ነገር ባለ ሥልጣኖቹ ከበታቻቸው በነበሩ ሰዎች ላይ እምነት የሌላቸው መሆኑ ነበር። የብሪታንያ ጦር ባለ ሥልጣኖች ራስ ወዳድ፣ ኃላፊነት የማይሰማቸውና ሥርዓት የሌላቸው ነበሩ። እኔ ራሴ የወታደር ባለ ስልጣን ልጅ ነበርኩ፤ ይህን የምለው ምን ማለቴ እንደሆነ በሚገባ አስቤበት ነው። አንዱ ምሳሌ ይህ ነበር። ከፍተኛ የውሃ እጥረት ነበረብን።

አንድ ወታደር ለሚያስፈልገው ሁሉ ማለት ለመታጠብ፣ ጺም ለመላጨት፣ ለመጠጣት፣ ምግብ ለማብሰል ለሁለት ቀን አንድ ጠርሙስ ውሃ ነበር የሚሰጠው። ወደ ባለስልጣኖቹ ምግብ ቤት ስትሄዱ ግን በአንድ ምሽት ከውስኪያቸው ጋር የሚጠጡት አንድ ወታደር ለማንኛውም ነገር ከሚጠቀምበት የበለጠ ውሃ በቀላሉ ማየት ይቻላል።

ያኔ ገና አዲስ አማኝ ነበርኩ። የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ለመካፈል ምንም ዕድል አልነበረኝም። ያሉኝ መጽሐፍ ቅዱሴ እና መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነበሩ በዓላማ ስለዚህ ሁኔታ መጸለይ መቻል አለብኝ በማለት አሰብኩ። ምን እንደምጸልይ ግን አላውቅም። ስለዚህም እንዲሁ በገርነት፣ ‹‹ጌታ ሆይ ስለ ምን እንድጸልይ እንደምትፈልግ አሳየኝ›› በማለት መጸለይ ጀመርኩ።

‹‹ጌታ ሆይ፣ ለአንተ ክብር በሚሆንበት መንገድ በእነርሱ በኩል ድል የምታስገኝበት መሪዎች ስጠን›› በማለት እጸልይ ለነበረው ጸሎት እግዚአብሔር ግልጽ የሆነ መልስ ሰጠኝ ያንን ጸሎት በጸለይኩ ጊዜ በጌታ ገና ዓመት እንኳ አልሆነኝም ነበር። ዘወትር ያንን መጸለይ ጀመርኩ።

ምን እየሆነ እንደ ነበር ባላውቅም እግዚአብሔር ግን በፍጥነት መንቀሳቀስ ጀምሮ ነበር። የብሪታንያ መንግሥት በመካከለኛው ምሥራቅ ሰሜን አፍሪካ ለነበረው ጦሩ አዲስ አዛዥ ሾመ። ይህ ሰው ኃላፊነቱን ለመያዝ ወደ ካይሮ በመብረር ላይ እያለ አውሮፕላኑ አደጋ ገጥሟት ሞተ። ስለሆነም ጦርነቱ ተፋፍሞ በነበረበት ወሳኝ ወቅት የብሪታንያ ጦር ያለ አዛዥ ነበር።

በወቅቱ የብሪታንያ ጠቅላይ ሚንስትር የነበሩት ዊንስተን ቸርችል ከሞላ ጎደል በራሳቸው ውሳኔ አንድ ይህን ያህል ያልታወቀ ባለ ሥልጣን ስለ ሾሙ ከብሪታንያ ተነሥቶ መምጣት ጀመረ። የሠውየው ስም ቤርናርድ ሞንትጎሞሪ ይባል ነበር። ሞንጎሞሪ ጥሩ ክርስያን እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር። የተዋጣለት አዛዥና፣ ከፍተኛ ሥነ ሥርዐት ያለው ሰው ነበር።



የብሪታንያ ጦርን እንደ ገና ማደራጀት ጀመረ። ሥርዓትና ሞራልን እንደ ገና አጠናከረ፤ የባለ ሥልጣኖቹን ዝንባሌን ... ለወጠ። በኅብረቱ ጦር ታሪክ በሙሉ የመጀመሪያው ታላቅ ድል የተገኘበት ታዋቂው የኤል አላሚን ውጊያ የተደረገው ያኔ ነበር። ከሰሜን አፍሪካ የኅብረቱን ጦር ሂደት ለወጠ።

በዚያ ጊዜ እኔ እየገሠገሠ በነበረው የብሪታንያ ሠራዊት ጀርባ ጥቂት ርቀት ላይ ከጦሩ የበረሃ አምቡላንስ ጋር እየሠራሁ ነበር። በአንድ ከባድ መኪና ላይ አንድ ተንቀሳቃሽ ሬዲዮ ነበር። የኤል አላሚን ጦርነት ከመደረጉ በፊት በሞንት ጎሞሪ ዋና ዕዝ ጣቢያ እየተደረገ ስለ ነበረው ዝግጅት ዜና ዘጋቢው ሲናገር እየሰማሁ ነበር። ሞንት ጎሞሪ መጥቶ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ባለ ሥልጣኖችና ሰዎቹን እንዳደራጀና፣ ‹‹በጦርነት ብርቱ የሆነውን እግዚአብሔር ድል እንዲሰጠን እንለምነው›› በማለት መናገሩን ገለጸ።

ይህን ዜና እየሰማሁ እያለ፣ ‹‹ሰማያዊ ኤሌክትሪክ›› የምለው ንዝረት ከራሴ እስከ እግሬ ድረስ ተሰማኝ። ይህ የጸሎትህ መልስ ነው በማለት በጸጥታ ሆኖም በእርግጠኝነት እግዚአብሔር ተናገረኝ።

ስለሆነም ጸሎት የታሪክ ሂደትን መለወጥ እንደሚችል የተማርኩት ገና የክርስትና ልምምዴ መጀመሪያ ላይ ነበር። የሞንትጎሞሪ ልደት 100ኛ ዓመት በሚከበርበት ጊዜ ሞንትጎሞሪ በዚያ ወቅት በሰሜን አፍሪካ ያደረገውን ዘመቻ ያህል በሰው ልጅ ታሪክ ማንኛውም የብሪታንያ ጀኔራል አድርጎ እንደማያውቅ ከአንድ ጋዜጣ አነበብኩ። ስጸልይ እግዚአብሔር ክብር የሚሰጠውን ሰው አስነሣ። ያንን ታምናላችሁ? ጸሎታችሁ ታሪክን መለወጥ እንደሚችል ታምናላችሁ? ስትጸልዩ እግዚአብሔር ነገሮችን እንደሚያደርግ ታምናላችሁ?

ምናባትም አንዳንድ ሰዎች፣ ‹‹ያ ድፍረት ነው። አንተ ብትጸልይም ሌሎች ሰዎችም እየጸለዩ እንደ ነበር እርግጠኛ ነን›› ይሉ ይሆናል። ያለ ጥርጥር ሌሎች ሰዎችም በብሪታንያ እየጸለዩ ነበር። ያም ሆኖ ግን ይህም እውነት ነው -አንድ ሰው ብቻ እንኳ ቢጸልይ፣ የእምነት ጸሎት ቢጸልይና የእግዚአብሔርን መስፈርት ቢያሟላ ለዚያ ሰው ጸሎት እግዚአብሔር መልስ ይሰጣል።

ጸሎትን አስመልክቶ ሁለት አማራጮች አሉ። እግዚአብሔር ይመልሳል ወይም ደግሞ አይመልስም። ለጸሎት መልስ የማይሰጥ ከሆነ መጸለይ ሞኝነት ነው፤ ለጸሎት መልስ የሚሰጥ ከሆነ ግን አለመጸለይ ሞኝነት ነው። ይህ የማይናወጥ አቋሜ ነው። ሆኖም ቿዚህ ላይ አጽንዖት መስጠት የምፈልገው ትምህርት ጸሎቱን እግዚአብሔር ሊሰጣችሁ የሚገባ መሆኑን ነው። ጦር እንደምትይዙ ያዙት። አነጣጥራችሁ ያዙት። በፍጹም ወደ ኋላ አትመልሱት።

ጸሎት ታሪክን እነደሚለውጥ ልሰጣችሁ የምፈልገው ሁለተኛ ምሳሌ የተፈጸመው በ1960 በኬንያ ከተማሪዎችና አስተማሪዎች ጋር እሠራ በነበረበት ጊዜ ነበር። በዚያ ጊዜ በጥቂት ዓመት ውስጥ ኬንያ ነጻነቷን ከብሪታንያ መንግሥት የምትቀበልበት አካባቢ ነበር። አገሪቱ በከፍተኛ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ነበረች። ለነጻነት ይዋጋ የነበረው ማው ማዎ አገሪቱን ለሁለት ከፈለ፤ በነጮችና በጥቁሮች መካከል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አፍሪካዊ ጎሳዎች መካከልም ጠላትነትና መጠራጠርን ፈጠረ። ልክ በዚያው ወቅት በስተ ምዕራብ ያለችው የቤልጂየም ኮንጎ ነጻነቷን ከቤልጂየም ብትቀበልም ወዲያውኑ መራራ የእርስ በርስ ውጊያ ውስጥ ገብታ ነበር። እንደ ኮንጎ ሁሉ፣ ምናባትም ከዚያ በከፋ መልኩ ኬንያም ተመሳሳይ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ እንደምትገባ ብዙ የፖለቲካ አዋቂዎች እያመለከቱ ነበር። በዚያው ዓመት ነሐሴ ወር ላይ ለአፍሪካውያን ወጣቶች በተዘጋጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፈረንስ ከተናጋሪዎችቹ አንዱ ነበርኩ። ኮንፈረንሱ አንድ ሳምንት ከተካሄደ በኋላ ማጠናቀቂያው ምሽት ላይ ነበርን። ሉዓላዊና ልዩ በሆነ መንገድ መንፈስ ቅዱስ ይንቀሳቀስ ጀመር። አንድ ደረጃ ላይ ሁሉን ቻይ የእግዚአብሔር ችሎት ጋር እንደ ተገናኘንና ያኔውኑ በዚያ መጠቀም የእኛ ኃላፊነት እንደ ሆነ ተሰማኝ። ስለሆነም ወደ መድረኩ ሄድኩና እየጸለዩ የነበሩትን ወጣቶች ጸጥ አሰኘሁ። ስለ አገራቸው የወደ ፊት እጣ ፈንታ አጥብቀው እንዲጸልዩ ተናገርኩ። ክርስቲያኖች ለመንግሥታቸው የመጸለይ ኃላፊነት እንዳለባቸውና አገራቸው ከባድ ከሆነ ችግር ጋር ፊት ለፊት እየተጋፈጠች እንደ ሆነ አመለከትኩ። ምናልባትም አገራቸውን ከእልቂት የሚያድን የእነርሱ ጸሎት ብቻ ሊሆን እንደሚችል



ነገርኳቸው። በቦታው የነበሩ እነዚያ ሦስት መቶ ወጣቶች ከዐሥር ደቂቃ ያህል በአንድ ልብ ጸለዩ። ያ ጸሎት ከተሳተፍኩባቸው ከፍተኛ ልምምዶች አንዱ ነበር። ከዚያም፣ ሁሉም ጸጥ ካሉ በኋላ መድረክ ላይ ከጎኔ ቆሞ የነበረ አፍሪካዊ ወጣት ለአፍሪካውያን ወገኖቹ ረጋ ባለ ሁኔታ መናገር ጀመረ። ‹‹እየጸለይን እያለ ጌታ ራእይ እንደሰጠኝ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ቀይ ፈረስ ላይ የተቀመጠ ሰው አየሁ - ፈረሱ አስፈሪና አደገኛ ነበር - ከወደ ምሥራቅ ወደ ኬንያ እየመጣ ነበር። ከእርሱ ኋላ እንደ እርሱ አስፈሪና አደገኛ የሆኑ ሌሎች ቀያይ ፈረሶችም ነበሩ። ይሁን እንጂ እየጸለይን እያለ እነዚያ ቀያይ ፈረሶች አቅጣጫ ለውጠው ከኬንያ ወደ ሰሜን ሔዱ›› አለ።

እያይዞም፣ ‹‹ይህን በማሰላሰል ላይ እያለሁ፣ እግዚአብሔር እንዲህ በማለት ተናገረኝ፣ በኬንያ ላይ እየመጣ ያለውን ችግር መመለስ የሚችል የሕዝቤ ጸሎት ልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል ብቻ ነው።

የቀጣዮቹ ዓመቶች ታሪክ ዝርዝር ውስጥ አልገባም፤ እግዚአብሔር ለዚያ አፍሪካዊ ወጣት የሰጠው ራእይ በትክክል መፈጸሙን ግን እናገራለሁ። ከሦስት ወይም አራት ዓመት በኋላ አገሪቱን ለመቆጣጠር ከምሥራቅ ወደ ኬንያ ለመዝለቅ ሙከራ ያደረገ አደገኛ የኮሚኒስቶች ሤራ የመጀመሪያው የኬንያ ፕሬዘዳንት በነበሩት ጆሞ ኬንያታ አስተዋይና ፈጣን ርምጃ ከሸፈ። ኮሚንስቶች እንዳሰቡት ወደ ኬንያ ዘልቀው አልገቡም። ወደ ሰሜን ዞረው ሶማሊያን በሁኋላም ኢትዮጵያን ያዙ፤ አገሪቱም የታጠቁ ኮሚንስቶች ካምፕ ሆነች።

ይሁን እንጂ፣ ከዚያ ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ በክፍለ አህጉሩ እያቆጠቆጡ ካሉ ከሃምሳ አዲስ አፍሪካዊ አገሮች የበለጠ ኬንያ የተረጋጋችና እያደገች ያለች አገር ሆናለች። እንደ እውነቱ ከሆነ የፖለቲካ አዋቂዎች ያመለከቱት ያንን አልነበረም። ያ በአገሪቱ ታሪክ ቀውስ ውስጥ የተቀናጀ፣ የተባበረና በእምነት የተደረገ ጸሎት ውጠት ነበር።

በዚያ መልኩ መጸለይ መቻል ከዚህ ዓለም ሀብት ሁሉ የበለጠ ዋጋ ያለው ነው። በዚያ መልኩ መጸለይ የሚችል ሰው ድል ካገኘ ጀኔራል ወይም ጀኔራሉን ከሚቆጣጠረው መንግሥት የበለጠ ተጽእኖ ማድረግ ይችላል።

የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደሚፈጸም ሁሉ በምድር እንዲፈጸም አዘውትሬ አልጸለይኩም። አንዳንዴ በራሴ ጥቃቅን ነገሮችና ውስንነት ስለምሸነፍ አብዝቼ የምጸልየው ስለ ራሴ ነው። በመሠረቱ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ መጸለይ ስሕተት አይደለም፤ ይሁን እንጂ፣ መላው ዝንባሌያችሁና ዓላማችሁ ከእግዚአብሔር ዓላማ በምድር መፈጸም ጋር እስኪጣጣም ድረስ በእውነት መለኮታዊ ውጤት አያስገኝም።

እግዚአብሔር አይለወጥም። ለምሳሌ ያህል እኔና እግዚአብሔር ሳንስማማ ብንቀር መለወጥ ያለበት ማን እንደ ሆነ ግልጽ ነው። ከዚህም በተረፈ በተለይ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቃችሁ አማኞች ከሆናችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ሳይስማሙ መኖር የማይመች ነገር ነው። መስማማት የምንችለው እንዴት ነው? መልሱ፣ ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር መጣጣም ነው። ፈቃዱን ለማወቅ የመጀመሪያዎቹ ቁልፎች የጌታ ጸሎት መጀመሪያ ላይ አሉ። ‹‹በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ።››

## የእግዚአብሔር ፈቃድን ማወቅ

በጣም ከምወዳቸው ምንባቦች አንዱ የሆነው ሮሜ 12 የእግዚአብሔር ፈቃድን ለማወቅ ተጨማሪ ቁልፎች ይሰጠናል። እኔ እንደምረዳው ሁሉም በመጀመሪያዎቹ ስምንት ቁጥሮች ውስጥ ይገኛሉ።

> እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁን ነው። መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ፣ ይህን ዓለም አትምሰሉ። እግዚአብሔር በሰጣችሁ እምነት መጠን ራሳችሁን በአግባቡ መዝኑ እንጂ፣ ከሆናችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዳታስቡ በተሰጠኝ ጸጋ እያንዳንዳችሁን እመክራለሁ። እያንዳንዳችን በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች እንዳሉን፤ እነዚህም ብልቶች አንድ ዐይነት ተግባር እንደሌላቸው ሁሉ፣ እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን። እንደ ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን፤ ለአንዱ የተሰጠው ስጦታ ትንቢት መናገር ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን ይናገር። ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተማርም ከሆነ ያስተምር፤ መምከር ከሆነ ይምከር፤ ለሌላው መስጠት ከሆነም አብዝቶ ይስጥ፤ ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር፤ ምሕረት ማድረግ ከሆነም በደስታ ይማር።
>
> **ቁጥር 1-8**

ቁጥር 1 ላይ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ነበር የጀመረው። ብዙ ጊዜ እንደምለው፣ እንግዲህ ወይም ስለዚህ የሚል ቃል ስታገኙ ለምን እንደ ሆነ መረዳት ይኖርባችኋል። ይህ እንግዲህ የእግዚአብሔርን፣ ምሕረትና ጸጋ መልእክት በተመለከተ ሲናገር ከነበረባቸው ካለፉት ዐሥራ አንድ ምዕራፎች ጋር ይያያዛል። ከዚያም፣ ‹‹ከዚያ አንጻር፣ ምን ማድረግ አለብን፤ ምላሻችን ምን መሆን አለበት?›› በማለት ይጠይቃል። የሚሰጠው መልስ፣ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ›› የሚል ነው።

ይህ ሁሉም በጣም ይባርከኛል። መጽሐፍ ቅዱስ እውነታን ያገናዘበ ነው። ብዙዎቻችን ልዕለ መንፈሳዊ የሆነ ነገር እንጠብቃለን። ከዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ መገለጽ በኋላ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ምን እንድናደርግ ትፈልጋለህ?›› በማለት እንጠይቃለን።

እርሱም፣ ‹‹ሰውነታችሁን እፈልጋለሁ›› ይለናል። አያችሁ፣ ሰውነታችንን ሲያገኝ፣ ሌሎች ብልቶቻችንንም ያገኛል።

ጳውሎስ እንዴት እንደምንሰጠውም ይናገራል፣ ‹‹ሕያው መሥዋዕት

አድርጋችሁ አቅርቡ።›› ሕያው መሥዋዕት መሆን ያለበት ለምንድነው? ምክንያቱም ጳውሎስ መጀመሪያ ከሚገደለው፣ ከዚያም መሠዊያ ላይ ከሚደረገው የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ጋር እያነጻጸረው ነበር። ስለሆነም ጳውሎስ፣ ‹‹ሰውነታችሁን ገድላችሁ መሠዊያ ላይ አታቅርቡ። በሕይወት እንዳለ መሠዊያ ላይ አቅርቡት›› እያለ ነው።

አንድ ነገር መሥዋዕት ሆኖ መሠዊያ ላይ ከቀረበ ከእንግዲህ የቀረበው ሰውዬ ንብረት የራሱ አይደለም፤ የእግዚአብሔር ነው። ስለሆነም እዚህ ላይ እግዚአብሔር፣ ‹‹እንደ ሕያው መሥዋዕት ሰውነታችሁን የእኔ መሠዊያ ላይ አቅርቡት። ከእንግዲህ የእናንተ አይደለም። ባለቤቱ እኔ ነኝ። በሰውነታሁ ላይ የሚሆነውን የምወስን እኔ እንጂ እናንተ አይደላችሁም። የት እንደምትሄዱ አትወስኑም፤ ምን እንደምትበሉ አትወስኑም፤ ምን እንደምትለብሱ አትወስኑም። ይህ የእኔ ውሳኔ ነው። ለሰውነታሁ ሙሉ ኃላፊነት እወስዳለሁ›› እያለ ነው ያለው።

ይህን በጥንቃቄ አስቡበት። እንዲህ ያለ ውሳኔ ስታደርጉ ከልባችሁ መሆኑን እርግጠኛ ሁኑ። የእንዲህ ዓይነት ውሳኔ ጠቀሜታዎችንም ተረዱ። እግዚአብሔር የእርሱ በሆነና እንዲሁ ለእርሱ በተሰጠ ንብረት የተለየ ዝንባሌ አለው። የእርሱ የሆነውን የማኖር ኃላፊነት ይወስዳል። ምናልባትም የችግራችሁ መልስ ይኸው መሆኑን ትረዱ ይሆናል። ሰውነታሁን ለእግዚአብሔር ስጡ። የሚበቃችሁን ያህል ስትታገሉት ኖራችኋል።

የሚቀጥለው ጥቅስ፣ ‹‹መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ›› ይላል።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የአስተሳሰብ ለውጥ ሊኖራችሁ ይገባል። አእምሮአችሁ መታደስ አለበት። እግዚአብሔር ያንን ማድረግ ይችላል፤ ሰውነታሁን እስክትሰጡት ድረስ ግን ያንን አያደርግም። ሰውነታሁን ከሰጣችሁት በኋላ ያኔ አእምሮአችሁን ያድሳል።



አእምሮአችሁ ከታደሰ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ታውቃላሁ። ብዙ ሰዎች ይድናሉ፤ ወደ መንግስተ ሰማይ እንደሚገቡም አስባለሁ፤ ይሁን እንጂ አእምሮአቸው በፍጹም ባለ መታደስ በዚህ ሕይወት ጨርሶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አያውቁም።

በሚቀጥለው ጥቅስ ደግሞ ጳውሎስ፣ ‹‹ እግዚአብሔር በሰጣችሁ እምነት መጠን ራችሁን በአግባብ መዝኑ እንጂ፣ ከሆናችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዳታስቡ በተሰጠኝ ጸጋ እያንዳንዳችሁን እመክራለሁ›› ይላል።

የታደሰ አእምሮ ትእቢተኛ አይደለም። እብሪተኛም አይደለም። ስለ ራሱ ብዙ የሚናገር አይደለም። ትሑት፣ ጭምትና እውናዊ ነው። ለምሳሌ አንድ ባንክ ውስጥ ሥራ አገኛችሁ እንበል። ሥራ በጀመራችሁ በመጀመሪያ ቀን ማናጀሩ ወንበር ላይ አትቀመጡም። በተመሳሳይ መልኩ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስትመጡም በመጀመሪያው ቀን ሐዋርያ እንደምትሆኑ መጠበቅ የለባችሁም። ቆሻሻ ወረቀቶችን ቅርጫት ውስጥ የሚጨምር ተራ ተላላኪ ለመሆን ፈቃደኛ ሁኑ። በመንፈሳዊ ሕይወት ወደ ላይ የመውጫው መንገድ የታችኛው መንገድ ነው። ዝቅ ብላችሁ የጀመራችሁትን ያህል በዚያው መጠን ፍጻሜያችሁ ከፍ ይላል።

ከዚያ ጳውሎስ ይህን በራሳችን እንደማናደርገው ይናገራል። የክርስቶስ አካል ብልቶች እንሆናለን። በዚያው አካል ውስጥ ለሚያኖረን ቦታ የሚሆን እግዚአብሔር የእምነት መጠን፣ የእምነት ልክ ሰጥቶናል። ቦታችንን ስናገኝ ለዚያ ቦታና ለዚያ ተግባር የሚያስፈልገን እምነት እንደሚኖረን እንረዳለን።

አያችሁ እጄ በጥሩ ሁኔታ ይሠራል፤ ግን በእጆቼ መሄድ ከሞከርኩ ችግር ላይ እወድቃለሁ። እጄ እጅ እንዲሆን እንጂ እግር እንዲሆን አልተፈጠረም። ብዙ ክርስቲያኖች እግር ሆነው ሳለ እጅ ለመሆን ይሞክራሉ፤ አፍንጫ ሆነው ሳለ ጆሮ መሆን ይሞክራሉ። በክርስትና ሕይወታችሁ እምነት እንዲኖራችሁ እየታገላችሁ ከሆነ እግዚአብሔር ያልወሰነላችሁን ነገር ለመሆን እየሞከራችሁ ለመሆኑ ማረጋገጫ ያህል ነው።

በመሠረቱ፣ የእምነት ሕይወት ፈተናዎችና ችግሮች አሉት፣ ሆኖም የሚንቀሳቀስ ነው። የማያቋርጥ ትግል አይደለም። በአካል ውስጥ ቦታችሁን ካገኛችሁ እግዚአብሔር በመደበላችሁ እምነት መጠን በዚያ ቦታ ስኬታማ ያደርጋችኋል። ከዚያም በመጨረሻ ቀለል ያለ ዝርዝር ሲደመደም ጳውሎስ በአካሉ ውስጥ ቦታችሁን ከያዛችሁ ለዚያ ቦታ የሚያስፈልጋችሁን ስጦታ እግዚአብሔር ይሰጣችኋል ይላል። ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይፈልጋሉ፤ እኔም እስማማለሁ፤ በጣም ግሩም ናቸው። ሆኖም ከአካሉ በተነጠለ ሁኔታ መፈለግ የለባቸውም። እንዲያውም በአካሉ ውስጥ ያላችሁን ቦታ እስካላወቃችሁ ድረስ ምን ዓይነት ስጦታዎች እንደሚያስፈልጓችሁ አታውቁም። የእኔ ልምምድ በትክክለኛው ቦታ ሲሆን፣ ትክክለኛ ስጦታዎችን መቀበል ነው።

እግዚአብሔር እኔን ወደ ነጻ ማውጣት ማለትም ሰዎችን ከአጋንንት ነጻ ወደ ማድረግ አገልግሎት ያመጣበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ። አንድ ጓደኛዬ ነጻ እንድትወጣ ባለ ትዳር እኅቱን እኔና ሊዲያ በኮሎራዶ ወዳረፍንበት ሆቴል ይዞ መጣ። ሴትየዋ የጭንቀት ምሳሌ ነበረች። ችግር ያለባት መሆኑ ግልጽ ነበር። ሴትየዋን ትኩር ብዬ አየኋትና፣ ‹‹ከ ... ነጻ መውጣት ይኖርብሻል›› በማለት ሲናገር ራሴን አገኘሁት። የስምንት አጋንንት ስም ዘረዘርኩ። ወዲያውኑ እንዴት ይህን አወቅሁ? በማለት ማሰብ ጀመርኩ። እግዚአብሔር የዕውቀት ስጦታ እንደ ሰጠኝ ተረዳሁ። ለምን? ጌጥ እንዲሆነኝ? አይደለም፣ እርሱ ባኖረኝ ቦታ ውጤታማ እንድሆን ስለሚያስፈልገኝ ነው።

ለሕይወታችሁ የእርሱን ፈቃድ ለማወቅ የምትፈልጉ ከሆነ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ሰውነታችሁን ለእግዚአብሔር የማቅረብ አስፈላጊነትን አያችሁ? አጥብቄ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። የሰውነታችሁ ተቆጣጣሪ እንዲሆን በእውነት ራሳችሁን ለጌታ አስረክባችሁታል? እግዚአብሔር ሆይ፣ ከእንግዲህ የአንተ ነው። በአንተ ኃላፊነት ሥር ነውእንደምትፈልገው አድርገው›› ብላችኋል?።



እንደዚያ አላደረጋችሁ ከሆነ ያንን ውሳኔ ለማድረግ ከዚህ የተሻለ ጊዜ የለም።

አንዴ ካደረጋችሁ እንደ ገና ወደ ኋላ የማትሉት በጣም ከባድ ውሳኔ ነው። ከዚህ ቅጽበት በኋላ እግዚአብሔር ፍጹም ትሆናላችሁ ብሎ አይጠብቅም። እውነተኛ የማያወላውል ልብ ያላችሁ እንድትሆኑ ግን ይጠብቃል። ሰውነታችሁን በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ የምታቀርቡበት ጊዜ አሁን መሆኑን በእውነት ከወሰናችሁ፣ ይህን ቀላል ጸሎት እንድታደርጉ እነግራችኋለሁ።

> ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ እኔን ከኃጢአቴ ለማዳንና የእግዚአብሔር ልጅ ለማድረግ በእኔ ቦታ መስቀል ላይ ስለ ሞትህ አመሰግንሃለሁ። ለአንተ ምሕረት ምላሽ እንዲሆን፣ ጌታ ሆይ፣ ሰውነቴን ለአንተ አቀርባለሁ። ሕያው መስዋዕት አድርጌ የአገልግሎት መሠዊያህ ላይ አኖረዋለሁ። ከእንግዲህ የአንተ እንጂ የእኔ አይደለም። ይህን መሥዋዕት ስለ ተቀበልህ ተመስገን። በኢየሱስ ስም አሜን።

በበለጠ ሁኔታ የእግዚአብሔር መንፈስ በምድር ላይ ወደሚንቀሳቀስበት ጊዜ እየመጣን ነው። ያለው ጊዜ አጭር መሆኑን የሚያውቅ ጠላታችን ከምንጊዜውም ይልቅ መሰጠታችንን ይፈትናል። በኋላ በሚኖሩን ምዕራፎች አካልን የጸሎት ቤት አድርጎ ስለ መገንባት የበለጠ እንማራለን። ይሁን እንጂ፣ በመጀመሪያ ስለ መንፈሳዊ ውጊያና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጸለይ ስለሚያስፈልጉን መሣሪያዎች እንመለከታለን። እስቲ አሁን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመረዳት ወደዚህ ጥልቅ የጸሎት ቦታ እንሂድ።

# 6

## ለመንፈሳዊ ውጊያ መንፈሳዊ መሣሪያዎች

**ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀ በክርስቶስ አንድ ሰው አውቃለሁ። የተነጠቀው በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ አላውቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል። (2 ቆሮንቶስ 12፡2)**

ይህ ጥቅስ ከአንድ የበለጠ ሰማይ መኖሩን ግልጽ ያደርግልናል። ጳውሎስ አንድ ሰው ዐውቃለሁ ይላል በነገራችን ላይ ይህ ወደ ሦስተኛው ሰማይ የመነጠቅ አስደናቂ ልምምድ ያገኘው ‹‹በሰው አንደበት ሊገለጥ ነው ብዬ አላምንም (2 ቆሮንቶስ 12፡4)።

ሦስተኛው ሰማይ ካለ የመጀመሪያና ሁለተኛ ሰማይም መኖሩን መገመት እንደሚቻል አምናለሁ። በአጭሩም ቢሆን እነዚህ ሰማዮች ቦታቸው የት እንደ ሆነና እነማን እንደሚኖሩባቸው እንድንመለከት እፈልጋለሁ። በድል እንድንጸልይ ከተፈለገ ይህን መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው ሦስተኛው ሰማይ ገነት ያለበት ቦታ እንደ ሆነ ጳውሎስ ያመለክታል። በአሁኑ ጊዜ በሞት የተለዩ ቅዱሳን መንፈሶች የሚሄዱት ወደዚህ ቦታ ነው፤ ሁሌም ግን እንደዚያ አልነበረም።



ሲኦል ማለትም በምድር ታችኛው ክፍል ባለ የተለየ ቦታ የሞቱ ቅዱሳን ይኖሩ የነበረበት ጊዜም ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን አብርሃምና ቅዱሳን ሁሉ፣ ከሞቱ ኃጢአተኛ ነፍሳት በታላቅ ገደል ወደሚለይ ወደ አንድ ልዩ ቦታ ይሄዱ እንደ ነበር ታስታውሱ ይሆናል። ከኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ገነት ተከፈተ። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ገነት ሁሉን የሚችል አምላክ ባለበት ሦስተኛው ሰማይ ነው ያለው። መጽሐፍ ቅዱሥ መካከለኛው ወይም ሁለተኛው ሰማይ ብለን መጥራት ስለምንችለው ቦታም ይናገራል። ይህ ቃል የተወሰደው ከራእይ መጽሐፍ ነው። ለምሳሌ ያህል ዩሐንስ፣ ‹‹ከዚያም ሌላ መልአክ በሰማይ መካከል ሲበር አየሁ›› ብሏል(ራእይ14፡6)። ‹‹መካከለኛው ሰማይ›› ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ሁለተኛው ሰማይ የሰይጣን ማዘዣ ጣቢያ ነው። በምድር ላይ ጥፋት ለማድረስ፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ ዓላማ፣ በረከትና ምሕረት ለመቃወም እርሱና መላእክቱ የሚቻላቸውን ሁሉ የሚያደርጉት ከዚያ ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስለዚያ በስፋት እናያለን።

የመጀመሪያው ሰማይ በየምሽቱ ከዋክብትን የምናይበት በዓይን የሚታየው ሰማይ ነው። የሰው መኖሪያ ቦታ ጣሪያ ነው ማለትም ይቻላል። ስለሆነም እግዚአብሔር የሚኖረው በሦስተኛው ሰማይ መሆኑን፣ የሰው ልጅ የሚኖረው በመጀመሪያው ሰማይ አጠገብ መሆኑን እናያለን። በሁለቱ መሐል የሰይጣንና የወደቁ መላእክቱ አመፀኛ መንግሥት ያለበት ሁለተኛ ሰማይ አለ።

ታዲያ፣ ይህ እግዚአብሔር የሚሰማው ዓይነት ጸሎት ከመጸለይና መልስ ከመቀበል ጋር ምን ያገናኘዋል? በጥቂቱ ያገናኘዋል ስለ መንፈሳዊ ግጭት ስንጸልይ ስለሚገጥመን ተቃውሞ ስዕል ይሰጠናል።

### ሰማያዊ ዕይታ

መንፈሳዊ ውጊያን ለመረዳት ከማን ጋር እንደምንዋጋም መረዳት ይኖርብናል። በአሁኑ ጊዜ የሰይጣን ማዘዣ ጣቢያ በሰማያት እንደ ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ይገልጻሉ። ይህን በተመለከተ በኤፌሶን መልእክቱ ጳውሎስ በጣም ግልጽ ስዕል ይሰጠናል፤ ‹‹ምክንያቱም ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፣ ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኃይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ክርኩሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው››(ኤፌሶን 6፡12)። የንጉሥ ጀምስ

/King James/ ትርጉም ተመሳሳይ ቢሆንም፣ በጣም ትክክል የሆነ ትርጉም አላቀረበም። እስቲ ይህን ጥቅስ በመከፋፈል የግሪኩ የሚለውን ለመረዳት እንሞክር።

ምክንያቱም ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን
ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች ከሥልጣናትና ከኃይላት ...

በኤፌሶን መልእክትና በሌሎችም ምንባቦች ሥልጣናትና ኃይላት የተሰኙት ቃሎች ብዙውን ጊዜ በአንድነት ይያያዛሉ። ሥልጣናት የሚለው ቃል ገዦች ከሚለው የግሪኩ ቃል በቀጥታ የተወሰደ ነው። ኃይላት የሚለው ቃል ባለ ሥልጣኖች ማለት ነው። ስለሆነም እንደ አማኞች ውጊያ የምንገጥመው ከሥጋና ከደም ጋር፣ ከሰብዓዊ ፍጡራን ጋር ሳይሆን ከአገዛዞችና ከሥልጣናቸው ክልል ጋር ነው ማለትን እመርጣለሁ። እንዲሁም፣

ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች ... ጋርም ነው።

የበለጠ ቃል በቃል ትርጉም ይሆን የነበረው፣ ‹‹አሁን ካለው ጨለማ ዓለም ገዦች ጋር ነው›› ቢባል ነበር መልካም የሚሆነው። ይህ አሁን ያለው ዓለም ጨለማ አገዛዙ የሚከናወንበት የእዝ ጣቢያ አለው። ዕዝ ጣቢያው መካከለኛው ሰማይ ሲሆን ገዢው ሰይጣን ነው። በኤፌሶን 2፡2 ሰይጣን፣ ‹‹በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኃይላት ገዥ›› ተብሏል። እንግዲህ እርሱ አየር ተብሎ የተገለጸው ሥልጣን ክልል ገዢ ነው ማለት ነው። ብዙ ሰዎች ሰይጣን በምድር ባሉ ዋሻዎች ውስጥ የሚኖር ይመስላቸዋል። እርሱ በሰማያዊ ቦታ እንጂ እዚያ አይደለም። መቼም፣ እርሱ ያለው እግዚአብሔር ባለበት ሰማይ ውስጥ እንደማይሆን ግልጽ ነው፤ ከዚያ ተጥሏል። እንዲህ ሲባል ደግሞ ምድር ላይ ነው ማለት አይደለም። ራእይ 12፡9 ከሰማያዊ ቦታ ወደ ምድር የሚጣልበት ጊዜ እንደሚመጣ ይነግረናል። በቀረው አጭር ጊዜ የሚቻለውን ሁሉ ክፉ ነገር እንደሚያደርግም ይነግረናል። (ምዕራፍ 7 ላይ ይህንን በስፋት እናያለን)። ያ ራእይ 12 ላይ ያለው ክፍል እስኪፈጸም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ግን የዕዝ ጣቢያው መካከለኛው ሰማይ ላይ ይሆናል። በተጨማሪም የምንጋደለው-በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው።



እስቲ አሁን ደግሞ የኤፌሶን 6፡12 የበለጠ ቃል በቃል ትርጉም ይሆን ነበር ያልነውን እንመልከት-

ውጊያ የምንገጥመው ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፣
ከአገዛዝና ከሥልጣናቸው ክልል፣ አሁን ካለው ጨለማ
ዓለም ገዦች ጋር፣ በሰማያዊ ስፍራ ካሉ መንፈሳዊ
የአመፅ ኃይሎች ጋር ነው።

የሚናገረው ስላለንበት መንፈሳዊ ግጭት ነው። በትንቢተ ዳንኤል ይህ ውጊያ በመካሄድ ላይ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ግልጽ የሆነ ስዕል ያቀርብልናል።

## ውጊያ በሰማያዊ ቦታ

ከእስራኤል ወደ ባቢሎን የተወሰደው ወጣቱ ዳንኤል የወገኖቹን ሥነ ጽሑፍ በትጋት በማጥናት ነው የኖረው። ከዚህም የተነሣ የባቢሎናውያን ምርኮ ትንቢት ቀነ ገደብ እያከተመ እንደ ነበር ተገነዘበ። ‹‹በዘመነ መንግስቱ በመጀመሪያው ዓመት፣ እኔ ዳንኤል ለነቢዩ ለኤርምያስ በተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ የኢየሩሳሌም መፈራረስ ሰባ ዓመት እንደሚቆይ ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተዋልሁ›› (ዳንኤል 9፡2)።

ዳንኤል ስለዚህ እየመጣ ስላለው ፍጻሜ እየጸመ መጸለይ ጀመረ። ‹‹በዚያን ጊዜ እኔ ዳንኤል ለሦስት ሳምንት አለቀስሁ፤ ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ምርጥ ምግብ አልበላሁም፤ ሥጋም ሆነ የወይን ጠጅ አፌ አልገባም፤ ቅባትም አልተቀባሁም›› (ዳንኤል 10፤2-3)።

ዳንኤል እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን አይቶ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ በዚህ ጉዳይ እኔም ከአንተ ጋር ነኝ። በዚያ መልኩ ተቀበለኝ። የአንተ ተስፋ ተፈጽሞ እስካይ ድረስ ከዚህ በፊት ካደረግሁት በተለየ ሁኔታ ራሴን ለጸሎትና ጾም እሰጣለሁ። የሚል ምላሽ ሰጠ።

የጸሎታችን ብርቱ አካል ከመሆኑ አንጻር በተለይ ደግሞ በመጨረሻዎቹ ቀኖች ያለችው ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ስለ ጾም ርዕስ ጉዳይ ምዕራፍ 8 ላይ እንመለከታለን። ለአሁኑ ግን አንድ ዐይነት መንፈሳዊ ሀዘን መግለጫ መሆኑን እናስተውል። በጽዮን ለሚያለቅሱትም (ኢሳይያስ 61:3 ይመ) ተፈጥሮአዊ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቤት እና የእግዚአብሔር ሕዝብ ጉስቁልና ተሰምቷቸው መንፈሳዊ ለቅሶ ለሚያለቅሱ የደስታ ዘይት እንደሚሰጥ እግዚአብሔር ተናግሯል።

በተራራው ስብከቱ ኢየሱስ፣ ‹‹የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መጽናናትን ያገኛሉና›› አለ(ማቴዎስ 5:4)። ይህን በተመለከተ ለመንፈስ ቅዱስ በጣም ንቁ መሆን እንደሚገባን ማሳሰብ እፈልጋለሁ። መንፈስ ቅዱስ ሲያጽናናን ለማዘን መሞከር የለብንም፤ መንፈስ ቅዱስ እንድናዝን ሲጠራን የራሳችንን የደስታ ጊዜ ለማድረግ መሞከር የለብንም።

በማልቀስ፣ በጸሎትና እግዚአብሔርን በመጠበቅ ዳንኤል 21 ቀን አሳለፈ። በጣም መሠረታዊ ከሆነ የምግብና መጠጥ ውጪ ከሌላው ሁሉ ተቆጠበ እንጂ ጾሙ ሙሉ በሙሉ አልነበረም። ሦስተኛው ሳምንት መጨረሻ ላይ በመጨረሻዎቹ ቀኖች እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን ዓላማ መገለጽ ይዞ ሊቀ መልአኩ ገብርኤል ወደ ዳንኤል ተላከ። ምዕራፍ 10 የተቀረው ክፍልና ቀጥሎ ያሉት የዳንኤል ሁለት ምዕራፎች ስለ መልአኩ መምጣት፣ ስለ መታየቱና ይዞት ስለ መጣው መገለጥ ይገልጻሉ። መንፈሳዊ ውጊያን ለመረዳት ዓላማችን መልአኩ ስለ ታየበት ጊዜ ሁኔታ እንመልከት። ደግሞም እንዲህ አለኝ ‹‹ዳንኤል ሆይ አትፍራ፤ ማስተዋልን ለማግኘትና በአምላክህም ፊት ራስህን ለማዋረድ ከወሰንህበት ከመጀመሪያው ቀን እንሥቶ ቃልህ ተሰምቷል፤ እኔም የቃልህን መልስ ይዤ መጥቻለሁ›› (ዳንኤል 10:12)። የዳንኤል ጸሎት የተሰማው መጸለይ የጀመረ ቀን ነበር ሆኖም፣ ሦስት ሳምንት ድረስ መልአኩ አልደረሰም ነበር። በመካከሉ የሆነው ምንድነው? ቀጥሎ ያለው ቁጥር፣ ‹‹ነገር ግን የፋርስ መንግሥት አለቃ ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ ከዋናዎቹ አለቆች አንዱ የሆነው ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም በዚያ ከፋርስ ንጉሥ ጋር



ተውሁት›› ይላል(ቁጥር13)።

መልአኩ ስለ፣ ‹‹የፋርስ መንግስት አለቃ›› ሲናገር ስለ ሰብዓዊ ፍጡር መናገሩ አልነበረም። በመካከለኛው ሰማይ ስላሉ የጨለማ መላእክት ስለ አንዱ ነበር የተናገረው። ገብርኤል ጉዞውን የጀመረው ዳንኤል መጸለይ በጀመረ መጀመሪያ ቀን ነበር፤ በሰማያዊ ስፍራ እየተደረገ የነበረ መናፍስታዊ ውጊያ ግን መምጣቱን አዘገየ። መልካሞቹ ቅዱሳን መላእክት የጨለማ መላእክት የሰይጣን መላእክት ተቃውሞ ገጠማቸው። ሆኖም መልአኩ የሚያልፍበትን መንገድ ያዘጋጀ ዳንኤል በምድር ያደረገው ጸሎት እንደ ነበር እናስተውል። ጸሎት ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን አያችሁ? የሚያልፍበት መንገድ ለማግኘት ሊቀ መልአኩ በዳንኤልና በጸሎቱ መደገፍ ነበረበት።

ነገሩ የተጀመረው በምድር እንጂ በሰማይ እንዳልነበረም እናስተውል። ዳንኤል ነገሮች እንዲንቀሳቀሱ አደረገ። በአንዳንድ መልኩ ዛሬም እንደዚያው እንደሆነ አስባለሁ። እግዚአብሔርን መጠበቅ የለብንም፤ እግዚአብሔር እየጠበቀን ነው። ስንንቀሳቀስ ሰማይ ይንቀሳቀሳል። ይህን ተከትሎ ግጭት ይነሣል፤ በምድር የምናደርገው ጸሎት መፍትሔ ይሰጠዋል። አማኖች የሆንንና እንዴት መጸለይ እንዳለብን የምናውቅ ወገኖች አብዛኞቻችን መረዳት ከምንችለው በላይ በጣም አስፈላጊዎች ነን።

ይህ ቃል ሌላም ነገር ያሳየናል። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለአንዳች ነገር ብንጸልይም ወዲያውኑ መልሱን የማናገኝበትን ምክንያት ያሳየናል።

እስቲ በዚህ መልኩ እንረዳው ሦስቱ ሰማዮች አንዱ ከሌላው ላይ በመሆን በሦስት ደረጃዎች ነው ያሉት። የአማኞች ጸሎት ከምድር ሲወጣ መልሱን የሚያመጣው መልአክ በእግዚአብሔር ቃል ታዝዞ ከሦስተኛው ሰማይ ወደ ታች ይመጣል። በሁለቱ መካከል ግን መካከለኛው ሰማይ ላይ ያሉ ክፉ አለቃ መልሱን እንዳይደርስ ለማድረግ ይሠራል። አማኞች ‹‹ሳይታክቱ›› ሲጸልዩ መልሱ ይመጣል። እንግዲህ ጸሎቱና መልሱ የሚገናኙበት ነጥብ ድል የሚገኝበት ነው።

‹‹ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱ መጸለይ እንደሚገባቸው›› ኢየሱስ የተናገረው በዚህ ምክንያት ነበር(ሉቃስ 18፡1)፡፡ እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ሐሳብ እጃችን እንዲገባ ከፈለግን ብዙ ጊዜ ሳንታክት መጸለይ ይኖርብናል፡፡ (ይህን በተመለከተ ምዕራፍ 8 ላይ ስለ ጾም ከምናያቸው የበለጠ እንማራለን)፡፡

ግን ልዩነቱን ልብ አድርጉ፡፡ ‹‹ሳንታክት›› መጸለይ ያለብን አንዳንዶች እንደሚያስቡት በእግዚአብሔር በኩል ቸልተኝነት ወይም ማመንታት በመኖሩ አይደለም፡፡ ሳንታክት የምንጸልየው በመካከለኛው ሰማይ እግዚአብሔር ለእኛ ማድረግ የሚፈልገውን መልካም ነገር ሁሉ የሚዋጋ ሰይጣናዊ ተቃውሞ ስላለ ያንን ጥሶ ለማለፍ ነው፡፡

ለመንፈስ ንቁዎች ከሆናችሁ መቼ ድሉ እንደ ተከናወነ ታውቃላችሁ፡፡ በመንፈሳዊ ልምምዴ የጸለይኩበት ነገር መልስ ማግኘቱን ያወቅሁባቸው ጊዜዎች ነበሩ፡፡ እንዲህ ሲሆን፣ ድል አግኝተናል ማለት ነው፤ ማሸብሸብና መዘመር እንችላለን ማለት ነው፡፡ ከእንግዲህ ውጊያው አብቅቷል፡፡ የቀረው ምርኮ መሰብሰብ ብቻ ነው፡፡ ከኢዮሳፍጥ ታሪክ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነንን ጥቂት ቆየት ብሎ እናያለን፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት በሚያቀርቡት መሠረት ይህ የመንፈሳዊ ውጊያ መሠረታዊ ስዕል ነው፡፡ መልአኩ ከዳንኤል ተለይቶ ሲሄድ፣ ‹‹የፋርስን አለቃ ለመውጋት በቶሎ እመለሳለሁ፤ እኔም ስሄድ የግሪክ አለቃ ይመጣል(ዳንኤል 10፡20) በማለት ተጨማሪ መረጃ ሰጥቶት ነበር፡፡

የፋርስ አለቃ የፋርስ መንግሥትን የሚገዛ ሰይጣናዊ መልአክ ነበር፡፡ ይህ ለዳንኤል በጣም አስፈላጊ ነበር፤ ምክንያቱም በዚያ ጊዜ ፋርስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እስራኤልን እየገዛ ነበር፡፡ የፋርስ መንግሥት ከወደቀ በሁዋላ የግሪክ መንግሥት ተከተለ፡፡ ከግሪክ መንግሥት በስተጀርባ የግሪክ አለቃ የሚባል ሌላ ሰይጣናዊ መልአክ ነበር፡፡

ይህ የሚያሳየን የምድር መንግሥታት አቻ ሰይጣናዊ መንግሥት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ገዢዎቹንና መንግሥታቱን የፈቃዱ መሣሪያዎች ለማድረግ በራሱ ገዦች በኩል ሰይጣን የምድር መንግሥታትን ይጠቀማል፡፡



ከመንግሥተ ሰማይ ተጽእኖ ሥር ለማድረግ ለመንግሥታት መጸለይ ይኖርብናል፡፡

ከሁሉም በፊት ማለትም - ለበሽተኞች፣ ለሚሲዮናውያን፣ ለወንጌላውያን ሌላው ቀርቶ ለቤተ ሰቦቻችን እንኳ ከመጸለያችን በፊት ለመንግሥታችን መጸለይ እንዳለብን ጳውሎስ የሚናገረው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው የአገሩን መንግሥት የሚተች ሰው ጸሎቱ ውጤት አለማስገኘቱን ለዓለም እየተናገረ ነው፡፡ ተግባሩን አልፈጸመም፡፡ ያ እኛን ብቻ ሳይሆን መላው የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ ሁነኛ ውሳኔዎች የሚደረጉበት ሕንፃ ላይ እንዲያንዣብቡ ለእነዚህ ጨለማ መላእክት ፈቅዶላቸዋል፡፡ ያንን የሰይጣን ወረራ በቸልታ ማለፍ የለብንም፡፡

## በሰማያዊ ስፍራ የእኛ ቦታ

ከሰይጣን ጋር በሚደረገው ታላቅ ውጊያ ወሳኙ አንድ ነገር ነው - የሚጸልዩ አማኞች፡፡ ድሉ ፀእግዚአብሔር ወገን ይሆን ዘንድ ሚዛኑን የምናጋድለው እኛ ነን፡፡ ይህ እጅግ አስደናቂ ሐቅ ነው፤ እንደዚያ መሆኑንም ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ አድርገዋል፡፡ ጸሎታችን አላስፈላጊ አይደለም፤ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይም አይደለም፡፡ በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ሁሉ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

የምንጸልይበት መንገድ አጽናፈ ዓለሙ የሚሄድበትን መንገድ ይወስናል፡፡ ይህ ቃል በቃል እውነት እንጂ ማጋነን ነው በማለት አላምንም፡፡ አማኞች ዋጋ እንደሌላቸው ሲናገሩ መስማትን የመሰለ በጣም የሚሳዝነኝ ነገር የለም ‹‹ እኔ የምናገረው ወይም የማደርገው ይህን ያህል ዋጋ የለውም፡፡ ፋይዳ ያለኝ ሰው አይደለሁም›› ይላሉ፡፡ እውነት ነው ፋይዳ ቢስ ናችሁ፡፡ ነጥቡም ይኸው ነው፡፡ በመላው አጽናፈ ዓለም የጥበቡ የጸጋውና የኃይሉ መገለጫ እንድትሆኑ እግዚአብሔር የመረጣችሁ ፋይዳ ቢስ ስለሆናችሁ ነው፡፡

ይህም ማለት ከእንግዲህ ፋይዳ ቢስ አይደላችሁም ማለት ነው፡፡ ከፍተኛ ፋይዳ አላችሁ! መላው አጽናፈ ዓለም በእናንተ ዙሪያ ይሽከረከራል፡፡ ይህን አምናለሁ፡፡ 2ቆሮንቶስ 4፡15 ላይ ጳውሎስ፣ ‹‹ይህ ሁሉ ለእናተ ጥቅም ሆኖአል›› ይላል፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ካለን ግንኙነት የተነሣና በእኛ አማካይነት

እግዚአብሔር ለአጽናፈ ዓለሙ ማድረግ ከወሰነው ነገር የተነሣ ሁሉም ነገር ለእኛ ጥቅም ሆኖአል።

በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ቦታችንን እንድናውቅ ጳውሎስ ይረዳናል። ‹‹በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ›› (ኤፌሶን 1:3)። ‹‹ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሣውና በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው የታየ ነው። ያ ዘመን ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ቢሆን ሊሰየም ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ ነው›› (ኤፌሶን 1:20-21)። ‹‹እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን›› (ኤፌሶን 2:6)።

ኢየሱስ ከሰይጣን እዝ ጣቢያዎች ክልል ሁሉ በላይ እጅግ ከፍ ብሏል። ከዚህም በላይ እኔና እናንተ ከሰይጣንና ከክልሉ ሁሉ በላይ በመንፈስ ከክርስቶስ ጋር እንደ ተቀመጥን በእምነት እንቀበላለን። በአካል እዚህ ታች በምድር ነን፤ ከክርስቶስ ጋር ካለን ግንኙነት የተነሣ በመንፈስ ግን ከእርሱ ጋር ነን። ‹‹አሳቡም በአሁኑ ዘመን በቤተክርስቲያን አማካይነት ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት ይታወቅ ዘንድ ነው›› (ኤፌሶን 3:10)።

ምንኛ ድንቅ አባባል ነው! ቤተክርስቲያን ማለት በክርስቶስ የምናምን እኛ እግዚአብሔር ባለ ብዙ ገጽታ ጥበቡን ለመላው አጽናፈ ዓለም የሚያሳይበት ነን። አያችሁ፣ ምድር መድረክ እንጂ፣ የአጥናፈ ዓለም ማዕከል አይደለችም። የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ እንደ ደመና ብዛት ባላቸው ምስክሮች እንደተከበብን ይናገራል (ዕብራውያን 12:1ይመ)። አይዞአችሁ የሚሉን ሦስተኛው ሰማይ ያሉት ይመለከቱናል። ለሰዎች ለመላእክትና ለመላው ዓለም ማሳያዎች መሆናችንን ጳውሎስ ይናገራል። በደካሞቹ፣ በማንበቃው፣ በተጣልነውና ችላ በተባልነው እግዚአብሔር የጸጋውን ባለ ጠግነት፣ ክብሩንና ጥበቡን ሁሉ በእኛ ውስጥ ያሳያል። ለምን እግዚአብሔር እንደ መረጠን ታውቃላችሁ? በእኛ ውስጥ ክብሩን መውሰድ የሚገባው ምንም ነገር ባለ መኖሩ ነው። ክብሩን ሁሉ እግዚአብሔር መውሰድ ይገባዋል። ‹‹እግዚአብሔር



የተከበረውን እንደሌለ ለማድረግ፣ በዚህ ዓለም ዝቅ ያለውንና የተናቀውን ነገር፣ ቦታም ያልተሰጠውን ነገር መረጠ›› (1ቆሮንቶስ 1:28)።

### መንፈሳዊ መሣሪያችን

መንፈሳዊ በሆነ ጠላት ላይ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ እየተሳተፍን ከሆነ መንፈሳዊ መሣሪያዎች እንደሚያስፈልጉን ግልጽ ነው። መንፈሳዊ ለሆነ ውጊያ ሥጋዊ መሣሪያ ጥቅም የለውም። አጋንንትና አመፀኛ መላእክትን በታንክ ማስወገድ አይቻልም።

ጳውሎስም ያለው ይህንኑ ነው፤ የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም፣ የምንዋጋው በዚህ ዓለም አይደለም። ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኃይል ያለው ነው›› (2 ቆሮንቶስ 10:3-4)።

የማንን ምሽግ? የሰይጣንን ምሽግ ያለው የት ነው? ምናልባትም በዚህ ጊዜ የአገራችሁ መንግሥት ዋና ጽሕፈት ቤቶች ውስጥ ይሆናል። ምናልባትም የሰይጣን ምሽጎች የሆኑ ወንዶችና ሴቶች በከፍተኛ አስተዳደር ቢሮዎች ውስጥ ይኖሩ ይሆናል። እነርሱን ማፍረስ የማን ሥራ ነው? የእኛ መሣሪያዎችም ተሰጥተውናል። የውጊያ መሣሪያችን፣ ‹‹በእግዚአብሔር እውቀት ላይ በትእቢት የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ ያፈርሳል›› (ቁጥር5)።

የእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣ ታላቅ ነገር በሰማያዊ ስፍራ ያለ የሰይጣን መንግሥት ነው። የሰይጣንን መንግሥት ለማፍረስ መሣሪያ ተሰጥቶናል፤ ያንን ማድረግ ያለብንም እኛው ነን። ምንም እንኳ መላእክት የራሳቸው መሣሪያ እንዳላቸው ጥርጥር ባይኖርም መሣሪያዎቹ የተቀመጡት በእኛ እንጂ፣ በመላእክት እጅ አይደለም።

እግዚአብሔር ሦስት ዋና ዋና መንፈሳዊ መሣሪያዎች ሰጥቶናል፤ የእግዚአብሔር ቃል፣ የኢየሱስ ስምና የኢየሱስ ደም። እነዚህን መሣሪያዎች ጥቅም ላይ የምናውለው በጸሎት፣ በምስጋና፣ በስብከትና በምስክርነት ነው።

እስቲ እነዚህን በአጭሩ እንመልት፡፡ (በሚቀጥለው ምዕራፍ የኢየሱስ ደም የተጨማሪ ጥናታችን ርዕስ ጉዳይ ይሆናል፡፡)

## የእግዚአብሔር ቃል

ኤፌሶን 6፡14-17 ላይ ጳውሎስ ለመንፈሳዊ ውጊያ ለክርስቲያኑ ስለሚያስፈልጉት መንፈሳዊ መሣሪያዎች ዘርዝሯል፡፡ የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የውጊያ መሣሪያዎች ለመከላከያነት የሚውሉ ናቸው፤ እነርሱም ወገባችንን በእውነት ዝናር መታጠቅ፣ የጽድቅን ጥሩር መልበስ፣ በሰላም ወንጌል እግሮቻችንን መጫማት፣ የእምነት ጋሻና የመዳን ራስ ቁር ናቸው፡፡ እነዚህ አማኙን ይከልሉታል፡፡ የመንፈስ ሰይፍ ወደ ተባለው ወደ ስድስተኛው መሣሪያ የእግዚአብሔር ቃል እስክንመጣ ድረስ ምንም ዓይነት የመዋጊያ ወይም የማጥቂያ መሣሪያ አልተጠቀሰም፡፡

እነዚህ ታላላቅ የማጥቂያ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ በእግዚአብሔር ቃል የማትጠቀሙ ከሆነ ራሳችሁን መከላከል ብትችሉ እንኳ ሰይጣንን የምታጠቁበት ነገር አይኖራችሁም፡፡ ሰይጣን እንዲሸሽ ከፈለጋችሁ፣ ከመንገዳችሁ፣ ከቤታችሁ፣ ከቤተሰባችሁ፣ ከሥራችሁ ዘወር እንዲል የምትፈልጉ ከሆነ፣ ተቻችሎ ከመኖር ይልቅ ጨርሶ ልታስወግዱት የምትፈልጉ ከሆነ፣ ልትጠቀሙበት የሚገባ መሣሪያ የመንፈስ ሰይፍ የሆነውን ያእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡

እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቃል ብዙ ጊዜ በአንደበት የሚነገርን ቃል በሚያመለክተው ሬማ በሚለው ተተርጉሞአል፡፡ በሌላ አነጋገር ጠረጴዛ ላይ ወይም መደርደሪያ ላይ ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ውጤታም መሣሪያ አይደለም ማለት ነው፡፡ ቃሉን በአንደበታችን ስንናገረውና በድፍረት ስናውጀው በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ ይሆንልናል፡፡ ይህም ቢሆን የመንፈስ ቅዱስ ሰይፍ መሆኑን ልብ አድርጉ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በአንደበታችን ማነብነብ እንችላለን፤ የተሟላ ውጤት የሚያስገኘው ግን ጥቅም ላይ የሚውለው በመንፈስ ቅዱስ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ የመንፈስ ሰይፍን መጠቀምን በተመለከተ ፍጹም ምሳሌ የሚሆነን በምድረ በዳ በተፈተነ ጊዜ ኢየሱስ ከሰይጣን ጋር ሲጋፈጥ የሆነው



ነው፡፡ ሰይጣን ከፈተና ጋር ሦስቴ ወደ ኢየሱስ መጥቶ ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ጊዜ ኢየሱስ የመለሰው ተጽፎአል በሚል ቃል ነበር (ማቴዎስ 4 ይመ)፡፡ ኢየሱስ ሬማ ማለትም በአንደበት የተነገረ የጌታ ቃል እንጂ ሌላ መሣሪያ አልተጠቀመም፡፡

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ተመሳሳይ መሣሪያ አዘጋጅቷል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በአእምሮአችን ሁለት ነገሮችን መያዝ ይጠቅማል፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ቀደም ሲል በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር (ሉቃስ4፡1 ይመ)፡፡ በቃሉ እንዲጠቀም የመራው ኢየሱስ ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነበር፡፡ ሁለተኛ፣ እንደ ማንኛውም በዘመኑ እንደ ነበር አይሁዳዊ ረጅም የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦችን በቃሉ ይዞ ነበር፡፡ ሰይጣን በገጠመው ጊዜ የጥቅስ ማውጫ ውስጥ መፈለግ ወይም ወደ ቤተ መጻሕፍት መሄድ አላስፈለገውም፡፡ ቀደም ሲል በቃሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዞ ነበር፡፡ ኢየሱስ እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም በእርግጥ እኛም ማድረግ አለብን፡፡

## የኢየሱስ ስም

ሌላው የምንጠቀምበት መሣሪያ የኢየሱስ ስም ነው፡፡ መዝሙር 8 ላይ ያሉ ሁለት ቁጥሮች ለየት ያለ መረዳት ይሰጡናል፡፡

> እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፣ ስምህ በምድር ሁሉ ምንኛ ግርማዊ ነው! ክብርህ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ ብሎአል፡፡ ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ፤ ከጠላትህ የተነሣ፣ ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ፡፡ መዝሙር 8፡1-2

ጠላትንና ባላንጣ የተባለው ሰይጣን ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ እርሱን ጸጥ የምናሰኝበት መሣሪያ ሰጥቶናል፡፡ ምንኛ ደስ የሚል ዜና! ለመሆኑ ያ መሣሪያ ምንድነው? የእግዚአብሔር ስም ነው፤ ‹‹እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፣ ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ ግርማዊ ነው፡፡›› ስሙን የሚጠራው የሰው አፍ ነው፤ ‹‹ከልጆችና ጡት ከሚጠበቡ ሕፃናት አፍ፡፡››

መንፈሳዊ ነገሮች በአፍ በኩልም ይገለጻሉ፡፡ ይህ ለመልካምም ሆነ ለክፉ እውነት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ራእይ 16፡13 ተመልከቱ፡፡ ከዘንዶው አፍ፣ ከአውሬው

አፍ፣ እና ከሐሰተኛው ነቢይ አፍ እንቁራሪት የመሰሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ ዩሐንስ አየ።

ዘማሪው ስለ ልጆችና የሚጠቡ ሕፃናት አፍ የተናገረው ለምንድነው? የግድ ትልልቅ መንፈሳዊ ሰዎች መሆን እንደሌለብን ለማሳየት ነው። በሰማያዊ ስፍራ ያለውን የሰይጣን መንግሥት ከንቱ ለማድረግ እግዚአብሔር ደካሞችን፣ ሞኞችንና የተናቀውን ነገር መርጧል።

ኢየሱስ ይህን መዝሙር 8:2 ላይ ያለውን ቃል መጥቀሱንና ትርጉሙንም መስጠቱንም ከማቴዎስ ወንጌል እናነባለን። ፈሪሳውያንና የቤተ መቅደስ አስተዳዳሪዎች በቤተ መቅደሱ ውስጥ ብዙ ጩኸት በመኖሩ ፍርኃታቸውን ለመናገር ወደ ኢየሱስ መጡ። ሰዎች እየጨፈሩ፣ እያጨበጨቡ፣ ሆሣዕና በማለት እየዘመሩ ስለነበር የሃይማኖት መሪዎቹን ረብሸዋቸዋል። ስለዚህም ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ ‹‹ጩኸቱ አይሰማህምን? እንዲህ ያለ ነገር በቤተ መቅደስ ማድረግ ተገቢ ነውን? እነዚህ ሰዎች ሥርዐት እንዲይዙ ልትነግራቸው አትችልም? አሉት።

በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፣ ‹‹እንዲህ የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ?›› (ማቴዎስ21:16)። በአንድ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መሠረት ዳዊት ብርታት አደራጀህ ነበር ያለው። ኢየሱስ ደግሞ ይህንኑ ቃል ምስጋናን ፈጸምህ በማለት ተረጎመው። ያ ምንድነው የሚነግረን? የተደራጁ የእግዚአብሔር ሕዝብ ብርታት ምስጋናን ፍጹም ማድረግ ነው። እንደሚገባ የእግዚአብሔርን ስም ስታመሰግኑ ዲያብሎስ ጸጥ ይላል።

ዲያብሎስ ለምን ጌታን እንዳታመሰግኑ እንደሚፈልግ ማየት ቻላችሁን? ፍጹም በሆነ ሁኔታ፣ በሙሉ ልባችሁ፣ በኅብረት፣ በአንድ ልብ ውጤታማ በሆነ መንገድ ኢየሱስን ስታመሰግኑ የዲያብሎስን አፍ ይዘጋዋል። በጣም የሚጠላው ነገር ቢኖር የአፍ መከፈትን ነው። በጸሎታችሁና የኢየሱስን ስም በማመስገን እንዳትፈቱ ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ ማለት ሃይማኖታዊ ጫና፣ ማኅበረ ሰባዊ ጫና ያደርጋል፤ ሰውን መፍራትን ያመጣል።



እግዚአብሔር እንደ ቴሌቪዥን እስክሪን በግልጽ የሚታይ መገለጽ ሰጥቶኝ ነበር፤ በምድር ሁሉ ያሉ አማኝ ወገኖች በአንድነት ተሰብስበው፣ በአንድ ልብ ቆመው፣ እጆቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው የኢየሱስን ስም ሲያመሰግኑና ከፍ ከፍ ሲያደርጉ አልፎ አልፎ አይ ነበር። እንደዚያ በሚሆንበት ጊዜ በዚያ ከተማ ወይም በዚያ አገር ያለ መንፈሳዊ የጨለማ ኃይል እንደሚሰበር እግዚአብሔር አሳይቶኛል። የሰይጣን መላእክትና አጋንንቱን ሰርጎ ገብነት ማስወገጃ መንገድ ይህ ነው። ፍጹም በሆነ ምስጋና በከተሞቻችን፣ በቤተክርስቲያኖቻችንና ከቤታችን በላይ ያለው አየር መንጻት ይችላል።

## የኢየሱስ ደም

የኢሱስ ደም ከጸሎት ጋር ስላለው ተያያዥነት ብዙ የምለው አለኝ፤ ይህ የሚቀጥለው ምዕራፍ ርዕሰ ጉዳይ ይሆናል። እዚህ ላይ ግን አንድ ነጥብ ብቻ ማለት እፈልጋለሁ። ራእይ 12:11፣ ‹‹እነርሱም በበጉ ደም በምስክርነታቸውም ቃል፣ ድል ነሡት›› ይላል።

እነርሱ እነማን ናቸው? በምድር ያሉ አማኞች ናቸው? እርሱ ማን ነው? ሰይጣን ነው። አጽንዖት መስጠት የምፈልገው ነገር የመጨረሻው ድል የሚመጣው በእግዚአብሔር መላእክት ሳይሆን በአማኖች መሆኑን ነው። ምንባቡ በሰማይ እየተደረገ ስላለ ውጊያ ይገልፃል። ሚካኤልና መላእክቱ እየተዋጉ ነው፤ ሰይጣንና መላእክቱም እየተዋጉ ነው። ሆኖም፣ በበጉ ደምና በምስክርነታቸው ቃል ድል ነሡት።

ዘወትር ስለ ኢየሱስ ደም በመመስከር ከሰማያዊ ስፍራ ሰይጣንን አስወግዱት። ይህ እጅግ ድንቅ መገለጽ አይደለም? አፋችሁን ለመዘጋት ሰይጣን ለምን ማንኛውንም ነገር እንደሚያደርግ ማየት ቻላችሁ? ማለት ሌላውን ሰው ከማማት ውጪ ግን ኢየሱስን ማመስገን ወይም የእግዚአብሔርን ቃል መናገር ወይም ጌታ ያደረገላችሁን መመስከር ስትፈልጉ ሰይጣን በከንፈሮቻችሁ ፊት መሰናክል ያኖራል። ለምን? ምክንያቱም ምሽጉን እያፈረሳችሁ ስለ ሆነ።

ከብሉይ ኪዳን የኢዮሳፍጥ ታሪክ ስለ መንፈሳዊ ውጊያ አንድ ሌላ ምሳሌ እናገኛለን። በዚህ ውጊያ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ድል አግኝተው ነበር፤ ጠላትም ፍጹም ተሸንፎ ነበር። እነርሱ ማድረግ የነበረባቸው ምርኮ መሰብሰብ ብቻ ነበር፤ ጠላትም ፍጹም ተሸንፎ ነበር። የኢዮሳፍጥን የጦርነት ስልት፣ የተጠቀመበትን መሣሪያና ድል ያገኘበትን መንገድ በአጭሩ ማየት እፈልጋለሁ። እያንዳንዳችው መርሖዎችና እያንዳንዳቸው መሣሪያዎች በትክክል ለዚህ ዘመን እንደሚጠቅም አምናለሁ።

## መንፈሳዊ ድል

ኢዮሳፍጥ የይሁዳ ንጉሥ ነበር። ሕዝቡን በቅርቡ ወደ እግዚአብሔር መመለሱና የሙሴን አምልኮ ሥርዓት፣ ሕጉን፣ ክህነትና ፈራጆቹን ማቋቋም ነበር። በጣም የተዋጣለት ሥራ ሠርቶአል።

ከዚያም ሞአባውያንን፣ አሞናውያንን፣ ኤዶማውያንና በሙት ባሕር በኩል በስተምሥራቅ ለመንግሥቱ ቅርብ የሆኑ ሌሎች ሕዝቦችን ያስተባበረ ግዙፍ ኃይል የወረራ ዛቻ እያደረገበት ነበር። ኢዮሳፍጥ የእርሱ ሕዝብ እጅግ በጣም ጥቂት፣ ጠላት ግን በቁጥርም ይሁን በጦር ኃይል በጣም ብልጫ ያለው በመሆኑ በተፈጥሮአዊ መንገድ ጠላቶቹን መግጠም እንደማይችል ተረዳ። ስለሆነም ኢዮሳፍጥና የይሁዳ ልጆች ውጊያውን ከተፈጥሮአዊው ክልል ወደ መንፈሳዊ ክልል አሻገሩት።

በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጾሙ፤ «ኢዮሳፍጥ እጅግ ስለ ፈራ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወሰነ፤ በይሁዳም ሁሉ ጾም አወጀ» (2ዜና 20:3)።

የእግዚአብሔር ሕዝብ የሕይወት ወይም የሞት የሆነ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል። ከተለመደ ሃይማኖታዊ ሥርዐታቸው ወጣ በማለት ፊታቸውን እግዚአብሔርን ወደ መፈለግ አቀኑ። ይህ የግለሰብ ሳይሆን ወታደራዊ ሽንፈት ከዚያም ባለፈ ዕልቂት የተጋረጠባቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ በአንድነት ያደረጉት ጾም ነበር። የመጨረሻው የእግዚአብሔር ሕዝብ ታላቅ መጠጊያ የኅብረት ጾም መሆኑን አውቀዋል።



ሁለተኛ፣ በአንድነት ተሰበሰቡ፣ «የይሁዳ ሕዝብም የእግዚአብሔርን ርዳታ ይሻ ዘንድ በአንድነት ተሰበሰበ፤ ከይሁዳ ከተሞች ሁሉም እግዚአብሔርን ለመፈለግ መጡ» (ቁጥር4)። በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በገጠማቸው በእያንዳንዱ ዋናዋና ቀውስ ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ ልዩነታቸውን አስወግደው በአንድነት ይመጡ ነበር።

ቀጥሎ ያለው ጸሎት ነበር፤

> ኢዮሳፍጥም በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ፤ ከአዲሱ አደባባይ ፊት ለፊት በይሁዳና በኢየሩሳሌም ጉባኤ መካከል ቆመ፤ እንዲህም አለ - የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ በሰማይ የምትኖር አምላክ አይደለህምን? የምድር ሕዝቦችን መንግሥታት ሁሉ የምትገዛ አንተ ነህ፤ ኃይልና ሥልጣን በእጅህ ነው፤ ሊቋቋምህ የሚችል ማንም የለም። አምላካችን ሆይ፣ የዚህችን ምድር ነዋሪዎች ከሕዝብህ ከእስራኤል ፊት አሳድደህ ያስወጣህና ለወዳጅህ ለአብርሃም ዘሮች ለዘላለም የሰጠሃቸው አንተ አይደለህምን? 2ዜና መዋዕል 20:5-7

ኢዮሳፍጥ አፉ እንዳመጣለት እንዳልጸለየ ልብ አድርጉ። የሚያውቀውን የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ ነበር የጸለየው። ለራሱ ለእግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ቃል ጠቅሷል።

እርሱ አደርጋለሁ ያለውን በድጋሚ ለእግዚአብሔር መናገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጸለይ ጥሩ ምሳሌ ነው። ኢዮሳፍጥ በትክክል ያንን ዓይነት ጸሎት ነበር የጸለየው። በእግዚአብሔር ፊት የሕዝቡን ታሪክ፣ የብሉይ ኪዳን ጽሑፎችን፣ የሙሴን ሕግ፣ መሳፍንቱንና ነቢያቱን አነሣ። ኢዮሳፍጥ እንዲህ አለ፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንና ያንን እንደምታደርግ ቃል ገብተሃል። አሁን አድርገው አደርጋለሁ እንዳልህ አድርግ።

ጸሎቱን እንዳበቃ ወዲያውኑ የትንቢት ቃል መጣ

> በዚህ ጊዜ የአሳፍ ዘር በሆነው በሌዋዊው በዘካርያስ ልጅ በሕዚኤል ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ መጣ። ዘካርያስም

> የበናያስ ልጅ ሲሆን፣ በናያስም የማታንን ልጅ የሆነው የይዔኤል ልጅ ነው። እርሱም እንዲህ አለ፤ «ንጉሥ ኢዮሳፍጥ፣ እናንተም በይሁዳና በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ሁሉ አድምጡ!

የእግዚአብሔር ሕዝብ በሚጾሙበትና በምስጋና በሚመጡበት ጊዜ ሁሉ ምንጊዜም ትንቢታዊ መገለጽ ይኖራል። አጥብቀው እርሱን ከሚፈልጉ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ኅብረት ትንቢታዊ አገልግሎት እንደሚወጣ አምናለሁ። በእግዚአብሔር ፊት ሙሉ በሙሉ እርሱን የሚፈልግ ልብ እንጂ፣ ሌላ ምንም ዓይነት ሰው ሠራሽ ዘዴ አልነበረም።

ይህ ሰው ትንቢትና የጥበብ ቃል ይዞ መጣ። «አትፍሩ። ውጊያው የእግዚአብሔር እንጂ የእናንተ አይደለም። እናንተ መዋጋት አይኖርባችሁም። እናንተ ማድረግ ያለባችሁ በነገው እለት ወደ ሸለቆው መጨረሻ መሄድ ብቻ ነው፤ እግዚአብሔር በጠላቶቻችሁ ላይ ያደረገውን ታያላችሁ» አለ።

ከዚያ አንድ ተጨማሪ መሣሪያ ተጠቀሙ - ምስጋና። «ከቀዓትና ከቆሬ ወገኖች ጥቂት ሌዋውያንም ቆመው እጅግ ከፍ ባለ ድምፅ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብርን አመሰግኑ» (ቁጥር 19)። በማግስቱም ማመስገናቸውን ቀጠሉ፤

> ከሕዝቡም ሁሉ ከተመካከረ በኋላ ከሠራዊቱ ፊት ቀድመው በመሄድ፣ «እግዚአብሔርን አመስግኑ ፍቅሩ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራልና» እያሉ ለእግዚአብሔር የሚዘምሩና ስለ ቅድስናውም ክብር የሚያወድሱ ሰዎችን መደበ። ቁጥር 21

ከሠራዊቱ ፊት ለፊት የሚያመሰግኑና የሚዘምሩ ካህናት ቡድን ነበር። ጥቂት ሳያሸበሽቡ እንዳልቀረም አስባለሁ።



ስለ አይሁዶች የማውቀው ነገር ቢኖር ከማሸብሸብ የተለየ ምስጋናና ዝማሬ ማቅረብ አለመቻላቸውን ነው። «መዘመርና ማመስገን ሲጀምሩ እግዚአብር ድብቅ ጦር አመጣባቸው (በጠላቶች ላይ)» (ቁጥር22)። በምስጋናቸው መሐል እግዚአብሔር በጠላት ላይ የሚያደርገውን አደረገ። ምንኛ ድንቅ መገለጥ ነው! እናንተ ጌታን ስታገለግሉ፣ እርሱ ደግሞ ችግሮቻችሁን ይፈታል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ይህን ብቻ ማየት ቢችሉ እንዴት ጥሩ ነበር! መሣሪያዎቻችን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ናቸው። በመካከላችን ያለውን የመካከለኛ ሰማይ ጨለማ ስንጥቀን ወደ እግዚአብሔር እንደርሳለን። እንደ ግለሰብም ይሁን እንደ ሕዝብ ያለብን ማንኛውም ችግር እግዚአብሔር ይነካል። እግዚአብሔር በሰጠን መንፈሳዊ መሣሪያዎች ስንጠቀም ለኢዮሳፍጥና ለይሁዳ ልጆች እንደ ነበረው ሁሉ ለእኛ በዚህ ዘመን ላለነውም እግዚአብሔር ታማኝ ይሆንልናል።

በእነርሱ ላይ ለጦርነት የተነሣ ማንኛውም ጠላት ተደመሰሰ። ምርኮውን ለመሰብሰብ ሦስት ቀን አስፈለገ! እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ከኢዮሳፍጥ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤ በዙሪያቸው ባሉ አገሮች ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርሃት ወደቀ። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ምንም ዓይነት ወታደራዊ ወረራ አልገጠማቸውም (ቁጥር 25-30)።

ያ ዛሬም ሊሆን እንደሚችል ታምናላችሁ? አማኞች ያንን ዛሬም በዓለም ዙሪያ ማድረግ እንደሚችሉ ታምናላችሁ? ስለ ታላቅነቱና ስለ ክብሩ እግዚአብሔር መጠነኛ መንፈሳዊ እይታ ይስጠን። የሰማይ ሠራዊት ሁሉ እስኪታሰሩ፣ እስኪታገዱና በመጨረሻም እስኪወድቁ መጸለይ ያስችለን።

# 7

# የእግዚአብሔር አቶሚክ መሣሪያ

## የኢየሱስ ደም

**በሰማይም ጦርነት ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ከዘንዶው ጋር ተዋጉ፤ ዘንዶውና መላእክቱም መልሰው ተዋጓቸው፤ ነገር ግን ድል ተመቱ፤ በሰማይም የነበራቸውን ስፍራ አጡ። ታላቁ ዘንዶ፣ የጥንቱ እባብ ተጣለ፤ እርሱም ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው፣ ዓለምን ሁሉ የሚያስተው ነው፤ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።**

**ራእይ 12፡7-9**

የዩሐንስ ራእይ በሰማይ ስለ ተደረገ ጦርነት ይገልጻል። ሚካኤልና መላእክቱ ዲያብሎስና መላእክቱን ተዋጉ። ዲያብሎስ - የጥንቱ እባብ - አላሸነፈም። ከሰማይ ወደ ምድርተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ። የዩሐንስን ራእይ ለመተርም የተለያዩ መንገዶች መኖራቸውን እረዳለሁ። በበኩሌ



በዚህ ምንባብ የተገለጹ ነገሮች ገና ወደ ፊት የሚፈጸሙ መሆናቸውን አምናለሁ። የዩሐንስ ራእይ አተረጓጎም ያጠናሁት ከታሪካዊነቱ አንጻር ከሚመለከተው ትምህርት ቤት ሲሆን፣ ይህ አመለካከት ክርስትና ከተጀመረ ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ያሉ ታሪካዊ ኩነቶች ስዕላዊና ትእምርታዊ ከሆነ ሁኔታ መካተታቸውን ማሳየት ይሞክራል፤ ሆኖም፣ እኔን ሊያሳምነኝ አልቻለም። እኔ እንደምረዳው ታሪካዊ ሐቆችንና የዩሐንስ ራእይ ሐቆችን በተመለከተ ፍትሐዊነት ይጎድለዋል።

ሰይጣን የሚለው ቃል፣ ቃል በቃል፣ ‹‹ተቃዋሚ›› ማለት መሆኑን አስታውሱ። ባሕርዩ እንደዚያ ስለሆነ ስሙም እንደዚያ ሆኖአል። ሰይጣን ሆን ብሎና ያለማሰለስ ማንኛውንም የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ ምሕረትና በረከት ዓላማ ይቃወማል። የሚቃወመው እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ጭምር ነው። ኢየሱስክርስቶስን ጌታና አዳኝ ካደረግንበት ቅጽበት አንሥቶ ውጊያ ውስጥ ነን። እንግዲህ ይህ የወደፊት ሁኔታዎች መገለጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለይቶ ማወቅ እንደሚፈልግ የካህናት መንግሥት አሁን እንዴት መጸለይ እንዳለብን ማወቅን በተመለከተ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ቀደም ሲል ተናግሬአለሁ፤ አሁን ድጋሚ መናገሬም ጠቃሚ ነው፤ ምድር የአጽናፈ ዓለሙ መድረክ እንጂ፣ ማዕከል አይደለችም። ሐዋርያው ጳውሎስ አጽናፈ ዓለሙ የእግዚአብሔር፣ የሰዎችና የመላእክት መድረክ መሆኑን አመልክቷል። በአሁኑ ጊዜ በማይታየው ክልል ውስጥ ያሉ ሁሉ ይመለከቱናል።

በዚህች ታናሽ ዓለም ታናሽ መድረክ ላይ የአሁኑ ዘመን የመጨረሻ ታላቅ ድራማ እየተሠራ ነው። ድራማውን ወደ ፍጻሜ ከሚያመጡ ኩነቶች አንዱ የሰይጣንና መላእክቱ ከሰማያዊ ቦታ ወደ ምድር መጣል ነው። በሌላ አነጋገር ኤፌሶን 6፡12 አሁንም እውነት ነው። ከሰይጣናዊ ኃይሎች ከአመፅ መንፈሳዊ ኃይሎች ውጊያ ላይ ነን። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ጸሎት ያለውን ቦታ መረዳት እንዲያስችለን ወደዚህ የመጨረሻ ትዕይንት የሚያደርሱ ሁኔታዎችን እስቲ ቀረብ ብለን እንይ።

## የወቅቱ የሰይጣን ተግባር

ራእይ 12 እያንዳንዳችን ማስታወስ ያለብንን በአሁኑ ጊዜ ጠላታችን እያደረገ ስላለው ነገር መጠነኛ እይታ ይሰጠናል፤ «ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት ሲከሳቸው የነበረው፣ የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና» (ቁጥር10)። በአሁኑ ጊዜ ሰይጣን አንድ ከባድ ተግባር አለው፤ ይህን ለማድረግ ሌት ተቀን እየሠራ ነው። ወንድሞች የሚለው አማኞችን ያመለክታል፤ ስለዚህም እኔና እናንተን ሌት ተቀን በእግዚአብሔር ፊት ይከሰናል። በባሕሪያችን፣ በዓላማችንና ዝንባሌያችን ያለ ማንኛውም ጥፋት፣ ማንኛውንም ድካም፣ ማንኛውንም ጉድለት፣ ማንኛውንም ቃልን አለማክበር ለእግዚአብሔር ሪፖርት ያደርጋል።

ከመውደቁ በፊት ሰይጣን ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው መልአክ እንደ ነበር ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ያመለክታሉ። በጣም የተለመደው የቅዱሳት መጻሕፍት መጠሪያው፣ ሉሲፈር ማለትም፣ «ብርሃን ያዥ» ነው። በዚያ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት በነበረው ጊዜ የእርሱ ተግባር ከዚህኛው የአጽናፈ ዓለሙ ክልል ለእግዚአብሔር ሪፖርት ማቅረብ ነበር። አመፀኛ ሆኖ ከወደቀ በኋላ እኔ እንደማውቃቸው ብዙ አመፀኞች ምንም ያልተፈጠረ ይመስል በዚያው መቀጠል ሞከሩ። ስለሆነም እጅግ ፍቅር የሌለባቸው፣ ነቃፊ፣ መራራና አሽዋፊ ሪፖርቶቹን ያቀርባል። ዓላማችንና ጸባያችንን መሠረት በማድረግ ስለ እኛ የሚሰጠው ገለጻ እስከ መጨረሻ ቅዳጅ የሚበጣጥቅ ነው።

የሰዎችን በደል መያዝን በተመለከተ የእኛ እገዛ አያስፈልገውም። የእግዚአብሔር ልጆች ነቃፊ መሆን የለብንም፤ ምክንያቱም ያለ እኛ እገዛ ሰይጣን ያንን በበለጠ ሁኔታ ያደርገዋል። ከሁሉም በላይ፣ በፍጹም የራሳችሁ ነቃፊዎችም አትሁኑ። ራሳችሁን የምትኮንኑ ከሆነ እናንተን በተመለከተ የዲያብሎስን ሥራ እየሠራችሁለት ነው። በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ከሆናችሁ ራሳችሁን ስትነቅፉ የእግዚአብሄርን እጅ ሥራ እየነቀፋችሁ ነው። ያ የእናንተ ሥራ አይደለም። አታድርጉት!



## በክርስቶስ መልሳችን

በክፉ ላይ የምንደርገው ውጊያ አንድ ነገርን ማዕከል ያደረገ ነው - ጽድቅን። ከኢየሱስ ጽድቅ የተነሣ ሰይጣን በሰማይ እኛ ላይ ምንም ነገር እንዳይኖረው እግዚአብሔር አድርጓል። «እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኃጢአት የሌለበትን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ቆሮንቶስ 5:21)።

የየትኛውም ቤተ ክርስቲያን አባሎች ብትሆኑ ለሰይጣን ደንታው አይደለም። የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ ስታመጡበት ግን ጸጥ ይላል ምንም የሚናገረው አይኖረውም። እናንተን በተመለከተ የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ ተግባራዊ በምታደርጉበት ደረጃ መጠን የመንፈሳዊ ዕድገታችሁን መጠን መለካት ትችላላችሁ። ይህ እንደ እግዚአብሔር ልጆች መማር የሚገባን ታላቅ ትምህርት ነው። ከእኛ ማንነት ሳይሆን ከኢየሱስ ምንነት የተነሣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አግኝተናል። ብዙ ጊዜ፣ «ከሁሉ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅን እሹ» በሌላ አነጋገር የእናንተን ጽድቅ ሳይሆን በማለት ማቴዎስ 6:33 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን በትክክል አንረዳውም። ሮሜ 10:3 ላይ የአይሁድ ሕዝብ የራሳቸውን ጽድቅ መመሥረት እንደ ሞከሩ ጳውሎስ ጽፏል። በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ጻድቅ አላስገዙም።

ከሁሉም ነገር በፊት የአሮጌ እኔነታችንን ጽድቅ ከንቱ ስለሚያደርግብን የክርስቶስን ጽድቅ መቀበል ዝቅ ማለትን ይጠይቃል። «የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው» (ኢሳይያስ 64:6)። በእግዚአብሔር ፊት እንደ መርገም ጨርቅ የሆነው ኃጢአታችን ሳይሆን ጽድቃችን መሆኑን አስተውሉ። በቤተክርስቲያን አባልነት፣ መልካም ሥራችንን፣ በመንፈሳዊነታችንን መርገም ጨርቅ የምንታመን ከሆነ ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት ይበጫጭቀናል። በሌላ በምንም ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ደምና በእርሱ ጽድቅ ብቻ የምንታመንበት ቦታ ላይ ስንመጣ ግን ሰይጣን ምንም ጣቱን የሚጠቁምበትና እኛን የሚከስበት ነገር በውስጣችን አያገኝም።

## ሰይጣን እንዴት እንደ ተሸነፈ

አንድ ደረጃ ላይ ሰይጣን ከአማይ ይጣላል። ሰማይ ይነጻል።

> ስለዚህ ሰማያት ሆይ፣ በውስጣቸውም የምትኖሩ ሆይ፣ ደስ ይበላችሁ፣ ምድርና ባሕር ግን ወዮላችሁ! ምክንያቱም ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን ብቻ እንደ ቀረው ስላወቀ፣ በታላቅ ቁጣ ተሞልቶ ወደ እናንተ ወርዶአል። ዘንዶው ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት። ራእይ 12:12-13

ሰማይ ደስ ይበልህ - ምድር ግን ተጠንቀቂ!

ዲያብሎስ ወደ ምድር በሚጣልበት ጊዜ የቀረው ጥቂት ዓመት ብቻ መሆኑን አውቆ ነው የሚመጣው እየተነጋገርን ያለነው ስለ አንድ በውል ተለይቶ ስለሚታወቅ ጊዜ ነው። ስለ ትንቢቶቹ የሚረዳ ዲያብሎስ ይህን በሚገባ ያውቃል። ወደ ታች ወደዚህ ሲመጣ፣ ያለው፣ «ዘመን፣ ዘመናትና የዘመን እኩሌታ እንደ ሆነ ያውቃል (ራእይ 12:14)። ይህ ሶስት ዓመት ተኩል እንደ ሆነ አጠቃላይ ስምምነት ላይ ተደርሷል። ኢየሱስም እነዚያ ቀኖች አጭር እንደሚሆኑ ተናግሮአል (ማቴዎስ 24:22)። ከዚያም ሰይጣን ይያዝና ጥልቁ ውስጥ ይታሰራል።

እንግዲህ፣ ይህን በአእምሮአችን ከያዝን ሰይጣን የሚጣልበት የመጨረሻ የሰይጣንን ውድቀት ማፋጠን ስለ ሆነው የጸሎት አገልግሎታችን ብዙ እንማራለን ማለት ነው።

> ከዚህ በኋላ ታላቅ ድምጽ በሰማይ እንዲህ ሲል ሰማሁ፣ አሁን የአምላካችን ማዳን፣ ኃይልና መንግሥት፣ የእርሱ የክርስቶስ ሥልጣንም መጥቶአል። ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት ሲከሳቸው የነበረው፣ የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። እነርሱም በበጉ ደም፣ በምስክርነታቸውም ቃል ድል ነሡት፤



> እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱለትም። ራእይ 12:10-11

ከዳንኤል ልምምድ እንደ ተመለከትነው መላእክትም የራሳቸው ድርሻ ይኖራቸዋል፣ መጨረሻ ላይ ግን ሰይጣንን በሰማያት ካለው ስፍራ የሚጥሉት በምድር ያሉ አማኖች ናቸው።

ራእይ 12:11 አማኞች ሰይጣንን እንዳሸነፉ ብቻ ሳይሆን እንዴት እንዳሸነፉትም ይነግረናል። እስቲ ሁኔታውን በግልጽ የሚያሳየውን ይህን ጥቅስ ተመልከቱ፤ «እነርሱም (በምድር ያሉ አማኖች) በበጉ ደም፣ በምስክርነታቸውም ቃል (ሰይጣንን) ድል ነሡት፤ እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱም።»

እነዚህ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ሰዎች ናቸው። መኖራቸው ወይም መሞታቸው ለእነርሱ ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም። ለእነርሱ አስፈላጊው ነገር ሰይጣንን ለመጣል ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ተግባር ፈጽመው መገኘታቸው ነው። ይህን የሚያደርጉት ደግሞ ፣ በእግዚአብሔር «አውቶሚክ መሣሪያ» ማለትም በበጉ ደምና በምስክርነታቸው በመጠቀም ነው።

ምናልባትም፣ «በደሙ መጠቀም» ተብሎ ሲነገር ብዙ ጊዜ ሰምታችሁ ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ በበጉ ደምና በምስክርነታችን ቃል ሲባል ምን ማለት እንደ ሆነ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በጥንቃቄና ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ያሰቡበት አይመስለኝም። በአጭሩ እንዲህ ማለት ነው፤ የኢየሱስ ደም ስላደረገላችሁ የእግዚብሔር ቃል የሚናገረውን በግላችሁ ትመሰክራላችሁ ማለት ነው።

ቁልፉ ቃሉቹ፣ ምስክርነት፣ ቃልና ደም የተሰኙት ናቸው። የክርስቶስ ደም ስላደረገላችሁ ነገር ቃሉ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን በግላችሁ ትመሰክራላችሁ። ጉዳዩ ውጤት ይኖረው ዘንድ የግል ታደርጉታላችሁ። የምትመሰክሩት ለማን ነው? ለሰይጣን። ይህ የአማኞች የምስክርነት ጊዜ አይደለም። ይህ እኔና እናንተ ከነፍሳችን ጠላት ጋር ፊት ለፊት የምንጋፈጥበት ጊዜ ነው። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና ሥልጣን በቀጥታ ለእርሱ እንናገራለን፤ የኢየሱስ ደም ስላደረገልን ነገር ቃሉ የሚለውን እንነግረዋለን።

## ደሙን በተመለከተ

ቀጥሎ ባለው ክፍል ደሙን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን እንመለከታለን። የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ለማድረግ ቃሉ ምን እንደሚል ማወቅ እንዳለብን ግልጽ ነው። እንዲያውም፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ባለማወቅ ከዳኑ የኋላ ኋላ በሰይጣን ይጠቃሉ። ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው፣ «የመንፈስ ሰይፍ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል» መጠቀም የእኔና የእናንተ ኃላፊነት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። (ኤፌሶን 6፡17)።

ወደዚያ ከመሄዳችን በፊት ድነት ለማግኘት ደምን ተግባራዊ ስለማድረግ በብሉይ ኪዳን የሚያቀርበውን ግሩም ገለጻ መጥቀስ እፈልጋሁ። ዘጸአት 12 ስለ ፋሲካ የሚናገር ምዕራፍ ነው። ፋሲካ እስራኤልን በግብፅ ከነበረው ባርነት፣ ጨለማና ችግር ለማውጣት እግዚአብሔር ያዘጋጀው መንገድ መሆኑን ታስታውሳላችሁ።

ከባርነት፣ ከጨለማና ከሰይጣንና ከኃጢአት ባርነት የዳንንበት መንገድ እንደ ሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በግልጽ ተናግሯል።

የእስራኤል ከግብፅ መዳን የፋሲካውን በግ ማዕከል ያደረገ ነው። በመጀመሪያው ወር አሥረኛ ቀን እያንዳንዱ ቤተሰብ የራሱን በግ ይመርጣል። በአሥራ አራተኛው ቀን ምሽት እነዚያን በጎች ያርዱአቸዋል። በመጨረሻም መዳን የሚመጣው በእያንዳንዱ በግብፅ ባለ እስራኤላዊ ቤተሰብ በር ላይ ደሙ ሲረጭ ብቻ ነው። በሩ ላይ ደሙን ሲያይ፣ «እንደሚያልፍ» እግዚአብሔር ተናግሯል፤ አጥፊው ወደ ውስጥ እንዲገባ አይፈቅድለትም። በጉ ከታረደ በኋላ አንዲት ጠብታ እንኳ ሳትቀር ደሙ በጥንቃቄ በሳህን ይጠራቀማል። ሆኖም በሳህኑ የተጠራቀመው ደም ማንንም አያድንም። እስራኤል በሳህን ያለውን ደም በዚያው በነበረበት ቢተውት፣ አንድ እስራኤላዊ እንኳ አያመልጥም ነበር። በሳህኑ የነበረውን ደም በሩ ላይ ማድረግ ነበረባቸው።

ያንን የሚያደርጉበት አንድ የተፈቀደ መንገድ ብቻ እግዚአብሔር ሰጥቷቸው ነበር።



በመካከለኛው ምሥራቅ በብዛት የሚበቅል ሂሶጵ የተሰኘ ተክል ጭብጥ ደሙ ውስጥ ይነክራሉ። ደሙ ውስጥ በተከነረው ሂሶጵ የቤታቸውን መቃንና ጉበን ይመቱዋቸዋል። ምንም እንኳ ሂሶጵ ደካማ ነገር ቢሆንም አጠቃላይ የመዳንን ዕቅድ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ እጅግ አስፈላጊ ነበር።

በተጨማሪም ደሙ የሚረጨው መቃንና ጉበኑ ላይ እንጂ ደፉ ላይ እንዳልነበር ማስተዋል ያሻል። ደሙ እጅግ ቅዱስ በመሆኑ በእግራችን የምንረግጠው መሆን የለበትም። የዕብራውያን መልእክት የኢየሱስን ደም ስለሚረግጡ ሰዎች ይናገራል። መልእክቱ ደሙን ለተሳሳተ ዓላማ ማዋልንና መጠቀም በማይገባ መልኩ መጠቀምን ያመለክታል(ዕብራውያን 10፡29ይመ)።

ደሙ ተግባራዊ ይደረግ ስለ ነበረበት ሁኔታ የሚያወሳው የብሉይ ኪዳን ታሪክ በክርስቶስ ያገኘነውን ድነት አመልካች ምሳሌ ነበር። ጳውሉስ፣ «የፋሲካ በጋችን የሆነው ክርስቶስ ተሠውቶአልና» ብሏል (1 ቆሮንቲስ 5፡7)። እርሱ ተገደለ፤ ደሙ ፈሰሰ። በምሳሌው መሠረት ከተመለከትን አሁን ደሙ ያለው ሳህን ውስጥ ነው። ይሁን እንጂ፣ ሳህን ውስጥ ያለ ደም ምንም ሊያደርግልን አይችልም። ሳህን ላይ ያለውን ደም፣ መንፈሳዊ፣ አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ገንዘብና ሥራን ለሚመለከቱ ግላዊ ነገሮቻችን ተግባራዊ አድርገነዋል። የምንጸልየው ምንም ይሁን ምን በሳህን ያለውን የክርስቶስ ደም ወስደን እርሱ ላይ ተግባራዊ እናደርገዋን። ያንን የምናደርግበት መንገድ እግዚአብሔር አዘጋጅቶልናል።

ያ መንገድ በጭብጥ ሂሶጵ መጠቀም አይደለም። ሳህን ላይ ያለውን ደም ወስደን በሕይወታችንና በግል ችግሮቻችን በር ላይ የምናደርገው በምስክርነት ቃላችን ነው። ክርስቶስ ተሠውቶአል፤ ደሙ ፈስሶአል። ከአጥቂ ከለላ ይሆነናል። እንግዲህ የኢየሱስ ደም ስላደረገልኝ ነገር የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን ስመሰክር ደሙ ውስጥ ሂሶጵ እንደ መንከርና እኔ ላይ የመርጨት ያህል ይሆናል ማለት ነው። በዚያ ጊዜ ሙሉ ጥበቃና እኔ ራሴ ላይ፣ ሁኔታዎቼ ላይ፣ አካሌ፣ ቤቴ፣ ሕይወቴ፣ እንዲሁም በምጸልይበት ነገር ሁሉ ላይ የኢየሱስን ደም የመጠቀም መብት ይኖረኛል ማለት ነው። ደሙን ተግባራዊ በማድረግ ዲያብሎስ እኛን ማስጨነቅ፣ መጉዳትና ቤተሰባችንን የመውረር ዕድል እናሳጣዋለን። ደሙን አልፎ መግባት አይችልም።

## የምስክርነታችን ቃል

እስቲ፣ የኢየሱስ ደም ስላደረገልን የእግዚአብሔር ቃል የሚናገራቸውን አንዳንድ ነገሮችን እንመልከት፡፡ በተከታታይ የተወሰኑ ቃሎችን እናይና በግል ምስክርነታችሁ አማካይነት እንዴት በጸሎት ተግባራዊ እንደምታደርጉ አሳያችኋለሁ፡፡

ምናልባትም እነዚህን ጥቅሶች በቃላችሁ መያዝ ትፈልጉ ይሆናል፡፡ በበኩሌ የቱንም ያህል ድንግዝግዝ ውስጥ ብሆን እነዚህን ጥቅሶች ያለ ምንም ችግር መጥቀስ እችላለሁ፡፡ በእነዚህ ጥቅሶች እኖራለሁ፤ የምጠቀምበት ሂሶጵ ሁሌም ዝግጁ ነው፡፡ እነዚህ ጥቅሶችን ሳልጠቀም ያሳለፍኩት ቀን በጣም ጥቂት ነው፡፡

## በክርስቶስ ይቅር መባላችን

ኤፌሶን 1፡7 በክርስቶስ በመሆን ስለምናገኛቸው ሁለት ነገሮች ይነግረናል፤ ‹‹በእርሱ(በክርስቶስ) በደሙ በተደረገ ቤዛነት የኃጢአትን ይቅርታን አገኘን፡፡››

ከክርስቶስ ውጭ እስከ ሆንን ድረስ ደሙ ምንም እንደማይጠቅመን አስታውሱ፡፡ በግብፅ ፋሲካ በተደረገ ጊዜ ደሙ ከቤት ውጭ የነበሩትን ከአጥፊው አላዳናቸውም፡፡ በክርስቶስ ውስጥ በመሆናችን ቤዛነትና የኃጢአትን ይቅርታን እንዳገኘን እዚህ እናያለን፡፡

ቤዛነት፣ ‹‹የሚከፈለውን ዋጋ ከፍሎ እንደገና ማምጣት›› ማለት ነው፡፡ ቤዛነት ያገኘነው ከምን እንደ ነበር የሚነግረን እስቲ አንድ ሌላ ጥቅስ እንመልከት፡፡ ‹‹እግዚአብሔር የተቤዣቸው፣ ከጠላቱ እጅ የታደጋቸው ይህን ይበሉ›› (መዝሙር 107፡2)፡፡ በነገራችን ላይ የምስክርነትን ጥቅም ከሚያስተምሩን ብርቱ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃሎች አንዱ ነው፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ያዳናቸው ይህን ይበሉ›› ማለት በሂሶጵ ይጠቀሙበት የማለት ያህል ነው፡፡

መቤዠታችንን በተመለከተ በዲያብሎስ እጅ ነበርን - ያንን ታውቃላችሁ? በበኩሌ በአንድ ወቅት በዲያብሎስ እጅ እንደነበርኩ የማወቅ ችግር የለብኝም፤ አሁን ግን ከዚያ ስለ ተዋጀሁ ከእንግዲህ



በዲያብሎስ እጅ አይደለሁም፡፡ ሆኖም፣ በኢየሱስ ደም ያለውን ቤዛነት ውጤት እንድለማመድ ከፈለግሁ ያንን ማለት ይኖርብኛል፡፡

ስለሆነም ኤፌሶን 1፡7 መሠረት ያደረገ ምስክርነቴ ይህን ይመስላል፤ በኢየሱስ ደም ከዲያብሎስ እጅ ድኛለሁ፡፡

ይኸው ጥቅስ ኃጢአቴ ሁሉ ይቅር እንደ ተባለም ይነግረኛል፤ ስለሆነም ቀጣዩ ምስክርነቴ፤ በኢየሱስ ደም ኃጢአቴ በሙሉ ይቅር ተብሏል የሚል ይሆናል ማለት ነው፡፡

## መስፈርት ማሟላት

ቀጥሎ 1ኛዮሐንስ 1፡7፣ ‹‹ነገር ግን እርሱ(ክርስቶስ) በብርሃን እንዳለ፣ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በርሳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል››፡፡

እዚህ ላይ ያሉ ግሦች ጉዳዩ ገና ያላበቃ መሆኑን የሚያመለክቱ ቀጣይ ጊዜዎች ናቸው፡፡ ቀጣይ በሆነ ሁኔታ በብርሃን ብንመላለስ፣ ያልተቋረጠ ኅብረት ይኖረናል፤ ደሙም ያለ ማቋረጥ ያነጻናል፡፡ የኢየሱስ ደም ማንጻት የዘወትር እንጂ የአንድ ጊዜ ልምምድ አይደለም፡፡

እንግዲህ መስፈርቱን ካሟላሁ - በብርሃን ከተመላለስሁ፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ካለኝ - ምስክርነቴ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ዘወትር ያነጻኛል የሚል አይነት ይሆናል ማለት ነው፡፡

## ጻድቅ መደረግ

ሮሜ 5፡9፣ ‹‹በኢየሱስ ደም ጸድቃችኋል›› በማለት ይነግረናል፡፡ እዚህ ላይ ጽድቅ የሚለው ቃል የተተረጎመው justified ከሚወከለው የእንግሊዝኛ ቃል ሲሆን፣ Just እና righteous በዕብራይስጥም ይሁን በግሪክ፣ በብሉይ ኪዳንም ይሁን በአዲስ ኪዳን በመተካት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

ጻድቅ መደረግ ምን ማለት ነው? በጣም የማዘወትረው ገለጻ፣ ጻድቅ መደረግ፣ ምንም ኃጢአት እንዳላደረገ መቆጠር የሚለውን ነው፡፡

እንግዲህ በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ እንድንጸድቅ ሲደረግ፣ ምንም ኃጢአት እንዳላደረግሁ ተቆጥሬአለሁ ማለት ነው።

ቀጥሎ ያለው ምስክርነታችን ይህ ነው - በኢየሱስ ደም ጸድቄያለሁ፣ ምንም ኃጢአት እንዳልሠራ ተቆጥሬአለሁ።

## መለየት

ዕብራውያን 13፡12 በኢየሱስ ደም እንደ ተቀደስን ይነግረናል፤ ‹‹ኢየሱስ በራሱ ደም አማካኝነት ሕዝቡን ሊቀድስ ከከተማው በር ውጭ መከራን ተቀበለ።›› መቀደስ የሚለው ቃል መጽደቅ ከሚለው ጋር ይመሳሰላል። መጽደቅ፣ ‹‹ትክክል ወይም ጽድቅ›› ማለት ነው። መቀደስ ደግሞ፤ ‹‹ቅዱስ መደረግ›› ማለት ነው። ቅዱስ የተደረገ ሰው ለእግዚአብሔር ተለይቷል። በሌላ አነጋገር ለእግዚአብሔር የተለየሁ ከሆንኩ በዲያብሎስ ክልል ወይም ግዛት ውስጥ አይደለሁም። በኢየሱስ ደም ከዲያብሎስ ተለይቻለሁ።

በግብፅ ሕዝብና በእስራኤል ሕዝብ ደም ከዲያብሎስ መዋጀትን የተመለከተ ልዩነት እንደሚያደርግ እግዚአብሔር ለፈርዖን ነግሮት ነበር። መዋጀትን የተመለከተ ልዩነት በመኖሩ ምንም እንኳ እዚያ ቢሆኑም ግብፅ ላይ የወረደ መቅሠፍት እስራኤልን አይነካም። በእኛ ሕይወት ይህን ልዩነት የሚያመጣ የኢየሱስ ደም ነው።

አመፀኛው ላይ የሚወርድ ፍርድ ጻድቁን እንዲያጠፋ በፍጹም የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ስለሆነም፣ በኢየሱስ ደም ለእግዚአብሔር ከተለየሁ፣ አመፀኛው ላይ የሚወርድ የእግዚአብሔር ፍርድ እኔን አይነካኝም ማለት ነው። ምክንያቱም ፍርዱ በሚወርድበት ክልል ውስጥ አይደለሁም።

ቀጣዩ ምስክርነታን ይህ ነው። በኢየሱስ ደም አማካኝነት ተቀድሻለሁ፣ ቅዱስ ሆኛለሁ፤ ለእግዚአብሔር ተለይቻለሁ።

## በዋጋ መገዛት

የምስክርነታችን መደምደሚያ የሚገኘው 1ኛቆሮንቶስ 6፡19-20 ላይ ነው። ይሁን እንጂ፣ ከዚያ በፊት ከዚሁ ምዕራፍ ሌሎች ሁለት ጥቅሶች



እንድንመለከት እፈልጋለሁ። የመጀመሪያው ይኸው፣ ‹‹ሰውነት ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤ ጌታም ለሰውነት ነው›› (ቁጥር13)። ከዚያም፣ ‹‹ሰውነታችሁ የክርስቶስ የአካሉ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? የሚል እናነባለን (ቁጥር15)።

ሰውነታችሁ የጌታ ነው፤ ጌታም የሰውነታችሁ ነው። እንግዲህ በርኩሰት ወይም በአመጽ፣ በሆዳምነት፣ በስካር፣ በኒኮቲን ወይም ዘግናኝ የሆኑ ሰይጣናዊ ፊልሞችን እና፣ ሌሎችን በሚያጠፉ ሌሎች ክፉ ነገሮች ሰውነታችሁን ካላዋላችሁት፣ ሰውነታችሁን ለጌታ ለይታችሁ ከሆነ፣ ‹‹ሰውነቴ የጌታ ነው፤ ጌታም የሰውነቴ ነው›› ማለት ትችላላችሁ። ሆኖም፣ ሰውነታችሁ የጌታ መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለባችሁ። እዚህ ላይ ያን አመጻኛ ታናሽ የሰውነታንን ብልት ማለትም ምላሳችንንም መጨመር ይኖርብናል።

አሁን ወደ መደምደሚያው መጥተናል -

> ለመሆኑ ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ነው። እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም፤ በዋጋ ተገዝታችኋል፤ ስለዚህም በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ። 1ቆሮንቶስ 6፡19-20

ጌታ ለራሱ ይፈልጋችኋል፤ ክቡር ደሙን የሚያህል ዋጋ ከፍሎባችኋል። ሕይወታችሁን እንደ ፈለጋችሁት ማድረግ ትችላላችሁ፤ እንደዚያ ከሆነ ግን እንዳልተገዛችሁ አስታውሱ። ሁለቱም ሊሆን አይችልም። የእግዚአብሔር ከሆናችሁ የራሳችሁ አይደላችሁም። የራሳችሁ ከሆናችሁ የእግዚአብሔር አይደላችሁም።

ኢየሱስ መስቀል ላይ የሞተ ጊዜ ለሙሉ ድነት የሚሆን ሙሉ ዋጋ ከፍሏል። የዋጀው ሙሉ ሰውነታችሁን እንጂ፣ የተወሰነውን ክፍል ብቻ አይደለም። በደሙ በኩል ቤዛነት አግኝታችሁ ከሆነ፣ እናንተን የእርሱ ለማድረግ ደሙን ከፍሎባችኋልና መንፈሳችሁ፣ ነፍሳችሁ፣ አካላችሁ የእግዚአብሔር ነው።

ይህ ቀጣዩ ምስክርነታችን ነው፤ ሰውነቴ በኢየሱስ ደም የተዋጀ፣ የነጻ፣ የተቀደሰ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው። ስለዚህ ከኢየሱስ ደም የተነሣ ሰይጣን በእኔ ውስጥ ስፍራ የለውም፤ በእኔ ላይ ምንም ኃይል የለውም።

አሁን ጀግም አንድ ብርቱ ምስክርነት በማድረግ እነዚህ ጥቅሶችን በሙሉ በኅብረት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ከግል ልምምዬ እንደ ተመለከትኩት የሰይጣንን ኃይል በማሸነፍ ረገድ ይህ እጅግ ብርቱ መሣሪያ ሆኖኛል። በእምነቴ እነዚህ ምስክርነቶች በእምነት ብታውጇቸው ጠላት ያንን መቋቋም ከቻለ በጣም እገረማለሁ።

በመሠረቱ በቃሉ አማካኝነት ከመንፈስ ቅዱስ ታላላቅ አገልግሎቶች አንዱ ዲያብሉስን ማወክ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቃቸው በፊት በሰላም ይኖሩ እንደነበር ብዙዎች ይነግሩኛል። ሰይጣንን ማሳደድ እንድትችሉ መንፈስ ቅዱስ በግልጽ ስለሚያወጣው እንዲህ መሆኑ አይገርምም።

እንግዲህ ደሙን ለሕይወታችን ተግባራዊ የምናደርግበት ምስክርነታችን እዚህ ቀርቧል። ጥቅሶቹ ከየምስክሮቹ በፊት ተቀምጠዋል።

* ኤፌሶን 1:7 በኢየሱስ ደም አማካኝነት ከዲያብሉስ እጅ ተዋጅቻለሁ።
* ኤፌሶን 1:7 በኢየሱስ ደም አማካኝነት ኃጢአቴ ሁሉ ይቅር ተብሏል።
* 1 ዩሐንስ 1:7 የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ደም ዘወትር ከኃጢአት ያነጻኛል።
* ሮሜ 5:9 በኢየሱስ ደም ጸድቄአለሁ፤ ምንም ኃጢአት እንዳልሠራ ተቆጥሬአለሁ።
* ዕብራውያን 13:12 በኢየሱስ ደም ተቀድሻለሁ፤ ቅዱስ ተደርጌአለሁ፤ ለእግዚአብሔር ተለይቻለሁ።
* 1 ቆሮንቶስ 6:19-20 ሰውነቴ በኢየሱስ ደም የተዋጀ፣ የነጻ፣ የተቀደሰ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው። ስለዚህ በኢየሱስ ደም ሰይጣን እኔ ውስጥ ቦታ የለውም፤ በእኔ ላይ ኃይል የለውም።



በእርግጥ እነዚህን የምታምኑ ከሆነ ቀጥሎ የምታደርጉት ስለዚያ ጌታን ማመስገን ነው። የምትጠቀሙበት የምስጋና ዓይነት እዚህ ላይ ቀርቧል።

> ክቡር ስለሆነው የኢየሱስ ደም እግዚአብሔር ሆይ ተመስገን፡ መዋጀት ስላደረው የክርስቶስ ደም ተመስገን። ስለሚያጸድቅ፣ ስለሚቀድስ ክቡር የበጉ ደም ተመስገን። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን። አንተ የመዋጀቴን ዋጋ ከፍለሃልና ኢየሱስ ሆይ አመሰግንሃለሁ። ክቡር ደምህን መስቀል ላይ አፍስሰሃል። አንተ ከዓለም መፈጠር በፊት የታረደ በግ ነህ። በምስክርነቴ አማካይነት በሳህን ያለውን ደም የግል ችግሮቼ ላይ በሂሶጵ አኖራለሁ።

## ሦስት ምስክሮች

ለዚህ ዓይነቱ ጸሎት በጣም ጠቃሚ ወደ ሆነ አንድ ተጨማሪ የቅዱሳት መጻህፍት ምንባብ ትኩረታችሁን እመራለሁ። ስለ ኢየሱስ ሲናገር ቃሉ እንዲህ ይላል፤

> በዉሃና በደም የመጣው ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ በውሃና በደም እንጂ፣ በውሃ ብቻ አልመጣም። የሚመሰክረውም መንፈስ ነው፤ መንፈስ እውነት ነውና። ስለዚህ ሦስት ምስክሮች አሉት። እነርሱም መንፈሱ ውሃውና ደሙ ናቸው፤ ሦስቱም ይስማማሉ።
>
> 1ዩሐንስ 5:6-8

ይህ ስለ ሦስት ምስክሮች ይናገራል። ዩሐንስ በነበረበት ዘመን ሕጋዊ ስምምነት የሚጸናው በሁለት ምስክሮች ነበር። ሦስተኛ ምስክር ያንን የበለጠ ያጸናዋል። ሦስቱ ምስክሮች ውሃው፣ ደሙና መንፈስ ቅዱስ ናቸው።

ኢየሱስ በውሃና ደም መጣ። እዚህ ላይ ውሃ የቃሉ ማንጻት ነው። ኢየሱስ ለተከተሉት ሰዎች፣ ‹‹ከነገርኋችሁ ቃል የተነሣ እናንተ አሁን ንጹሐን ናችሁ›› ብሏቸዋል (ዩሐንስ 15:3)።

ደሙን ካፈሰሰ በኋላ ሙሽራውን መቀደስና ማንጻት ተጨማሪ ዓላማው ሆነ። ኤፌሶን 5:25-27 ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ

እንዳነጻት ይናገራል። በዚህ መልክ ሙሽራዋን ለእርሱ የምትስማማ አደረገ።

የሚመሰክረው መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የሚመሰክረው እውነት ስለሆነ ነው። ስለሆነም መንፈሱ፣ የቃሉ ውሃና መስቀል ላይ የፈሰሰው ደም በአንድነት ይስማማሉ።

በሕይወታችን ወደዚህ በሦስቱ ምስክሮች መካከል ወዳለው መለኮታዊ ስምምነት ስንመጣ ሰይጣንን እናሸንፋለን። ያስተማርኳችሁ ምስክርነት እውነት ነው፤ ስለ ደሙ በሚመሰክር ቃሉ ይጠቀማል። እውነተኛ ውጤት የሚገኘው መንፈስ ሲመሰክር ነው።

በሌላ አነጋገር በክርስትና ሕይወት ውስጥ እንዲሁ ደንቦች ብቻ የሆኑ ነገሮች የሉም ማለት ነው። ድነት ሰው ሠራሽ ዘዴ አይደለም። ፈውስ ሰው ሠራሽ ዘዴ አይደለም። ከክፉ መናፍስት ነጻ መውጣት ሰው ሠራሽ ዘዴ አይደለም። ከእነዚህ አንዱን እንኳ ወደ ደንብና ሥርዐት ዝቅ ማድረግ የሚሞክር ሰው ዋናውን ነገር ይስታል። ኣላማው ሁሉ ይህ ነው፤ የቃሉን ውሃ ስንጠቀም፣ በምስክርነታን በደሙ ስንጠቀምና መንፈስ ቅዱስ ሲመሰክር ያኔ ሰማይ ይከፈታል።

እኔና እናንተ የምንፈልጋቸው የጸሎት ውጤቶችን ማግኘት ከፈለግን መምጣት ያለብን ወደዚህ ስፍራ ነው። እስቲ ጥቅሶቹ የሌሉባቸው ምስክርነቶችንና መደምደሚያው ላይ ያለ የትእዛዝ ጸሎት እንደ ገና እንመልከት መንፈስ ቅዱስ ይመስክርልን።

በኢየሱስ ደም አማካይነት ከዲያብሎስ እጅ ተዋጅቻለሁ። በኢየሱስ ደም አማካኝነት ኃጢአቴ ሁሉ ይቅር ተብሏል። የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ዘወትር ከኃጢአት ያነጻኛል። በኢየሱስ ደም ጸድቄአለሁ፤ ምንም ኃጢአት እንዳልሠራ ተቆጥሬአለሁ። በኢየሱስ ደም ተቀድሻለሁ፤ ቅዱስ ተደርጌአለሁ፤ ለእግዚአብሔር ተለይቻለሁ። ሰውነቴ በኢየሱስ ደም የተዋጀ፣ የነጻ፣ የተቀደሰ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው። ስለዚህ በኢየሱስ ደም ሰይጣን እኔ ውስጥ ቦታ የለውም፤ እኔ ላይ ኃይል የለውም። እክደዋለሁ፤ ራሴን ከእርሱ እለያለሁ፤ ከእኔ እንዲርቅ በኢየሱስ ስም አዝዘዋለሁ። አሜን።



# 8

## ጾም፤ ለእግዚአብሔር ዓላማ የእኛ ምላሽ

### ቅዱስ ጾምን አውጁ፤ የተቀደሰውን ጉባኤ ጥሩ

### … ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ። ኢዮኤል 1፡14

ከዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ መስጠት እንደሚፈልግ ስንማር ነበር። በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ስንለምን፣ የተለያዩ መስፈርቶችን ስናሟላ ጸሎታችን መልስ ያገኛል።ጠላት እኛን ለማሰናከል እንደሚሞክርም እንረዳለን። መልሱ እስኪመጣ ድረስ ሳንታክት የመጸለይ ኃላፊነት አለብን።

ለምሳሌ ያህል እንድትፈወሱ ፈቃዱ መሆኑን እግዚአብሔር ተናግሮአል። የፈውስ ተስፋ ከሰጣችሁ፣ መቀመጥና፣ ‹‹ሁሉንም ለእግዚአብሔር እተዋለሁ። የእርሱ ፈቃድ ስለሆነ በማንኛውም መንገድ ያደርገዋል›› በማለት እጃችሁን አጣጥፋችሁ መቀመጥ የለባችሁም። ይህ ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር የተጣጣመ አይደለም።

ይልቁንም ተገቢው ምላሽ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ የተስፋ ቃል ሰጥተኸኛል። አመሰግንሃለሁ። ለሰጠኸኝ ተስፋ መፈጸም በፍጹም ልቤ አንተን እፈልጋሁ። ማለት ሊሆን ይገባዋል።

ሕዝቡን በተመለከተ የጸጋ ተስፋ ቃሉን በመፈጸም ላይ እግዚአብሔር እንድንጸልይ የሚፈልገው እንዲህ ዓይነት ጸሎት ነው። ምን የማድረግ እቅድ እንዳለው ቢነግረን እንኳ እርሱን እንድንፈልገው ይፈልጋል። ይህ የግለሰቦች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ሕዝቦችና ዓለምን በተመለከተም ቢሆን እውነት ነው።

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው በተለይ አማኞችን የሚመለከት የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል ይሆናል፤ በመጨረሻዎቹ ቀኖች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን ማድረግ ይፈልጋል? የእኛስ ምላሽ ምን ሊሆን ይገባል? ቅዱሳት መጻሕፍት ለሁለቱም ጥያቄዎች መልስ አላቸው።

**ተገቢ ምላሽ**

በግልጽ የታወቀ የእግዚአብሔር ዓላማን በተመለከተ ምላሻችን ምን መሆን እንዳለበት እንዲረዳን ስለ እስራኤል በተነገረ ትንቢታዊ ቃል እንጀምር። ሕዝቅኤል ውስጥ ያለው ትንቢት የእስራኤል ብሔራዊ መታደስን፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ዓላማ ይመለከታል፡፤ በመሠረቱ በበለስ ዛፍ ለተመሰለችው እስራኤል የተነገሩ አብዛኞቹ ቁሳዊ የመታደስ ነገሮች በወይን የተመሰለችው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መታደስ አርዓያዎችና ምሳሌዎች ናቸው።

የሕዝቅኤል 36 ኋለኛው ክፍል የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ገዛ አገራቸውና ርስታቸው መመለስን አስመልክቶ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ተስፋ ቃል ነው። ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱስ ዘመናዊና ሊታመንበት የሚገባ መጽሐፍ ለመሆኑ ትልቁ ማስረጃ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ አገራቸው መመለሱ ሊሆን ይችላል። የእስራኤል መመለስና፣ መታደስ የሚባል ነገር ባይኖር ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ስለዚሁ እውነት የሚናገር በመሆኑ ምንም ጥቅም እንደሌለው ነገር አውጥተን መጽሐፍ ቅዱሳችንን መጣል ይኖርብን ነበር፡፤

ከቁጥር 24 ጀምረን እስከ 30 ድረስ ብናነብ ስለ ቅዱስ ስሙ ሲል (ቁጥር 22) ለእስራኤል ቤት አንዳንድ ነገሮችን እንደሚያደርግ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከአሥራ ሁለት ጊዜ በላይ እግዚአብሔር መናገሩን እንመለከታለን።

እስቲ የዚህን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ቁጥሮች ብቻ ተመልከቱ።

> ከሕዝብ መካከል አስወጣችኋለሁ፤ ከየአገሩ ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፤ ወደ ገዛ ምድራችሁም መልሼ



> አመጣችኋለሁ። ንጹህ ዉሃ እረጫችኋለሁ፤ እናንተም ንጹህ ትሆናላችሁ፤ ከርኩሰታችሁ ሁሉና ከጣዖቶቻሁ ሁሉ አነጻ ችኋለሁ። ሕዝቅኤል 36፡ 24-25

እዚህ ላይ እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮችን እንደሚያደርግ ይናገራል። አራት ጊዜ ያህል ‹‹እንዲህ አደርጋለሁ›› ይላል፤ ያም ሆኖ ግን በዚህ ታላቅ ትንቢት መዝጊያ ላይ፣ ‹‹ለእስራኤል ቤት ልመና እሺ እላለሁ፤ ይህንም አደርግላቸዋለሁ›› ማለቱንም ተመልከቱ (ቁጥር 37)።

ልመና ለሚለው ቃል ዕብራይስጡ፣ ‹‹ በታላቅ ትጋት እግዚአብሔርን መፈለግ ›› የሚል ትርጉም አለው። ምን እንደሚያደርግ ቀድሞውኑ እግዚአብሔር የተናገረ ቢሆንም፣ ያንን በተመለከተ ሕዝቡ በትጋት እርሱን እንዲፈልጉ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ከዚህ ጥቅስ ከሚጸልዩ ሕዝቡ ጋር እግዚአብሔር ስላለው ግንኙነትና አሠራር መርሕ የሚሆን ሐሳብ አያለሁ፤ አስቀድሞ የተወሰነው የእግዚአብሔር ዓላማ በእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅ መሠረት የሰውን ነጻ ምላሽ ያነቃቃል፡፤

‹‹እናንተን በተመለከተ በዚህ መልኩ ጣልቃ መግባቴን ስታዩ፣ የተስፋ ቃሎቼ እየተፈጸሙ መሆናቸውን ስታዩ፣ ከእናንተ ምላሽ እጠብቃለሁ። ቃል በገባሁት መሠረት ሲፈጸም ያያችሁትን ሙሉ በሙሉ እንድፈጽመው በራሳችሁ ነጻ ፈቃድ በትሕትና ወደ እኔ እንድትመለሱና በትጋት በመጸለይ እንድትፈልጉኝ እጠብቃለሁ›› እያለ ነው።

በሌላ አነጋገር ሕዝቡን በተመለከተ ትንቢቶችንና የቃሉ መገለጦች ለመፈጸም እግዚአብሔር ሉዓላዊ በሆነ ጸጋ መንቀሳቀስ ሲጀምርና እነዚህ ተስፋዎች እየተፈጸሙ መሆናቸውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲያይ፣ ‹‹በጣም አይገርምም! እስቲ እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን ተመልከቱ! በማለት›› በሥራ ፈትነት መቀመጥ የለብንም። ያ ተገቢ ምላሽ አይደለም።

ምላሻችን፣ ‹‹እኛን በተመለከተ እግዚአብሔር እየተንቀሳቀሰ ነው። የተናገረውን መልካም ቃል ይፈጽመው ዘንድ በሙሉ ልባችን እርሱን እንፈልገው›› ማለት መሆን አለበት። ምዕራፍ 6 ላይ እንደ ተመለከትነው ውጊያው የሚያበቃበትና ሽብሸባ የሚኖርበት ጊዜ ይመጣል። ያ ጊዜ ምርኮ የመሰብሰቢያ ጊዜ ነው እስከዚያ ድረስ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቃችን ልዩ ወደ ሆነ መንፈሳዊ ትጋት ሊያነሳሳን ይገባል።

## እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኑ ያለው ዓላማ

እስቲ እንዲህ የሚሉ ጠቃሚ ጥያቄዎች እንጠይቅ ፡ ለእኛም ሆነ ለኢየሱስ ክርስቶስ አካል የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድነው? እግዚአብሔር እንደሚያደርግ የተናገረው ምንድነው? በዚህ ጊዜ ምን እያደረገ ነው? ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች መልስ ይሰጡናል። የመጀመሪያው በመጨረሻዎቹ ቀኖች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን በተመለከተ ሉዓላዊ መገለጽ የሚሰጠን የሐዋርያት ሥራ 2፡17 ነው። ቃሉ እንዲህ ይላል፣ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በመጨረሻው ቀን መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ጎልማሶቻችሁራእይ ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁ ያልማሉ።››

‹‹አብያተ ክርስቲያናት አንድ ከሆኑ›› ወይም ‹‹የነገረ መለኮት ምሑራን ከተስማሙ›› ወይም፣ ‹‹ጳጳሶቹ ከተስማሙ›› ባለማለቱ እግዚአብሔር ይመስገን፤ እንደዚያ ቢል ኖሮ በፍጹም እውን አይሆን ነበር። ይልቁንም እግዚአብሔር፣ ‹‹ምንም ይሁን ምን እኔ አደርገዋለሁ። ይህ ሉዓላዊ ጸጋዬ ነው። ይህ ሕዝቤን በተመለከተ ጣልቃ ለመግባት ቀድሞውኑ የተወሰነ ነው። ሥጋን በለበሰ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ። ጎልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ። ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ። ነው ያለው።

በበዓለ ሃምሳ ቀን ጴጥሮስ ይህን ክፍል በመጥቀስ የተናገረ ጊዜ በመጨረሻው ቀኖች የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሚሰበሰቡ ከሚያመለክተው ኢዮኤል ውስጥ ካለው ትንቢት ጋር አያይዞታል። ረጋ ብለን ኢዮኤል 2፡25 ብንመለከት በዚህ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ አማካይነት እግዚአብሔር



ስለሚያደርገው ነገር የሚገልጽ ቁልፍ የሆነውን ቃል እንደምናገኝ አምናለሁ፤ ‹‹በመካከላችሁ የሰደድሁት ታላቁ ሰራዊት ትልልቁ አንበጣና ትንንሹ አንበጣ፣ ሌሎች አንበጦችና የአንበጣው መንጋ የበላውን፣ እነዚህ ሁሉ የበሏቸውን ዓመታት ዋጋ እመልስላችኋለሁ።

እመልስላችኋለሁ የሚለው ቁልፍ ቃል ብሔራዊ የእስራኤልን መታደስንና መንፈሳዊ የቤተክስቲያን መታስ ያመለክታል። በቅዱሳት መጻሕፍት በተገለጸው መሠረት በዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ዓላማ በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ሕዝቡን መመለስ ነው። የሐዋርያት ሥራ 2፡17፣ ‹‹መንፈሴን እፈሳለሁ›› ሲል፣ ኢዮኤል 2፡25፣ ‹‹እመልስላችኋለሁ›› ይላል።

በዓለም ሁሉ ይህ ሲፈጸም ለአሥርት ዓመታት ተመልክተናል። እንዲህ ያሉ ውጤቶችን ማየት የቻልነው ታላላቅ ሰባኪዎች ወይም ድንቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ስላሉን አይደለም። ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ክብሩን መውሰድ አይችልም። እግዚአብሔር ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ መንፈስን የሚያፈሰው ለቃሉ ታማኝ ከመሆኑ የተነሣ ነው። በመጨረሻ ቀኖች የመንፈስ ቅዱስን መፍሰስ ያለ አንዳች ልዩነት ሰዎች ሁሉ የሚለማመዱት ይሆናል።

እግዚአብሔር ለእስራኤል፣ ‹‹ከአሕዛብ መካከል አወጣችኋለሁ፤ በገዛ ምድራችሁ አኖራችኋለሁ፤ ንጹሕ ውሃ እረጫችኋለሁ፤ ከኃጢአታሁ፣ ከጣዖቶቻችሁና ከርኩሰታችሁ አነጻችኋለሁ›› ብሏል። ቤተክስቲያንን በተመለከተም እግዚአብሔር፣ ‹‹በአብያተ ክርስቲያናት ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ። እጅግ ታላቅ ልዕለ ተፈጥሮአዊ መንብኘት ይኖራል›› እያለ ነው።

ይህ ሲፈጸም እያየን ነው። ስለሆነም ቀጣዩ ጥያቄ፣ ለዚህ ታላቅ የእግዚአብሔር መንቀሳቀስ የእኛስ ምላሽ ምን መሆን አለበት? የሚል ይሆናል።

## በፍጹም ልባችን መመለስ

እንደ ገና ትንቢተ ኢዮኤልን እንመልከት። የዚህ አጭር ትንቢታዊ መጽሐፍ ዝርዝር በጣም ቀላል ነው። ጥፋት፣ መታደስ፣ ፍርድ። ከጥፋት እንዲድኑና ወደ መመለስ እንዲገቡ ከተፈለገ እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚጠብቀው

ይህን ነው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ «ቅዱስ ጾምን አውጁ፤ የተቀደሰውንም ጉባኤ ጥሩ፤ ሽማግሌዎችን ሰብስቡ፤ በምድሪቱ የሚኖሩትን ሁሉ፣ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ጥሩ፤ ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ።(ኢዮኤል 1:14)።

ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ የሚለው ሌላ አማራጭ ያጣ የምልጃ ጸሎትን ያመለክታል። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእግዚአብሔር ቤት ሰብስባችሁ ወደ እግዚአብሔር ጩኹ። በተጨማሪም ጾማችሁን ከጸሎት ጋር አድርጉ። በግል ሳይሆን በኅብረት፣ በአንድነት አድርጉት።

እንደ ገና ኢዮኤል 2:12፣ «አሁንም ቢሆን፣ በጾም፣ በልቅሶና በሐዘን፣ በፍጹም ልባችሁ ወደ እኔ ተመለሱ» ይላል። ከዚያም ከቁጥር 15 ጀምሮ እንዲህ የሚል እናነባለን።

> በጺዮን መለከትን ንፉ፤ ቅዱስ ጾምን አውጁ፤ የተቀደሰውን ጉባኤ ጥሩ። ሕዝቡን ሰብስቡ፤ ጉባኤውን ቀድሱ፤ ሽማግሌዎችን በአንድነት አቅርቡ፤ ሕፃናትን ሰብስቡ፤ ጡት የሚያጠቡትንም አታስቀሩ ...በእግዚአብሔር ፊት የሚያገለግሉ ካህናት፣ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ አደባባይ መካከል ሆነው ያልቅሱ። ቁጥር 15:17

መለከትን ንፉ የሚለው ለሕዝቡ ሁሉ የሚነገር አዋጅ ያመለክታል። ሁሌም የማስጠንቀቂያ ምልክት ነው፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲሰበሰቡ ይጠራል። ሁሉም ከተሰበሰቡ በኋላ፣ የተለየ አጽንዖት የተሰጠው ለመሪዎች መሆኑን ልብ እንበል፤ መሪዎች፣ አገልጋዮችና ካህናት።

በቤተ ክርስቲያን የሚመራ ሰው እንደሚገባ መምራት አለበት። አንድ ጊዜ አንድ መንፈሳዊ መሪ፣«እውነቱን ለመናገር ልመራቸው ከሚገቡኝ ሰዎች ጋር እኩል ለመራመድ መሮጥ አለብኝ» በማለት ነግሮኝ ነበር። መሪዎች ከሆናችሁ፣ መሪዎች ሁኑ በማለት ለመናገር እፈልጋለሁ። መምራት ማለት



«ፊት ለፊት መሄድ ማለት» ነው። ያ ካልሆነ ግን ተመሪዎቹ ከመደበኛው መሪ ቀድመው ይሔዳሉ። ይህ ጥሪ ከእግዚአብሔር ቃል ሲመጣ ርምጃ ለመውሰድና እውነተኛ አመራርን ለማሳየት ካህናት፣ አገልጋዮችና መሪዎች ግዴታ አለባቸው።

ኢዮኤል 2:28፣ «ከዚህም በኋላ፣ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ እፈሳለሁ» በማለት መታደስን በተመለከተ ስለ ተሰጠው ተስፋ ይናገራል። ኢዮኤል ከዚያም በኋላ ያለውን ጴጥሮስ ደግሞ በመጨረሻ ቀኖች ብሏል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንዲረዳው ያደረገ መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ያ ተገቢ ነበር። ሆኖም፣ ጴጥሮስ በመጨረሻ ቀኖች ያለው የኢዮኤልን ከዚያም በኋላ እንደማይሽረው ልነግራችሁ እፈልጋለሁ።

ከዚያም በኋላ የሚለው በድጋሚ እንድናይ ጥሪ የሚያቀርብ ስለዚህ የሚለውን ቃል የመሳሰሉት ዓይነት ነው። ከዚያም በኋላ የሚል ቃል ሲገጥመን፣ «ከምን በኋላ? በማለት መጠየቅ ይኖርብናል፤ እዚህ ላይ መልሱ እግዚአብሔር የነገረንን ካደረግን በኋላ የሚል ነው። እግዚአብሔር አድርጉ ያለን ምን ነበር? ጾምን አውጁ ነበር ያለን። የተቀደሰውን ጉባኤ ጥሩ። በፍጹም ልባችን በለቅሶና በዋይታ ወደ እርሱ እንድንመለስ ጥሪ ያቀርባል። በፍጹም ልባችን በለቅሶና በዋይታ ወደ እርሱ እንድንመለስ ነበር ያደረገን። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሱን እንደሚያፈስ እግዚአብሔር ይናገራል።

እስከ አሁን ያየነው የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ እርሱ አደርጋለሁ ካለው ጋር ሲነጻጸር የጥቂት ጠብታዎች ያህል ነው። ሲንቀሳቀስ አይተነዋል። ይህ ጊዜው እንደ ሆነ እናውቃለን። ከእንግዲህ ምላሽ መስጠት የእኛ እጣ ፋንታ ነው። ፍጹም በሆነ ሁኔታ ይፈጸም ዘንድ አደርጋለሁ ካለው ጋር መንቀሳቀስና መተባበር የእኛ ፈንታ ነው።

የምንቀሳቀሰው ወይም ርምጃ የምንወስደው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ሕዝቡን በአዲስ አጽንዖት ለጾምና ለጸሎት እየጠራ እንደ ሆነ ላመለክታችሁ እፈልጋለሁ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጾምን በተመለከተ በአንዳንድ ቦታዎች አንሥተናል።

ለመንፈሳዊ ክንዋኔ ሆን ብለን ምግብን መተው ማለት እንደ ሆነ እናውቃለን። ጾም እግዚአብሔር ለሚያምኑ ሕዝቡ ያዘጋጀው አጠቃላይ መንገድ አንዱ ነው። የመንፈሳዊ ራስን መግዛት አካል ነው። ጾም ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው የተገለጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ሳይሆን፣ ከተለይ በዚህ የእግዚአብሔር መንፈስ መፍሰስ ዘመን ላለን ለእኛ የእርሱ ፈቃድ ነው።

አሁን ደግሞ ጾም ከመመለስ ወይም ከመታደስ ጋር ያለውን ተያያዥነት እንመልከት

## ሁለት የጾም ዓይነቶች

ጾም ከመመለስ ወይም ከመታደስ ጋር የተለየ ትስስር አለው። ታላቁ የጾም ምዕራፍ ኢሳያስ 58 ሁለት የጾም ዓይነቶች ያቀርባል - አንደኛው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና የእርሱን ክንድ የሚያንቀሳቅስ ነው።

ከቁጥር 3-5 ያለው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስለሌለው ጾም ይናገራል። ለዚህ ምክንያቱ እየጾሙ ያሉ ዝንባሌያቸውና እርስ በርሱ ያላቸው ቅርርብና ግንኙነት ትክክል ባለመሆኑ ነው። ቅሬታ ያለባቸው ነበሩ፤ ያላቸውን የማያካፍሉ ነበሩ፤የሌላውን የሚመኙ፤ እርስ በርስ ወገኞች ነበሩ፤ ስሕተትን የሚከታተሉና በነቃፊነት የተሞሉ ነበሩ። በዚያ ዓይነት ዝንባሌና መንፈስ የምንጾም ከሆነ እርሱ ጸሎታችንን እንዲሰማና መልስ እንዲሰጠን መጠበቅ እንደሌለብን እግዚአብሔር ይናገራል።

ከቁጥር6-12 ያለው እርሱ ስለሚፈልገው የጾም ዓይነት ይዘረዝራል። እያንዳንዱን ቁጥር በጥቂቱም ቢሆን ስናነብ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ካለው ጾም ጋር ተያያዥ የሆኑ ተስፋዎችን ብዛት አስተውሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቁጥር 6 ያህል እጥር ምጥን ባለ ሁኔታ አስደናቂ ተስፋ ቃሎችን የያዘ ክፍል አላውቅም። ‹‹እንግዲህ እኔ የመረጥሁት ጾም፣ የጭቆናን ሰንሰለት እንድትበጥሱ፣ የቀንበርን ገመድ እንድትፈቱ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንድታወጡ፣ ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ አይደለምን?››

የምንጾምበት ዓላማ ትክክል መሆን እንዳለበት ልብ አድርጉ ‹‹የጭቆናን ሰንሰለት›› መበጠስን በተመለከተ በዚህ የነጻ ማውጣት አገልግሎት



ውስጥ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ በዋነኛነትም የእግዚአብሔር አገልጋዮች የጾምና የጸሎትን ዋጋ እስኪከፍሉ ድረስ በፍጹም ነጻ የማይወጡ ሰዎች እንዳሉ እነግራችኋለሁ።

ከዚያም ቁጥር 7፣ ‹‹ምግብህን ለተራቡ እንድታካፍለው፣ ተንከራታቹን ድሃ ወደ ቤትህ እንድታስገባው፣ የተራቆተውን ስታይ እንድታለብሰው፣ የሥጋ ዘመድህንም ፊት እንዳትነሣው አይደለምን?›› ይላል።

ጾም ችግር ውስጥ ላሉት እውነተኛና ተግባራዊ ፍቅር ከማሳየት ጋር መጣመር ይኖርበታል። አንዳንድ ወንጌላውያን አማኞች ወንጌል ባልንጀራን እንደራስ መውደድን እንደሚጨምር ዘንግተዋል። ይህ እግዚአብሔር የሚፈልገው ተግባራዊ የፍቅር ዓይነት ነው። ዓላማችን ትክክል ከሆነ፣ ዝንባሌያችንና ከሌሎች ጋር ያለን ግንኙነት ትክክል ከሆነ እርሱ ስለ መረጠው ጾምና ያ ጾም ደግሞ ምን ሊያደርግልን እንደሚችል እግዚአብሔር ይነግረናል።

ቁጥር 8፣ ‹‹ይህ ከሆነ ብርሃንህ እንደ ንጋት ጮራ ይፈነጥቃል፤ ፈውስህም ፈጥኖ ይደርሳል፤ ጽድቅህ ቀድሞህ ይሄዳል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ደጀን ይሆንልሃል›› ይላል።

እነዚህ የተስፋ ቃሎች፣ ‹‹ስሜን ለምትፈሩ ለእናንተ ግን የጽድቅ ፀሐይ፣ በክንፎቿ ፈውስ ይዛ ትወጣለች›› ከሚለው ሚልክያስ 4፡2 ላይ ካለው ተስፋ ቃል ጋር በጣም ይመሳሰላል። ይህም ቢሆን ከተመሳሳይ ወቅት ማለትም ከመጨረሻ ቀኖች ጋር የተያያዘ ነው። እግዚአብሔርን ለምንፈራ ለእኛ በክንፎቿ ፈውስ የያዘች የጽድቅ ፀሐይ ትወጣልናለች።

ኢሳይያስ 58፡8 ላይ ያለው አንኳር ተስፋ፣ ብርሃን፣ ጽድቅና ፈውስ ናቸው። ለነፍስ ጽድቅ፣ ለአካል ፈውስ ይሆን ዘንድ የጽድቅ ፀሐይ የሆነው ኢየሱስ መጥቷል። መጾም ስንጀምርና በትክክለኛ መንገድ፣ በትክለኛ ዓላማ እርሱን ስንፈልገው ብርሃን፣ ጽድቅና ፈውስ እንደሚሆን እግዚአብሔር ቃል ገብቷል።

በመቀጠል ቁጥር 9፣ ‹‹የዚያን ጊዜ ትጣራለህ፣ እግዚአብሔርም ይመልስልሃል፤ ለርዳታ ትጮኻለህ እርሱም፣ ‹አለሁልህ› ይልሃል›› ይላል። ለጸሎታችሁ መልስ ለመስጠት እግዚአብሔር አጠገባችሁ ይሆናል።

ከዚያም ቁጥር 9 ሁለተኛው አጋማሽ ላይ መጥፎ ዝንባሌን እንደሚያጠፋ እግዚአብሔር ያስጠነቅቃል። እንዲህ ይላል፣ «የጭቆና ቀንበር፣ የክፋትን ንግግርና ጣት መቀሰርን ከአንተ ብታርቅ።» እነዚህን በሦስት ሐረጎች ማጠቃለል እንችላለን። ቀንበሩ ወገኝነት ነው። ጣትን መቀሰር ነቃፊነት ነው። ክፉ ንግግር ቅንነት ማጣት ነው። እንግዲህ፣ ወገኝነትን፣ ሌሎችን መንቀፍና ቅንነት ማጣትን ካስወገድን እርሱ ሊሰማን ዝግጁ መሆኑን እግዚአብሔር ይናገራል።

ቁጥር 10፣ «ለተራበው ብትራራለት፣ የተገፉት እንዲጠግቡ ብታደርግ፣ ብርሃንህ በጨለማ ያበራል፤ ሌሊትህም እንደ ቀትር ፀሐይ ይሆናል» ይላል። የተግባራዊ ፍቅር አስፈላጊነትን ማየት ስንችል ብርሃን የጨለማን ቦታ ይይዛል።

ቁጥር 11፣ «እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይመራሃል፤ ፀሐይ ባቃጠለው ምድር ፍላጎትህን ያሟላል፤ አጥንትህን ያበረታል፤ በውሃ እንደረካ የአትክልት ቦታ፣ እንደማያቋርጥም ምንጭ ትሆናለህ» ይላል።

እነዚህን ቃሎች በማነብበት ጊዜ ቃል የተገባውን ተስፋ ማግኘት የምችለው እንዴት እንደ ሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ። ውስጤ፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ወደዚያ የሚያደርሰኝን መንገድ አሳየኝ» ይላል። ወደዚያ የሚያደርሰው መንገድ ቁጥር 6 ላይ ተገልፆአል። «እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? » በዚህ መሀል ስንጾም፣ ምሪትን፣ ቀና አቅጣጫን፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሓልዎትና ምሪት መጠበቅ እንችላለን። ዙሪያችሁ የቱንም ያህል የደረቀ ቢመስል፣በ ነፍሳችሁ ውስጥ የማያቋርጥ ምንጭ ይኖራችኋል።

በአንድ ወቅት ድርቅ ባጠቃው አካባቢ የኖርኩበት ጊዜ ነበር። በእንዲህ ዓይነቱ አካባቢ የአትክልት ቦታውን ውሃ የሚያጠጡና ውሃ የማያጠጡ ሰዎችን ማየት ቀላል ነው። የሚያስከትለው ለውጥ በጣም ከፍ ያለ ነው። በተመሳሳይ መንገድ የእግዚአብሔርን መስፈርት የሚያሟሉ፣ በዙሪያቸው ያለው ነገር ሁሉ፣ የደረቀ፣ የጠወለገና፣ የተቃጠለ ቢሆንም ውሃ እንደሚጠጣ የአትክልት ቦታ ይሆናሉ።



ከዚያም የእነዚህ የእግዚአብሔር ተስፋ ቃሎች መደምደሚያ ወደ ሆነ ተስፋ እንመጣለን። ቁጥር 12 የመመለስና የመታደስ ተስፋ ቃል ይዞአል። «ወገኖችህ የቀድሞ ፍርስራሾችን መልሰው ይሠራሉ።» በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተመልሰው መሠራት ያለባቸው ብዙ ቦታዎች መኖራቸውን ታውቃላችሁ? «አንተም፣ የተናዱ ቅጥሮችን አዳሽ፣ ባለ አውራ መንገድ ከተሞችን ጠጋኝ ትባላለህ።»

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔርንና ሰዎችን ስላንቀሳቀሱ ግለ ሰቦች መጠነኛ ጥናት አድርጌአለሁ። አገልግሎታቸው ከነበሩበት ዘመን አልፎ የሚሄድ በመሆኑ የብዙ ትውልዶችን መሠረት አድሰዋል። ጆን ኖክስን፣ ጆን ካልቪንን፣ ማርን ሉተርን፣ ጆን ዌስሊን፣ ቻርለስ ፊኒን የመሳሉ ታላላቅ ወንጌላውያንን ታሪክ ብትመለከቱ እያንዳንዳቸው ጾምን ይለማመዱ እንደ ነበር ትረዳላችሁ። እንግዲህ የብዙ ትውልዶችን የተናዱ ቅጥሮች ማደስ የምትፈልጉ ከሆነ ይህ ከእርሱ ጋር የሚሄድ ነው።

ከዚያ፣ «አንተም የተናዱ ቅጥሮችን አዳሽ፣ ባለ አውራ መንገድ ከተሞችን ጠጋኝ ትባላለህ» ወደሚለው ቁጥር 12 ላይ ወዳለው የመጨረሻ ተስፋ እንመጣለን። በእግዚአብሔር ሕዝብ ርስት መታደስ የሚገባቸው በጣም ብዙ የተናዱ ቅጥሮች አሉ። በሕዝቅኤል ምዕራፍ 22 እግዚአብሔር፣ «ምድሪቱን እንዳጠፋት ቅጥርን የሚጠግን፣ በፈረሰውም በኩል በፊቴ የሚቆምላት ሰው ከመካከላቸው ፈለግሁ፤ ነገር ግን አንድም አላገኘሁም» (ቁጥር 30) በማለት መናገሩን እናስታውሳለን። የምልጃ ጾም ጸሎት ቅጥር ይሠራል፤ በመካከል ይቆማል። የፈረሰውን አዳሽ ያደርገናል።

በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ የተጻፉ ታላቅ የመመለስና የመታደስ አርዓያ አለ። ይኸውም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮ ወደ ገዛ አገራቸው መመለሳቸውና በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ማደሳቸው ነው። ይህን ከዳንኤል ሕይወት ጋር በተያያዘ ተመልክተናል። ከዚህ ታላቅ ሂደት ጋር የተያያዙ የሁለት ወንዶችና አንዲት ሴትን ሕይወት እንመልከት።

በቅደም-ተከተሉ መሠረት እነዚህ ሰዎች ዕዝራ፣ ነህምያና አስቴር ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው ጾምን ተለማምደዋል፡፡

## ዕዝራ

ዕዝራ ከባቢሎን የሚመለሱ ምርኮኞችን ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እየመራ ነበር፡፡ በጉዞአቸው በወንበዴዎችና ጠላት በሆኑ ሕዝቦች በተሞላ አካባቢ ለጥቂት ወራት ማለፍ ነበረባቸው፡፡ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ከእነርሱ ጋር ነበሩ፤ ለእውነተኛ አይሁድ እጅግ አስፈላጊ የሆኑት ተዘርፈው ወደ ባቢሎን የተወሰዱ የቤተ መቅደሱን ንዋየ ቅዱሳትንም ይዘው ነበር፡፡

ከምስክርነታችን ከሚጠበቁ ነገሮች አንዱ በመሰከርነው መሠረት መኖራችን ነው፡፡ የመመስከር አንዱ መልካም ነገርም ይኸው ነው፡፡‹‹እግዚአብሔር እኛ አገልጋዮቹንም ይጠብቀናል፡፡ ምንም ችግር አደጋ ወይም አዳጋች ነገር ቢገጥመን እርሱ ረዳታችን ነው›› የሚል ደፋር ምስክርነት ለፋርስ ንጉሥ ሰጥቶ ነበር፡፡ አሁን ያንን አደገኛ ጉዞ ሊጀምሩ ነው፤ ስለዚህም፣ ወደ ንጉሡ ተመልሼ መፍራታችንና ወታደሮችና ፈረሰኞች ከእኛ ጋር እንዲሄዱ መጠየቅ አልፈልግም፡፡ ያን ማድረግ ምስክርነቴን ያበላሽብኛል፡፡ ታዲያ ምን ማድረግ አለብን? በማለት አሰበ፡፡

ዕዝራ በሁለት ምርጫዎች መካከል ሆኗል፤ ሥጋዊና መንፈሳዊ፡፡ ሥጋዊው ምርጫ በወታደሮችና በፈረሰኞች መደገፍ ነው፤ ያንን የሚያገኝበት መንገድ ደግሞ ተዘግቷል፡፡ ስለዚህ አንድ ምርጫ ብቻ ነበረው፤ ይኸውም መንፈሳዊው ነው፡፡ ታዲያ፣ መንፈሳዊው የሚገለጠው በምን መልክ ነው፤ በጸሎትና በጾም፡፡

> ራሳችንን በአምላካችን ፊት ዝቅ እንድናደርግ፣ ጉዞውም ለእኛና ለልጆቻችን፣ ለንብረታችንም ሁሉ የተቃና እንዲሆንልን፣ እዚያው በአሐዋ ወንዝ አጠገብ ጾም አወጅሁ፡፡ ‹‹መልካሚቱ የአምላካችን እጅ በሚፈልጉት ሁሉ ላይ ናት፤ እርሱን በሚተው ሁሉ ላይ ግን ቁጣው ትወርድባቸዋለች›› ብለን ለንጉሡ ነግረነው ስለነበር፣ በመንገድ ላይ ከጠላት የሚጠብቁን ወታደሮችንና ፈረሰኞችን እንዲሰጠን ንጉሡን ለመጠየቅ አፍሬ ነበር፡፡ ስለዚህ ጾምን፤ ወደ አምላካችንም ስለዚህ ነገር ልመና አቀረብን፤ እርሱም ጸሎታችንን ሰማ፡፡ ዕዝራ 8:21-23



እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰማ፡፡ የጸሎትና የጾም ኃይል ማንኛውም ወንበዴ፣ ማንኛውንም ዘራፊ፣ ማንኛውም ጠላት ጎሳ፣ መንገድ ላይ ሊያገኛቸው የሚችል ማንኛውም ዓይነት ወረርሽኝና በሽታ አሰረ፡፡ ከመካከላቸው አንድ ሰው እንኳ ሳይሞት፣ ይዘውት ከነበረ ውብ ንዋየ ቅዱሳት አንድ እንኳ ሳይጠፋ በሰላምና በደኅና ወደ ፈለጉት ስፍራ ደረሱ፡፡ ይህ ከታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አንዱ ነው፡፡ በመንፈሳዊው ክልል ድል ካገኛችሁ፣ በእርግጥም ድል አግንታችኋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለዘመናችን ጠቃሚ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ለፖለቲካዊ፣ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች መልስ ይልጋል፡፡ በጸሎትና ጾም አማካይነት አንድ ሰው በመንፈሳዊው ክልል ድል ካገኘ በሰው በኩል ያለው ችግር ሁሉ ይስተካከላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ድል ካገኛችሁ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮች መልስ ሲይዙ ማየት ትችላላችሁ፡፡

## ነህምያ

በዚህ የመመለስና የመታደስ ሂደት ሁለተኛው ሰው ነህምያ ነው፡፡ ነህምያ ሲናገር፣ ‹‹በሕይወት ተርፈው ከምርኮ ወደ አገራቸው የተመለሱት ሰዎች በታላቅ ውርደት ላይ ይገኛሉ፤ የኢየሩሳሌም ቅጥር ፈራርሶአል፤ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋል አሉኝ›› በማለት ይናገራል (ነህምያ1:3)፡፡

የነህምያ ምላሽ፣ ቀጥሎ ያለው ቁጥር ላይ ይገኛል፤ ‹‹ይህን ነገር በሰማሁ ጊዜ አያሌ ቀናት አዘንሁ፣ ጾምሁ፣ ጸለይሁም›› (ቁጥር4)፡፡

ነህምያ ምስጢሩን ያውቃል፡፡ መንገዱ ተዘግቷል፤ ሁኔታው ተስፋ ቢስ ነው፡፡ ጾመ፤ ጸለየ፤ እግዚአብሔርም መንገዱን ከፈተ፡፡ እግዚአብሔር ለነህምያ መንገድ መክፈት ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሩሳሌም ከተማን እንደ ገና

ለመሥራት ከንጉሡ ዘንድ ሙሉ ሥልጣንና የሚያስፈልገውን ሁሉ ነገር አስገኘለት። ይህ ሁሉ የሆነው በጾምና በጸሎት ነበር።

## አስቴር

አሁን ወደ መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ 4 ሂዱ። ይህ እስከ ዛሬ ድረስ በጠቅላላው ታሪካቸው ሁሉ ሌላው ቀርቶ በአዶልፍ ሂትለር ዘመን እንኳ አይሁድን ከገጠማቸው ችግር የሚበልጥ ታላቅ መከራ ነበር። ሂትለር ያጠፋው አንድ ሦስተኛውን የአይሁድ ሕዝብ ሲሆን፣ የፋርስ ንጉሥ ግን መላውን የአይሁድ ሕዝብ ማጥፋት ፈልጓል።

በአይሁድ ላይ የጠላት መሣሪያ የሆኑ ከሐማን በታች ያሉ አንዳንድ ክፉ ሰዎችና ከፍተኛ የንጉስ ባለ ሥልጣኖች ወደ ንጉሥ በመቅረብ በፋርስ መንግሥት ውስጥ ሁሉ ያሉ አይሁድ እንዲገደሉ አዋጅ ማሳወጅ ችለው ነበር። መጽሐፈ አስተር ፑሪም ለሚሉት ለአይሁድ በዓል መፈጠር ምክንያት የሆነ ታሪክ ይዟል፤ በዕብራይስጥ ፑሪም ዕጣ ማለት ነው። በዓሉ ይህን ስም ያገኘው አይሁድ በየትኛው ቀን መገደል እንዳለባቸው ለማወቅ ሐማን ዓመቱን ሙሉ እጣ በማውጣቱ ነበር። እጣ ማውጣቱ የሚያመለክተው ይህን እንደ መንፈሳዊ ጉዳይ መመልከቱንና ልዕለ ተፈጥሮአዊ ምሪት ይፈልግ እንደ ነበር ነው። የሚመክሩት ጥበበኞች ወይም አስማተኞች ነበሩት። ከተፈጥሮአዊ ጥበብ የበለጠ ነገር እንደሚያስፈልጋቸው በሚገነዘቡበት ጊዜ መንፈሳዊ ያልሆኑ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚከተሉት እንዲህ ዓይነቱን መንገድ ነው። ምክር ለማግኘት ወደ ሰይጣናዊ አሠራር ዘወር ይላሉ።

ይህ በብርሃን ኃይሎችና በጨለማ ኃይሎች፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በሰይጣን ኃይል መካከል የተካሄደ መንፈሳዊ ግጭት ነበር። ሁሉም የየራሳቸው ወኪሎች በየስፍራው ነበሯቸው። በሐማን አማካይነት የተነሣሣው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሰይጣናዊ ኃይል መልሱ በአስቴር አማካይነት የተቀጣጠለው ልዕለ ተፈጥሮአዊ የእግዚአብሔር ኃይል ነበር። አስቴር ወሬውን ስትሰማ፣ ‹‹ሂድና በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ በአንድነት ሰብስብ ስለ እኔም ጹሙልኝ፤ ቀንም ይሁን ሌሊት ለሦስት ቀን አትብሉ፤ አትጠጡም እኔና ደንገጡሮቼም እናንተ



እንደምታደርጉት ሁሉ እንጾማለን፤ ይኅ ከተፈጸመ በኋላ ግን ነገሩ ምንም እንኳ ከሕግ ውጭ ቢሆንም፣ ወደ ንጉሡ እሄዳለሁ፤ ከጠፋሁም ልጥፋ። በማለት ለአጎቷ ለመርዶክዮስ ነገረችው (አስቴር 4:16)።

በአረተኛው ቀን አስቴር የክብር ልብሷን ለብሳ ወደ ንጉሡ አዳራሽ ሄደች፤ በእርሱም ዘንድ ሞገስ አገኘች። በእጁ የያዘውን የወርቅ ዘንግ ዘረጋላትና፣ «ንግሥት አስቴር ሆይ፣ ምን ትፈልጊያለሽ›› አላት።

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመደምሰስ የወጣው እቅድ በፋርስ መንግሥት ውስጥ ከታየው የበለጠ ታላቅና እጅግ አስደናቂ ድል ሆነላቸው። እስራኤል ዳነ፤ ሐማ ባዘጋጀው መስቀያ ተሰቀለ። ሁኔታውን ሁሉ የለወጠው ምን ነበር? የአስቴር፣ የደንገጡሮቿና የአይሁድ ሁሉ ጸሎትና ጾም ነበር።

## አራት የጾም መርሖዎች

ከጾም ጋር በተያዘ የእግዚአብሔር ቃል ብዙ መሠረታዊ መርሖዎች ያቀርባል። ቀጥሎ ያሉት አራቱ ናቸው። ራስን መካድ፣ ራስን ዝቅ ማድረግ፣ ተገቢ ነገርን ማስቀደምና በእግዚአብሄር መታመን። እስቲ በአጭሩ እንያቸው።

## ራስን መካድ

ማቴዎስ 16:24 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ›› አለ። ጾም አሮጌው አመፀኛ እኔነታችንን መካድ ነው። በአጭር አነጋገር መካድ ‹‹አይሆንም›› ማለት ነው። ሆዳችሁ፣ ‹‹ምግብ እፈልጋለሁ›› ይላል፤ እናንተ ደግሞ፣ ‹‹አይሆንም!›› ትሉታላችሁ።

ከ1ቆሮንቶስ 9:27 እንደምንመለከተው ጳውሎስ፣ ‹‹ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ እኔ ራሴ ውድቅ ሁኜ እንዳልቀር፣ ሰውነቴን እየጎሰምሁ እንዲገዛልኝ አአደርገዋለሁ›› ብሏል።

በሩጫ ውድድር አሸናፊ መሆን የሚፈልጉ ሰዎች ልከኞች ናቸው፤ በሁሉም ነገር ራሳቸውንም ይገዛሉ ብሏል (ቁጥር25)። መንፈሳዊ ሩጫ ውስጥ ያለን ሰዎችስ ምን ያህል ራሳችንን መግዛት ይኖርብን ይሆን? ፕሮፌሽናል ሯጭ ምን እንደሚመገብ፣ ምን ያህል መተኛት እንዳለበት ይጠነቀቃል። የሚጠብቀውን ስኬት

ሲያበላሹት ስለሚችል ሌላው ቀርቶ የአእምሮ ዝንባሌውን እንኳ ይቆጣጠራል። እንደ ክርስቲያኖች እኛስ አካላችንን እያስገዛን ያለነው ለእንዴት ያሉ ነገሮች ስለ መሆኑ ምን ያህል እርግጠኞች መሆን ይኖርብናል!

ከጥቂት ዓመታት በፊት እግዚአብሔር እንነዲህ በማለት ተናገረኝ፤ ወደ ፊት መገስገሥ ከፈለግህ ሁለት መስፈርቶች አሉ። የመጀመሪያው መስፈርት እድገት ሁሉ በእምነት መሆኑ ነው። በእምነት ወደ ፊት መገስገሥ የማትፈልግ ከሆነ፤ ወደ ፊት መሄድ አትችልም። ሁለተኛው መስፈርት ይህ ነው የሰጠሁህን አገልግሎት መፈጸም ካለብህ ብርቱና ጤነኛ አካል ያስፈልገሃል። ውፍረት እየጨመርህ ነው፤ ያንን በተመለከተ መጠንቀቅ ይኖርብሃል።

እግዚአብሔር በትክክል እንደዚያ ነበር የተናገረኝ። ከዚያ ወዲህ ባለፉት ዓመታት ብርቱና ጤነኛ አካል እደሚያስፈልገኝ እያስተዋልኩ መምጣቴን ስነግራችሁ እመኑኝ። በሕይወቴ ያለውን የእግዚአብሔር ጥሪ በመፈጸም ረገድ ከማገኛውም ይልቅ ለእኔ የበለጠው ነገር በመንፈሳዊ፤ በአእምሮአዊና አካላዊ ነገሬ ምቹ ሆኜ እንድገኝ ማድረግ የምችለውን ማንኛውንም ነገር አደርጋለሁ።

## ራስን ዝቅ ማድረግ

ጾም ራስን ዝቅ ማድረግ ነው። «በስሜ የተጠራው ሕዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢጸልይ ...» ከሚለው 2 ዜና መዋዕል 7:14 ላይ ካለው አንጻር ራስን ስለ ማዋረድ ተነጋግረናል።

ራሳችንን ዝቅ የምናደርገው ወይም የምናዋርደው እንዴት ነው? ዳዊት ይህን በተመለከተ በሁለት መዝሙሮቹ ማለትም መዝሙር 35:13 እና 69:10 ላይ ጽፏል። በሁለቱም ቦታ፤ «ነፍሴንም በጾም አደከምኋት (አዋረድኋት)» ብሏል። አንዳንድ ሰዎች፤ «እግዚአብሔር ሆይ፤ ትሑት አድርገኝ» በማለት ይጸልያሉ፤ ያ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጸሎት አይደለም። እግዚአብሔር፤ «ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ» ነው ያለው። ራሳችንን ዝቅ የምናደርገው ወይም የምናዋርደው እኛው ራሳችን ነን። ነፍሳችንን የምናዋርድበት አንድ ጥሩ



መንገድ ጾም ነው።

## ተገቢ ነገርን ማስቀደም

ጾም ተገቢ ስለሆነ ነገር ቅድሚያ ይሰጣል። ቀደም ሲል፤ «ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔር መንግሥትና ጽድቁን ፈልጉ» የሚለው የኢየሱስ መመሪያ ተመልክተናል (ማቴዎስ 6:33)። ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚፈልጉት በሁለተኛ፤ ሦስተኛ ወይም አራተኛ ደረጃ ነው። እንደዚያ ከሆነ ተስፋው እውን አይሆንም። ጾም ለመንፈሳዊው ቅድሚያ የምንሰጥበት፤ ከሁሉም በላጭ መሆኑን የምንገነዘብበት መንገድ ነው።

ጾም በእግዚአብሔር መታመናችንንም ያሳያል። ጾም፤ «እግዚአብሔር ሆይ፤ መልሱ የለኝም። ሊኖረኝም አይችልም። መልሱን እንድትሰጠኝ አንተን ተስፋ አደርጋለሁ» በማለት ለእግዚአብሔር የምናገርበት ነው። በእግዚአብሔር መደገፍን ይገነዘባል፤ ወደ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነትም ይመራናል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእነዚህ ነገሮች አንጻር መስፈርቱን ሲያሟሉ እነርሱን በተመለከተ ጣልቃ በመግባት እግዚአብሔር መልስ እንደሚሰጣቸው ለማሳየት ከቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ጥቅሶችን ማቅረብ ይቻላል።

ምናልባት የጾማችሁ እንደሆነ ሳይሆን፤ ስትጾሙ

የተራራው ስብከት መካከል ላይ ኢየሱስ፤ «ስትጾሙ» አለ (ማቴዎስ 6:16)። ኢየሱስ ምናልባት የጾማችሁ እንደሆነ አላለም። እንደዚያ ቢል ኖሮ መጾም ወይም አለመጾም ይቻላል ለማለት ያስችል ነበር። እርሱ ግን ስትጾሙ ነበር ያለው። መጾም እንደሚገባን ነው የተናገረው። በዚህ ምንባብ ሦስት ነገሮችን ማለትም በጎ ምግባርን (ቁጥር3)፤ ጸሎትን(ቁጥር5) እና ጾምን በተመለከተ ሲናገር ተመሳሳይ ቋንቋ ተጠቅሟል። በጎ ምግባር ክርስቲያናዊ ግዴታ ነውን? መጸለይ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነውን? እንግዲያውስ መጾምም ክርስቲያናዊ ግዴታ መሆን አለበት።

አንዳንድ ሰዎች መጾም እንደማይገባ ለማሳየት ማርቆስ 2:18 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ይጠቅሳሉ።

ከዚህ ምንባብ እንደምንመለከተው ሰዎች ወደ ኢየሱስ በመምጣት ፈሪሳውያን ይጾማሉ፣ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ይጾማሉ፣ የአንተ ደቀመዛሙርት ግን የማይጾሙት ለምንድነው? በማለት ጠይቀውት ነበር። ኢየሱስም እንዲህ በማለት መለሰ፣

> ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ሊጾሙ ይችላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሊጾሙ አይችሉም፤ ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወቅት ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ግን ይጾማሉ። ማርቆስ 2፡19-20

ይህን ቃል የምረዳው እንዲህ ነው። ሚዜዎች ደቀመዛሙርት ናቸው። ሙሽራው ጌታ ክርስቶስ ነው። ሙሽራው በአካል በምድር እስካለ ድረስ ደቀመዛሙርቱ አይጾሙም። ይሁን እንጂ ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ጊዜ እንደሚመጣና በእነዚያ ቀኖች እንደሚጾሙ ኢየሱስ ተናግሮአል። አሁን ሙሽራው በአካል ከእኛ ጋር ነው ወይስ ከእኛ ተለይቶ በመሄዱ መመለሱን እየጠበቅን ነው? የሚል ነው። እርሱ ከእኛ ተወልዶአል፤ የእርሱ ደቀመዛሙርት ከሆንን እንጾማለን። የማንጾም ከሆነ ግን አንድ የደቀ መዝሙርነት ምልክት ጎድሎናል።

## የምንከተለው አርዓያ

ኢየሱስ ጾምን ተለማምዶአል (ማቴዎስ 4፡1-2)። በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን የነበሩ አምስት ነቢያትና መምህራን ጾመዋል፤ በአንድነት ሆነው እግዚአብሔርን ጠብቀዋል (የሐዋርያት ሥራ 13፡1-2)። በርናባስንና ሳውልን (ጳውሎስ የተባለውን) እንዲልኩ እግዚአብሔር ተናገራቸው። ለሁለተኛ ጊዜ ከጾሙና ከጸለዩ በኋላ ላኩዋቸው(ቁጥር3)። ሳውልና በርናባስ በመጀመሪያ ሐዋርያዊ ጉዞአቸው ቀደም ሲል የተለዩዋቸው አማኞችን አግኝተው ጾመው ጸለዩ (የሐዋርያት ሥራ 14፡23ይመ)። እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ሕልውና ያገኙት በአንድነት ጾም ጸሎት ነበር። ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ይጾም ነበር። እንደ የክርስቶስ አገልጋይ ብቁ አድርጎ ራሱን ከሚያቀርብባቸው ነገሮች አንዱ



ነበር (2ቆሮንቶስ 6፡4-5፤11፡27ይመ)።

የጸሎታችን መልስ ማግኘት የምንፈልግ ከሆነ የጾምን ኃይል እግዚአብሔር አሳይቶኛል፤ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናች ለቤተክርስቲያን የምናቀርበው ጸሎት ከዚህ ቻነሰ ሊሆን አይችልም። የእርሱ ጸጋና ታማኝነት በፍቃዳችን ወደ እርሱ በመመለስ ምላሽ እንድንሰጥ ያነሣሣናል። ዓላማው ሲፈጸም ለማየት በታደሰ ትጋትና ቅንዓት፣ በልበ ሙሉነትና እምነት እንቅረብ።

# 9

## የከበረች ቤተ ክርስቲያን

### በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ወደዳት፤ ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ ሰጠ። ኤፌሶን 5:25-26

የካህናት መንግሥት ነን፤ ለመጸለይ የተጠራነውም በዚሁ መልክ ነው። የጸሎታችን መጨረሻ ግብ ምድነው? እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ለኢየሱስ መመለስ ድል አድራጊ፣ ፍጹምና ዝግጁ እንድትሆን ነው። ይህ በቃሉ የተሰጠን የእግዚአብሔር መመሪያ፣ በልባችን ያለ ናፍቆት ሁሉ ፍጻሜ ነው።

በዚህ ዘመን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ያላቸው ብዙዎች ምን እንደ ሆነ ሐሳቡ የላቸውም ወይም ስለ ከበረች ቤተ ክርስያን እንኳ መናገር አይችሉም። ቤተ ክርስቲያን ማለትም ኢየሱስ የሚመጣላት ሙሽራ የከበረች፣ እንደምትሆን ቅዱሳት መጻሕፍት ያመለክታሉ። ክብር ለሚለው ቃል ግሪክኛው ዶክሶ ሲሆን፣ ዶክሶሎጂ የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል የተገኘው ከዚሁ ቃል ነው፤ ትርጉሙም፣ ‹‹ለእግዚአብሔር ክብር የሆነ ነገር›› ማለት ነው።

ወደ አዲስ ኪዳን ግሪክ የመጣሁት በጣም ጥንታዊ በሆነው ግሪክኛ ዘይቤ በክላሲካል ግሪክ በኩል ነበር። የፕላቶ ፍልስና ተማሪና መምህር እንደነበርኩ ተናግሬአለሁ፤ ከፕላቶ ፍልስፍና መሠረታዊ ጽንሰ



ሐሳቦች አንዱ ዶክስ በሚለው ቃል ይጠቃለላል። በዚህ ቃል ውስጥ ግራ የሚያጋባኝ ልዩነት አለ። በፕላቶ ሥራዎች ውስጥ ዶክስ፣ ‹‹ክብር›› የሚለውን ቃል የሚያመለክት ሳይሆን፣ ይልቁን የሚያመለክተው፣ ‹‹የሚመስል ነገር፣ የሚታይ፣ አስተሳሰብን›› ነው።

በመጠኑም ቢሆን ለውጥ ወዳድ ስለ ነበርኩ ከካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ እረፍት ላይ በነበርኩ ጊዜ አንድ ወቅት ላይ የዩሐንስን ወንጌል በግሪክ ለማንበብ ወሰንኩ። ይህን እንደማደርግ በግል ግሪክኛ ለሚያስተምረኝ ሰው ነገርኩት፤ እርሱ ግን እንደዚያ እንዳላደርግ አጥብቆ መከረኝ። ክላሲካል ግሪክኛ ዘየየን እንደሚያበላሽብኝ ነገረኝ። እርሱ አጥብቆ መናገሩ ግን ይበልጥ በውሳኔየ እንድጸና አደረገኝ! ስለዚህም እረፍት ላይ በነበርኩ ጊዜ ሙሉውን የዩሐንስ ወንጌል በግሪክ አነበብኩ።

በዚያ ወቅት በጣም ከእግዚአብሔር ርቄ ያለሁ ሰው ነበርኩ። ክርስቲያን ነኝ ብዬ ተናግሬም አላውቅም። ፍልስፍናን ሙያየ አድርጌ የያዝኩ ሰው ነበርኩ፤ ይህ መልእክት ግን ከአእምሮየ አልወጣ አለ። ከደቡቡ አገር ከስመርሴት በባቡር እየተጓዝኩ ነበር። ለንደን ፓዲንግተን ባቡር ጣቢያ ስደርስ ከአንድ ተማሪ ጓደኛዬ ጋር ተናገርሁ። ‹‹የዩሐንስን ወንጌል እንቆቅልሽ እኮ ፈታሁት›› አልኩት፤ ልክ ይህንንኑ ነበር የተናገርኩት። እንዴት እንደ ፈታሁት ባላውቅም ፈትቼው ነበር! በዩሐንስ ወንጌል ውስጥ በጣም ትኩረቴን የሳበው ነገር፤ ዩሐንስ ደክሶ የሚለውን ቃል፣ ‹‹ክብር›› ለማለት ነበር የተጠቀመበት። በጣም ጥንታዊ የተባለ ግሪክኛ ቃሉን የተጠቀመበት በተለየ መልኩ ሲሆን እንዴት እንደዚያ ሊሆን እንደ ቻለ መገረሜን አስታውሳለሁ።

ከጥቂት ዓመት በኋላ በዚያ መከላከያ ውስጥ እያለሁ። እኩለ ሌሊት ላይ ጌታ ተገናኘኝ፤ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም ተወለድሁ። ሁለት ሳምንት በማይሞላው ጊዜ በዚያው ክፍል ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቅሁ። በዚያ ጊዜ የብርሃን ጎርፍ ወደ ውስጤ ገባ፣ ልክ ከአምስት ደቂቃ በፊት ያነበብኳቸው ያህል ባለፈው ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያነበብኳቸው ነገሮች እንደ ገና ወደ ውስጤ መጉረፍ ጀመሩ። በቅጽበት ደክስ የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለበትን ሁኔታ በተመለከተ ግራ ሲያጋባኝ የነበረውን ነገር ተረዳሁት።

በክልሲካል ግሪክ፣ ‹‹የሚታይ፣ መስሎ የሚታይ›› ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ግሪክ ግን፣ ‹‹ክብር›› ማለት ነው። ይህ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጽ ነገር በመሆኑ ነው። ሰው መረዳት በሚችለው መልኩ የሚታይ፣ ጉልህ የሆነ ሐልዎቱ ነው።

በሐዋርያት ሥራ 7 ተጽፎ እንደምናገኘው እስጢፋኖስ ለአይሁድ ሸንጎ ሲናገር፣ ‹‹አባታችን አብርሃም ወደ ካራን ከመምጣቱ በፊት ገና በመስጴጦምያ ሳለ፣ የክብር አምላክ ተገለጠለት›› ብሏል (ቁጥ22)። አብርሃም እግዚአብሔርን በክብሩ እንዳወቀው እነግራችኋለሁ። እርሱን የተለየ ያደረገው ይኸው ነበር። በመስጴጦምያ በነበረ ጊዜ በሚታይ ክብር ለአብርሃም ተገለጠ። ሁሉን በመተው ወደ ተስፋው ምድር እስኪሄድ ድረስ ይህ የአብርሃምን ሕይወት፣ ዓላማና ፍላጎት ለውጦታል።

ይህ ደግሞ ወደ ቤተክርስቲያን ያመጣናል። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ከበረች ቤተክርስቲያን ሲናገሩ በእግዚአብሔር ክብር የተሞላች ቤተክርስቲያን፣ ሆሉን የሚችል ሐልዎት በሚታይ፣ ንጹህ በሆነ ሁኔታ በውስጧ ስላለ ቤተክርስቲያን መናገራቸው ነው። ያለ አንዳች መለኮታዊ መገለጥ በእምነት ብቻ የምትኖር ቤተክርስቲያን ሳይሆን፣ የሚታይ፣ ጉልህ የሆነ ሐልዎቱ በሕዝቡ ውስጥ ወደሚታይበት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የገባች ቤተክርስቲያን ናት። ክርስቶስ የሚመጣው ለእንዲህ ዓይነቷ ቤተክርስቲያን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። የምንጸልየው ለእንዲህ ዓይነቷ ቤተክርስቲያን ነው።

## የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሰባት ምልክቶች

በኤፌሶን መልእክት ጌታ በሚመጣላት ጊዜ ሆና ስለምትገኘው ሰባት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የተለዩ ምልክቶች ተሰጥቶናል። ‹‹ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ወደዳት፤ ራሱን ስለ እርሷ አሳልፎ ሰጠ፤ በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት ቀደሳት›› (ኤፌሶን 5፡25-26)።



በቃሉ ንጹሕ ውሃ አማካይነት ለቀደሳት ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን እንደዋጃት ምዕራፍ 7 ላይ ተመልክተናል። ቤተ ክርስቲያንን ለጌታ መምጣት ዝግጁ ለማድረግ ደሙና የቃሉ ውሃ ያስፈልጋሉ።

የእግዚአብሔርን ቃል በመማርና ራስን በመግዛት፣ በመቀደስና በመንጻት ሂደት ውስጥ ያላለፈ ማንኛውም ክርስቲያን ጌታን ለመቀበል ዝግጁ ነው ብዬ አላምንም። የኢየሱስ ደም ከሰይጣን እጅ የወጣንበት ለመዋጀታችን የተከፈለ ዋጋ ነው። በደሙ ከተዋጀን በኋላ በቃሉ አማካይነት በውሃ በመታጠብ እንቀደሳለን፣ እንነጻለን። ኢየሱስ ይህን የሚያደርግበት ዓላማ ቤተክርስቲያንን፣ ‹‹ጉድፍ ወይም የፊት መጨማደድ ወይም አንዲት እንከን ሳይገኝበት ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች ክብርት ቤተክርስቲያን›› አድርጎ ለራሱ ማቅረብ ነው(ቁጥር27)።

ኢየሱስ የሚመጣላት እውነተኛ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ሦስት ምልክቶች በዚህ ጥቅስ ተዘርዝረዋል። (1)ክብርት ናት - ይህ በመካከልዋ ባለው የእግዚአብሔር ሓልዎት መገለጥ ይታያል። (2) ቅድስና (3) ነውር አልባ ናት።

ወደ ኤፌሶን 4 ከሄድን ደግሞ ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ መምጣት ዝግጁ ስለምትደረግበት ሂደት እንመለከታለን። ቁጥር 11 ስለ አምስቱ ‹‹አካል ገንቢ›› የቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ይናገራል። ‹‹አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ(ክርስቶስ) ነው። እነዚህ አገልግሎቶችን የሰጠው፣ ‹‹የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ነው›› (ቁጥር12)።

አምስቱ መሠረታዊ አገልግሎቶች የክርስቶስን አካል ለማነጽ ወይም ለመገንባት የአገልግሎት ሥራ ለመሥራት ቅዱሳንን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ‹‹ሁላችንም ወደ እምነት አንድነት እንድንደርስ›› የሚለው ቀጥሎ ያለው ቃል ግቡን ይገልጻል። ግሪኩ፣ ‹‹የእምነት ኅብረት›› ይላል። ‹‹የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ›› (ቁጥር 13) ለሚደረገው ጉዞ መድረሻ ቦታ ነው። የግሪክኛው ቃል፣ ‹‹ዕውቀት›› ብቻ ሳይሆን ‹‹ማመን›› - ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስን

ማመን ነው የሚለው።

ወደ እምነት ኅብረት የምንመጣው ኢየሱስን በማወቅ በኩል ብቻ ነው። ቁጭ ብሎ አስተምህሮዎችን በመወያየት አይደለም። አንድ በጣም በእርግጠኝነት የምናገረው ስለ አስተምህሮዎች መወያየት ክርስቲያኖችን ወደ ኅብረት የማያመጣ መሆኑን ነው። ኅብረት የምናደርገው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ መሆን ዙሪያ በአንድነት በመምጣት በማንኛውም የቤተክርስቲያን ገጽታ የበላይ መሆኑን ስናምን ያኔ ወደ እምነት ኅብረት እንመጣለን።

ከአዳኙ ማንነት ውጪ የድነት አስተምህሮ ትርጉመ ቢስ ነው። ከፈዋሹ ውጪ የፈውስ አስተምህሮ ትርጉመ ቢስ ነው። ከነጻ አውጪው ውጪ የነጻ መውጣት አስተምህሮ ትርጎመ ቢስ ነው። ያለ አጥማቂው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ትርጉም አይኖረውም። በአዳኙ ስናምን ድነትን እናምናን። ፈዋሹን ስናምን ፈውስን እናምናለን። ነጻ አውጪውን ስናምን ከክፉ መናፍስት ነጻ መውጣትን እናምናለን። አጥማቂውን ስናምን በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅን እናምናለን።

በማንኛም መልኩ የኅብረት መንገዱ፣ በአስተምህሮ የመከራከርና የመወያየት መንገድ ሳይሆን በክብሩ፣ በሥልጣኑ፣ በማንኛውም የአገልግሎቱ ገጽታ ራስ መሆኑን ማመን ነው። ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የሆነውን ሁሉ ስናምን፣ ወደ እምነት ኅብረት እንመጣለን።

በዚህ በኩል ወደ ሁለት ተጨማሪ የእግዚአብሔር ፈቃድ ክፍል እንመጣለን። የመጀመሪያው፣ «ፍጹም ሰው » መሆን ነው። ፍጹም የሚለው ቃል፣ «ወደ ብስለት፣ ያደገ ሰው ወደ መሆን» ቢባል ይበልጥ ግልጽ ይሆናል። ከዚያ፣ «በክርስቶስ ሙሉ ሰው» መሆን ነው (ቁጥር 13)። እዚህ ላይ ቁልፍ የሆነው ቃል ሙሉ የሚለው እንደ ሆነ አምናለሁ። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንደ የእርሱ አካል በማንኛውም ገጽታ በማንኛውም ጸጋ፣ በማንኛውም ስጦታ፣ በማንኛውም አገልግሎት በሙላቱ ሁሉ ክርስቶስን ማሳየት እስክትችል ድረስ ክርስቶስን ለመግለጥ ዝግጁ አይደለችም።



አሁን ባለንበት ዘመን ከክርስቶስ ሙሉነት ለዓለም የምንገልጠው እጅግ በጣም አነስተኛ የሆነውን ክፍል ነው። ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ያልገለጠችው ብዙ የክርስቶስ ማንነት አለ፤ ይሁን እንጂ በሰብዕናውና በአገልግሎት እንደ ተባባሪ አካል የኢየሱስ ክርሾቶስን ሙላት ወደምትገልጥበት ደረጃ እግዚአብሔር ያመጣታል። ሙላት ማለትም ይኸው ነው።

ስለሆነም፣ የራሱ ሊያደርጋትና ከዚያም ወደ ራሱ ሊወስዳት እግዚአብሔር እያዘጋጃት እያለ ስባቱ የቤተ ክርስቲያን የተለዩ ምልክቶች እንመለከታለን። (1) ክብርት ትሆናለች - በተገለጠው የእግዚአብሔር ሓልዎት የተሞላች፤ (2) ቅድስት ትሆናለች፣ (3) ያለነውር ትሆናለች፣ (4) ወደ እምነት ኅብረት ትመጣለች፣ (5) የኢየሱስ ክርስቶስን ራስነትና ጌትነት ታምናለች፤ ከዚህም የተነሣ ፣ (5) ወደ ብስለት፣ (7) የክርስቶስን ሙላት ለዓለም የምትገልጥ ትሆናለች።

በኤፌሶን መልእክት ሐዋርያው ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን ያደረገውን ግሩም ጸሎት እናገኛለን -

> በዚህም ምክንያት በአብ ፊት እንበረከካለሁ፤ ከእርሱም በሰማይና በምድር ያለ ቤተሰብ ሁሉ ስያሜ ያኛል። በውስጥ ሰውነታችሁ እንድትጠነክሩ፣ ከክብሩ ባለጠግነት በመንፈሱ በኩል ኃይል እንዲሰጣችሁ እጸልያለሁ፤ ይኸውም በእምነት ክርስቶስ በልባችሁ እንዲያድር ነው። ደግሞም ሥር ሰዳችሁ፣ በፍቅር ታንጻችሁ፤ የክርስቶስ ፍቅር ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ከፍታውና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደ ሆነ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር የመገንዘብ ኃይልን እንድታገኙ ነው። እስከ እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ልክ ደርሳችሁ እንድትሞሉ፣ ከመታወቅ በላይ የሆነውን የክርስቶስን ፍቅር ታውቁም ዘንድ ነው። ኤፌሶን 3:14-19

ግልጽ ማድረግ የምፈልገው ማንኛችንም በግል ይህን መገንዘብ እንደማንችል ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን ሙላት፣ ከፍታ፣ ጥልቀት፣ ስፋትና ርዝመት መገንዘብ የምንችለው ከሌሎች አማኞች ጋር ከቅዱሳን ሁሉ ጋር በአንድነት

ሆነን ስንመጣ ብቻ ነው።

‹‹እስከ እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ደርሳችሁ እንድትሞሉ፣ ከመታወቅ በላይ የሆነውን የክርስቶስን ፍቅር ‹‹(ቁጥር 9) ያውቁ ዘንድ ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን ጸልዮአል። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ሙላት ሁሉ የሚኖርባት ቦታ መሆንዋን የሚያመለክተው አባባል ድንቅ አይደለም? በባሕርዩ ሁሉ፣ በኃይሉ ሁሉ፣ በገጽታዎቹ ሁሉ የእግዚአብሔር ሙላት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገለጣል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ የእግዚአብሔር ሙላት የሚል ሐረግ የተጠቀሰበት አንድ ሌላ ክፍል ብቻ አውቃለሁ፤ ያም ቆላስይስ ምዕራፍ 2 ነው። ቃሉ እንዲህ ይላል፣ ‹‹የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ(በክርስቶስ) ይኖራልና›› (ቁጥር9)። በክርስቶስ ውስጥ እግዚአብሔር ተገልጧል። የተገለጠው በሙላት እንጂ በከፊል ወይም ግማሹ አይደለም። ከላይ ከተመለከትነው የኤፌሶን መልእክት ክብሩን የሚገልጥና እንዲገኝ የሚያደርግ መንፈስ መሆኑን ልብ አድርጉ። መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን አካል የመገንባት ሥራውን ከፈጸመ በኋላ፣ እንደ ገና የእግዚአብሔር ሙላት ይገለጣል።

በግላችሁ ይህ ይሆናል ብላችሁ አታስቡ። ከቅዱሳን ሁሉ ጋር የእግዚአብሔርን ስፋት፣ ርዝመት፣ ከፍታና ጥልቀት መረዳት የምትችሉና በዚህም ምክንያት በእግዚአብሔር ሙላት የምትሞሉት ከሌሎች አማኞች ጋር ሆናችሁ ወደ እምነት ኅብረት ስትመጡና ክርስቶስን ስታውቁ ብቻ ነው። የክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ዓላማ ይኸው ነው።

## ይህ እንዴት እደሚሆን

ይህ እንዴት እንደሚሆን ነቢዩ ኢሳይያስ ዝርዝር ይሰጠናል። ኢሳይያስ 59፡19-60፡5 ስዕሉን ያቀርባል። እስቲ ተራ በተራ እንመልከታቸው።

‹‹በምዕራብ ያሉት የእግዚአብሔርን ስም ይፈራሉ፤ በፀሐይ መውጫ ያሉት ለክብሩ ይገዛሉ›› (ቁጥር19)። መላው ምድር እስኪፈራና ክብሩን እስኪያይ ድረስ እግዚአብሔር ራሱን ይገልጣል።



‹‹ጠላት እንደ ጎርፍ በሚመጣበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ምልክት ያነሣል›› (ቁጥር 19)። ሐቁ በአሁኑ ጊዜ ጠላት እንደ ጎርፍ መምጣቱ ነው። ካለፉት ጥቂት ዐሥርተ ዓመታት ወዲህ ጠላት፣ ዲያብሎስ በዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲካን፣ ማኅበራዊ ሕይወትን፣ትምህርት ቤቶችን፣ ኮሌጆችን፣ በሴሚናሪዎችና በዩኒቨርስቲዎችን ጨምሮ ጠላት በማንኛውም ብሔራዊ ገጽታ መግባቱን ማየት ይቻላል። እንደ ጎርፍ የመጣው ወደ ዓለም ብቻ ሳይሆን፣ ከሁሉም በላይ ወደ አብያተ ክርስቲያናትም መጥቷል። አብዛኞቻችን ማንም ሲነግረን እስከማያስፈልገን ድረስ ያንን በሚገባ እናውቃለን።

ይህ የእግዚአብሔር ሕዝብና ርስታቸው በወራሪ እንስሳት እንደሚጠቁ በኢዮኤል የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ ነው። በዘመናት ሁሉ ቤተክርስቲያን ታላቅ በሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ ሠራዊት ስትወረር ኖራለች። አንበጣና ኩብኩባ መጥተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ርስት ወና አድርገውታል። ይሁን እንጂ፣ መንፈሱ በመካከላችን እንደሚንቀሳቀስ እግዚአብሔር ይናገራል። ጠላት እንደ ጎርፍ በሚመጣበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ምልክት ያነሣል።

የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያነሣው ምልክት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሰብዓዊ ፍጡርን ከፍ አያደርግም፤ አስተምህሮን ከፍ አያደርግም፤ ተቋምን ከፍ አያደርግም። ወደ ቤተክርስቲያን የመጣው አንድ ነገር ለማድረግ ነው። ኢየሱስ፣ ‹‹የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ... ከእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል›› ብሏል (ዮሐንስ 16፡13-14)። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መግለጥ፣ ከፍ ማድረግ፣ ገናና ማድረግና ማክበር ነው።

በጥንት ዘመን አንድ ሠራዊት ሲጠቃና መሸነፍ አፋፍ ላይ ሲደርስ፣ አዛገፉ ምልክት የሚይዘውን ሰው አንድ ከፍታ ቦታ ላይ ቆሞ ምልክቱን እንዲያነሣ ያዝዘው ነበር። ሠራዊቱ ውስጥ ያሉ ወታደሮች ወደ ላይ ከፍ ያለውን ምልክት ሲያዩ ምልክቱ በታየበት ቦታ ሥር መሰብሰብ እንዳለባቸው ያውቃሉ።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በቤተ ክርስቲያን እየሆነ ያለው ይኸው ነው። አማኞች መጸለይ ሲጀምሩ መንፈስ ቅዱስ ምልክቱን ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ያደርጋል። የመወረር፣ የመጠቃትና በመጨረሻም የመሸነፍ ስጋት ውስጥ በማንኛውም የቤተክርስቲያን ክፍል ያሉ የተጨነቁ የእግዚአብሔር ሕዝብ ድምፃቸውን በጸሎት ሲያነሡ ወደ ላይ ከፍ ያለውን ምልክት አይተዋል። ይህ ቤተ እምነት፤ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

እግዚአብሔር የተበታተነ ሕዝቡን እንደ ገና ሰብስቧል። የኢሳይያስ 59፡20 አንኳር ሐሳብም ይኸው ነው። ‹‹አዳኝ ወደ ጽዮን፣ ኃጢአታቸውንም ወደ ተናዘዙት ወደ ያዕቆብ ቤት ይመጣል ይላል እግዚአብሔር።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ጌታ ይመለሳሉ፤ ጌታም ወደ ህዝቡ ይመለሳል። መናዘዝና ወደኋላ ካፈገፈግንበት፣ ከሥጋዊነታችን፣ ለራሴ እበቃለሁ ከማለታችን፣ ከወገንተኛዊነታችንና ከአመፃችን መመለስ ይኖርብናል። ከኃጢአታችን ወደ አዳኙ ስንመለስ፣ አዳኙ ወደ ጽዮን መመለሱን እናያለን። መመለስና መታደስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መጥቷል።

በዚሁ አውድ እግዚአብሔር እንዲህ እያለ ነው -

> በእኔ በኩል ከእነርሱ ጋር ያለኝ ቃል ኪዳን ይህ ነው
> ይላል እግዚአብሔር በአንተም ላይ ያለው መንፈሴ፣
> በአፍህ ያስቀመጥሁት ቃሌ ከአፍህ፣ ከልጆችህ
> አፍ፣ ከዘር ዘሮቻቸውም አፍ ከዛሬ ጀምሮ እስከ
> ዘላለም አይለይም ይላል እግዚአብሔር። ኢሳይያስ
> 59፡21

መመለስና መታደሱ ከፊል ወይም ጊዜያዊ አይደለም። የተሟላና ዘላቂ ነው። ያለ ማንም አጽናኝ ለብዙ ምዕተ ዓመቶች እንደ ሙት ልጆች ሲኖሩ ለነበሩት የእግዚአብሔርን ሕዝብ በተመለከተ ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያመጣው የመጨረሻ መመለስና መታደስ ነው። ይህ መመለስና መታደስ ዘላለማዊ ነው።



## ጨለማን ማስወገድ

ምዕራፍ 60 አዲስ ምዕራፍ ቢሆንም ትንቢቱ ያለፈው ቀጣይ መሆኑን እምናለሁ - በብርሃንና ጨለማ መካከል ያለውን ግሩም ንጽጽር እንመለከታለን። መልእክቱ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ማለትም ለጽዮን ነው።

> ብርሃንሽ ወጥቶአልና ተነሺ አብሪ፤ የእግዚአብሔርም
> ክብር ወጥቶልሻል። እነሆ ጨለማ ምድርን፣ ድቅድቅ
> ጨለማም ሕዝቦችን (ምድርን) ይሸፍናል፤ ነገር ግን
> እግዚአብሔር ወጥቶልሻል፤ ክብሩንም ይገልጥልሻል።
> ኢሳይያስ 60፡1-2

በአሁኑ ጊዜ ያለነው እዚህ ነው። ጨለማ ምድርን ሸፍኗል፤ የከፋ ጨለማ የምድር ሕዝቦችን እየሸፈነ ነው። ሐቁን እንቀበል። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ተናግሮለታል፤ ከዚያ በፊት በፍጹም ይኖራል ብለን ያልገመትነው የጨለማ ዓይነት የምድር ነዋሪዎችን እየዋጠ ስለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎች ይኖረናል። ሆኖም፣ ከጨለማው መካከል እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው መልእክት፣ የጌታ ክብር እኛ ላይ እየወጣ መሆኑ ነው።

ንጽጽሩ ይኸው ብርሃኑ ይበልጥ እየደመቀ ነው፤ ጨለማው ይበልጥ እየጨለመ ነው። ሙሉ በሙሉና በማያዳግም ሁኔታ መንገዶቹ ወደሚለያዩበት ነጥብ ደርሰናል። ከአሁን ጀምሮ ገለልተኝነት አያዋጣም። ኢየሱስ፣ ‹‹ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል›› ብሏል (ማቴዎስ 12፡30)።

እያንዳንዳችን ውሳኔ ማድረግና መስጠት ይኖርብናል። ብርሃንን እንወዳለን? እንግዲያውስ ወደ ብርሃን እንምጣ። ወደ ብርሃን መምጣት የማንፈልግ ከሆነ ምክንያቱ ሥራችን ክፉ መሆኑ እንደ ሆነ ኢየሱስ ተናግሯል። ብርሃን ወደ ዓለም መጥቷል፤ ሰዎች ግን ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ(ዮሐንስ 3፡19 ይመ)። እያንዳንዳችን ፊት የተቀመጠ ምርጫ ይህ ነው። በብርሃን እመላለሳለሁን? ከብርሃንና ብርሃን በምድር ላይ ካለው ዓላማ ጋር እወግናለሁን? ወይስ በምድር ሁሉ ፊት ጨለማው እየበረታና እየሰፋ ሲሄድ ጨለማው ውስጥ እደበቃለሁ?

ይበልጥ እየሰፋ የሚሄደው ልዩነትን በተመለከተ እውነትን እንደሚያሳዩ የማምንባቸው ሦስት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ልሰጣችሁ እፈልጋለሁ። የመጀመሪያው ዘፍጥረት 15:5 ነው። አብርሃም ልጅ እንደሚሰጠው የገባለትን ቃል በተመለከተ እግዚአብሔርን እየለመነ ነበር፤ ምክንያቱም በዚያ ጊዜ አንድም ልጅ አልነበረውም። እግዚአብሔር በጨለማ ወደ ውጭ እንዳወጣውና በሰማይ ያሉ ከዋክብትን እንዳሳየው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ‹‹ከከቦቹን ቁጠር›› አለ እግዚአብሔር። ‹‹ዘሮችህም እንዲሁ ይሆናሉ። አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ‹‹እርሱም ጽድቅ አድርጎ ቆጠረለት›› በማለት ቁጥር 6 ይነግረናል።

ይህ እኛንም እንደሚመለከት አንድ ጊዜ እግዚአብሔር በስብከት መካከል በመገለጥ አሳይቶኝ ነበር። ምክንያቱም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የአብርሃም ልጆች እንደ ሆንን የገላትያ መልዕክት ይነግረናል። (ገላትያ 3:7ይመ)።

እውነት ለመናገር ብዙ ጊዜ ከዋክብትን ልብ አንላቸውም። ይሁን እንጂ፣ ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ፣ ጨረቃ በሌለችበት ምሽት፣ ምንም ዓይነት ሰው ሠራሽ ብርሃን በጠፋ ጊዜ ከዚያ በፊት ካያችሁት የበለጠ ከዋክብት ያበራሉ። በዘመኑ ማብቂያ የሚሆነው በትክክል ይኸው ነው። ጨለማ ምድርን፣ ድቅድቅ ጨለማም ሕዝቦችን ሲሸፍን ሌሊቱ ይበልጥ እየጨለመ ሲሄድ፣ የአብርሃም ልጆች በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት እንደ ከዋክብት በክብራቸው ያበራሉ። እየሄድን ያለነው ወደዚያው ነው።

ሁለተኛው ቃል ያለው ማሕልየ መሐልይ ውስጥ ነው። እዚህ ላይ ሙሽራዋ በክብር ስትመጣ ይታያል፤ ‹‹እንደ ንጋት ብርሃን ብቅ የምትል፣ እንደ ጨረቃ የደመቀች፣ እንደ ፀሐይ ያበራች አላማ ይዞ በሰልፍ እንደ ወጣ ሰራዊት ግርማዋ የሚያስፈራ ይህች ማን ናት?›› (ማሕልየ መሐልይ 6:10)። ዓለም በመገረም ይዋጣል። እንደዚህች ያለች ቤተክርስቲያን አይቶ አያውቅም። እንደ ንጋት ብቅ የምትል ይህች ማን ነች? በሌሊቱ ጨለማ ውስጥ እንደ ጨረቃ ውብ ናት። የጨረቃ ሥራ የፀሐይን ክብር ማንጸባረቅ ነው። ጨረቃ እንደምትጎድል፤



እንደምትሞላ ሁላችሁም ታውቃላችሁ። አንዴ ይደክማል፤ ሌላ ጊዜ ይደበዝዛል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ደክማም በርትታም ነበር። እንደ ሙሉ ጨረቃ በምትመጣበት ጊዜ ግን የልጁን ክብርና ድምቀት ስታንጸባርቅ ዓለም የቤተ ክርስቲያን ሙሉ ገጽታ ያያል። የጽድቅ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጧ የሚያኖረው ሥልጣን ይኖራታል። እርሟ እንደ ያዘ ሰራዊት የምታስፈራ ትሆናለች። የአመጽና የጨለማ ኃይሎችን፣ ኃጢአትና ሰይጣንን የምታስፈራ እንደዚህች ያለች ቤተክርስቲያን ማን አይቷል? የሰይጣን ኃይሎችን የምታንቀጠቅጥና የምታባርር ቤተክርስቲያን ትመጣለች።

ዲያብሎስን በተመለከተ አንድ እግዚአብሔር ያሳየኝ ነገር ከሌሎች መልዕክቶች ሁሉ ይበልጥ የሚፈራው መልዕክት መኖሩን ነው። ይኸውም ወደ ፊት ቤተ ክርስቲያን የምትሆነውንና ዲያብሎስ ላይ የምታደርገውን የሚመለከት መልዕክት ነው። ከማንኛውም ነገር ይልቅ ዲያብሎስ ይበልጥ ይህን እውነት እንደሚዋጋ አምናለሁ።

በብርሃንና በጨለማ መካከል ይበልጥ እየሰፋ የሚሄደውን ልዩነት የሚያሳየን ሦስተኛው ጥቅስ ያለው የዩሐንስ ራእይ ውስጥ ነው። በሌላ መንገድ ቀርቦ የነበረው እውነት ነው። የመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍና ወደ መጨረሻው የተቃረበው ቁጥር እንዲህ ይላል -

> እንዲህም አለኝ፤ ጊዜው ስለ ደረሰ የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው፤ አመፀኛው በአመፁ ይቀጥል፤ ርኩሱም ይርከስ፤ ጻድቁም ይጽደቅ፤ ቅዱስም ይቀደስ። እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ዋጋዬ በእኔ ዘንድ አለ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍላቸዋለሁ።
> የዩሐንስ ራእይ 22:10-12

ጊዜው በደጅ ነው። ኢየሱስ ቶሎ ይመጣል። መልእክቱ ምንድነው? አድምጡ - አስፈሪ መልእክት ነው። አመፀኛ የሆነ ሰው አሁንም ጨምሮ ያምፅ። ርኩስ የሆነ ሰው አሁንም ጨምሮ ይርከስ። ጻድቅ ሰው አሁንም ጨምሮ

ይጽደቅ። ቅዱሱ አሁንም ጨምሮ ይቀደስ። አንድ ቦታ ላይ አትሆኑም፤ ወይ ከፍ ትላላችሁ ካልሆነም ዝቅ ትላላችሁ ከእንግዲህ አንድ ቦታ ረግቶ መቆም፣ ወይም ገለልተኛ መሆን በፍጹም አይቻልም። ነጻ መውጣት የምትፈልጉ ከሆነ፣ ባላችሁበት ሁኔታ ማምረር ይኖርባችኋል። ሰባኪው እንዲያመርላችሁ አትጠብቁ፤

አንድ ጊዜ በችግሩ እንዳማክረው የጠራኝን ሰው አስታውሳለሁ። ችግሩ ከፖርኖግራፊ ጋር የተያያዘ ነበር። በአንድ በጣም በታወቀ ቤተ እምነት የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች መሪ ነበር፤ ሆኖም ፖርኖግራፊ እስራት ሆኖበት ነበር። የሚኖርበት ክፍል በፖርኖግራፊ መጽሔቶች የተሞላ እንደሆነና ከቆሻሻ ፊልሞች መራቅ እንዳልቻለ ይናገራል። እንዴት ንስሐ እንደሚያደርግና እንዴት ነጻ እንደሚወጣ ነገርኩት። በሚቀጥለው ዓመት እንደ ገና በዚያው አካባቢ ነበርኩ፤ ይኸው ሰው ስልክ ደውሎ ስለዚያው ችግሩ ነገረኝ። እኔም፣ ‹‹ዕድል ነበረህ። ባለፈው ዓመት የነገርኩህን ተግባር ላይ ያላዋልከው ለምንድነው?›› አልኩት። መጥቶ ሊያገኘን ዝግጁ እንደ ሆነ ተናገረ። ቀጠሮ ያዝኩ፤ ግን ቃሉን አልጠበቀም። በሚቀጥለው ቀን ደወለልኝና፣ ‹‹ቃሌን ባለ መጠበቁ አዝናለሁ፤ ቆሻሻ ፊልም ወደሚታይበት ቦታ ሄጄ ነበር›› አለኝ።

ምን እንዳልኩት ታውቃላችሁ? ‹‹በዚያው ቀጥል ምክንያቱም ረጅም ጊዜ የለህም›› ነበር ያልኩት። የረከሰ፣ የበለጠ ይርከስ፤ ምክንያቱም ገና አልበቃውም። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው። ያንን ቃል በዚያ መልኩ አይቼው አላውቅም ነበር፤ ግን ያንን ሰው በተመለከተ ያለጥርጥር ትክክል ነበር። ርኩሰት ውስጥ ያለሰው ለማስመሰል ነጻ መውጣት እፈልጋለሁ ይላል።

አመፀኞች ከሆናችሁ፣ እስኪያንገፈግፋችሁ ድረስ አምፁ። ርኩስ ከሆናችሁ የሚበቃችሁን ያህል አልሆናችሁምና ጨምራችሁ ርከሱ። ጻድቅ ከሆናችሁ፣ በጽድቃችሁ አትተማመኑ። ይበልጥ ጽደቁ። ቅዱስ ከሆናችሁ፣ የበለጠ ቅዱስ ሁኑ። ቤተክርስቲያን ውስጥ ጥሪ ሲቀርብ ወደ ፊት በመሄድ፣ ጥቂት የጸሎት ቃሎችን በማለትና የፓስተሩን እጅ



ያገኙት ድነት ወደ ላይ ወደ ታች የማይል ቋሚ እንደ ሆነ ማመንን የመሰለ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያታልል የለም። ይህ አሻንጉሊት ድነት ነው፤ ድነት ወደ ፊት ወደ ኋላ የማይል የረጋ ነገር አይደለም፤ ድነት የሕይወት ጉዞ ነው።

ምሳሌ 4፡18 እንዲህ ይላል፤ ‹‹የጻድቃን መንገድ ሙሉ ቀን እስኪሆን ድረስ ብርሃኑ እየጎላ እንደሚሄድ የማለዳ ውጋጋን ነው።›› ኢዮብ 17፡9 እንዲህ ይላል፤ ‹‹ጻድቃን ግን በያዙት መንገድ ይጸናሉ፤ ንጹሕ እጅ ያላቸውም እየበረቱ ይሄዳሉ።››

ድነት ምን ማለት መሆኑን አስመልክቶ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቤተክርስቲያን አዘውታሪዎች የተሳሳተ ሐሳብ ይዘዋል። ለዚህ ስሕተታቸው በተወሰነ ደረጃ እኔም ኃላፊነቱን እወስዳለሁ፤ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይጣጣም የድነት መልእክት ሰብስቤአለሁ። ድነት ለዓመታት የቤተክርስቲያን አባሎች ስለ ነበርን የምንቀበለው ሽልማት አይደለም። እያደገ የሚሄድ የሕይወት ጉዞ ነው። በጽድቅ መንገድ የማንሄድ ከሆነ፣ ብርሃኑ በመንገዳችን ላይ ይበልጥ እያበራ የማይሄድ ከሆነ እንስታለን። የጽድቅ መንገድ ፍጹም እስከሆነው ቀን ድረስ ይበልጥ እየበራ እንደሚሄድ መብራት ነው።

## የዚህ ክብር ውጤት

በክብር የምትገለጠው ቤተክርስቲያን ውጤት ምን ይሆናል? ከኢሳይያስ 60 የምንመለከታው ሦስት ጥቅሶች ለዚህ መልሱን እንደሚሰጡን አምናለሁ። ‹‹ሕዝቦች ወደ ብርሃንሽ፣ ነገሥታቶችም ወደ ንጋትሽ ጸዳል ይመጣሉ›› (ቁጥር 3)።

ሕዝቦችና ገዦች ወደ ቤተክርስቲያን ይመለሳሉ። አብዛኞቹ የዘመናችን ገዦች የሚያደርጉት እንደ ጠፋባቸው ታውቃላችሁ? ለችሮቻቸው መፍትሔ የላቸውም፤ ይህን እነርሱም ያውቁታል።

ቤተክርስቲያን መሆን ያለባትን ከሆነች በፊታችን ባለው ጨለማ ጊዜ መፍትሔ ሲጠይቁን የአሕዛብ ገዦች በየደጃችን እንደሚሰለፉ አምናለሁ። ያ ደግሞ እየመጣ ነው። ለዚያ ዝግጁ ለመሆን በጸሎት መበርታት አለብን።

ዳንኤልና ዮሴፍ በጸሎት የተጉና የአሕዛብ ገዦች ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ ሰዎች ነበሩ። የጭንቅ ጊዜ ሲገጥማቸው ሁለት ታላላቅ የአሕዛብ መንግሥታት

ከተፈጥሮአዊ በላይ የሆነ ጥበብ ወደ ነበራቸው ወደ እነዚህ አይሁዳዊያን ወጣቶች ሄደዋል። ከእግዚአብሔር ዘንድ መልሱ ነበራቸው - ይህም በእነዚያ መንግሥታት ውስጥ ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ አሰጣቸው። የዳንኤል አምላክና የዮሴፍ አምላክ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንም አምላክ ነው። እንደ ዳንኤልና እንደ ዮሴፍ መልስ ማግኘት እንድንችል ወደ ጌታ መምጣትና ከዚያም ለመሪዎቹ መልስ ማድረስ አለብን።

ከኢሳይያስ 60፡4 ወጣቶች እንደሚመጡ እናነባለን። ለቤተክርስቲያን እንዲህ ተብሎ ተነግሮአታል፤ ‹‹ቀና በዪ፣ ዙሪያሽን ተመልከቺ፤ ሁሉም ተሰብስበው ወደ አንቺ ይመጣሉ፤ ወንዶች ልጆችሽ ከሩቅ፣ ሴቶች ልጆችሽም በዕጥፍ ወደ አንቺ ይመጣሉ።››

በመጨረሻ ቀኖች ትንቢት ውስጥ ወጣቶችን በተመለከተ ብዙ ተነግሮአል። የሐዋርያት ሥራ 2፡17 ተመልከቱ፤ ‹‹በመጨረሻው ቀን መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ጎልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ።›› እጅግ በጣም ብዙ ወጣቶች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እየመጡ ነው። ከአሁኑ ተጀምሯል። በደቡባዊ የዩናይትድ ስቴትስ የባሕር ዳርቻ አራትና አምስት ሺህ ወጣቶች በአንድ ጊዜ ውሃ ውስጥ በመስጠም ሲጠመቁና በኢየሱስ ክርስቶስ ማመናቸውን ሲመሰክሩ እየሰማን ነው።

እነዚህ ወጣቶች ሲመጡ መልስ ሊኖረን እንደሚገባ በጥልቅ ልቤ ውስጥ ተቀምጧል። እኛ የምናውቀው ዓይነት ተቃዋሚ ቤተክርቲያንን ይቀላቀላሉ ብዬ አላምንም። ጸሎቴም፣ እንደዚያ ከማድረግ እግዚአብሔር ይጠብቃቸው! የሚል ነው። እኔና እናንተ ለብዙ ዓመታት እንደ ነበርነው በድን ወደ ሆነ ተቃዋሚ ቤተክርስቲያን ከመምጣት ይልቅ ተግባራዊ የሚያደርጉት የክርስትና ሕይወትና ራስን የመግዛት አርዓያ የሚሆናቸው ነገር ልንሰጣቸው ኃላፊነት አለብን።

የኢሳይያስ 60 አምስተኛው ቁጥር ቤተክርስቲያን ላይ ምን



እንደሚሆን ይነግረናል። ይህ በጣም የምወደው ቃል ነው። ‹‹ከዚያም ታያለሽ...›› ከብዙ መቶ ዓመታት መታወር በኋላ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ማን መሆኑንና ምን እያደረገ እንደ ሆነ እያየችው ነው። የሚቀጥለው ደግሞ ቤተክርስቲያን አብራ መንቀሳቀሷ ነው(ቁጥር 5-7ይመ)። ከብዙ የተለያዩ አካባቢዎች እጅግ በጣም ብዙ ትንንሽ ምንጮች እየመነጩና ወንዝ የሚሆን አንድ ታላቅ ምንጭ ለመሆን እየተሰባሰቡ ነው። ይህ ወንዝ በጣም ትልቅ ወንዝ ይሆናል። ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ እንድትሞላ የሚያደርግ ታላቅ ውቅያኖስ ለመሆን ወደ ፊት ይገሰግሣል።

እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ልሳንን የመተርጎም ስጦታን ሲሰጠኝ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቅሁ ገና 48 ሰዓት አልሆነውም ነበር። በማይታወቅ ልሳን ተናግሬ ነበር፤ ምን እያደረግሁ እንደ ነበር ሳስተውለው መተርጎም ጀመርኩ። ምን እንደ ነበር አላወቅሁም ነበር፤ ይሁን እንጂ የምናገራቸውን ቃላት እየመረጥሁ እንዳልነበር አውቅ ነበር። ልክ ትናንት ማታ የተፈጸመ ያህል ቃላቱን በሚገባ አስታውሳቸዋለሁ። እንደ ታናሽ ምንጭ ይሆናል፤ ምንጩ ወንዝ ይሆናል፤ ወንዙ ታላቅ ወንዝ ይሆናል፤ ታላቁ ወንዝ ባሕር ይሆናል፤ ባሕር ደግሞ ታላቅ ውቅያኖስ ይሆናል።

ይህን አምናለሁ። በዚያ ጊዜ ስለ መንፈሳዊ መነቃቃት ብትነግሩኝ ስለ ምን እየተናገራችሁ እንደ ሆነ እንኳ አላውቅም ነበር። የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮአዊ ዕውቀት አልነበረኝም፤ የወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት መሠረትም አልነበረኝም። እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ በግሌ ሲናገረኝ ምን እንደሚያደርግ ነግሮኝ ነበር። ከብዙ አሥርት ዓመታት በኋላ ታላቁ ወንዝ ሲፈስ የማይበት ደረጃ ላይ ነኝ።

ግን ይህ የመጨረሻ አይደለም። ታላቁ ወንዝ ባሕር ይሆናል፤ ባሕሩም እጅግ ታላቅ ውቅያኖስ ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፤ ‹‹ከዚያም ታያለሽ ታብረቀርቂያለሽ›› (ኢሳይያስ 60፡5)። ወደ ላይ ከፍ ያለውን የኢየሱስ ክርስቶስ ምልክት የሚያይ ሁሉ፣ ከትንንሽ ጥግ ቦታዎቹ፣ ከትንንሽ

ኮረብቶቹ፣ ከየትንንሽ ሸለቆዎቹ ይመጣና አንድ ታላቅ ምንጭ ለመሆን ይሰበሰባል።

በመጽሐፉ መደምደሚያ ላይ ሕዝቅኤል ከቤተ መቅደሱ ስለሚወጣው የሕይወት ውሃ በየ ጊዜ መጀመሪያ እሽክ ቁርጭምጭሚት ድረስ ነበር። አንድ ሺህ ክንድ ያህል ወደ ፊት ሲሄድ ጉልበት ድረስ ሆነ። ሌላ አንድ ሺህ ክንድ ላይ ወገብ ድረስ ሆነ። በመቀጠል አንድ ሺህ ክንድ ወደ ፊት ሲሄድ ውሃው ለመዋኘት የሚያስችል፣ መሻገር የማይቻል ወንዝ ሆነ። ቤተ ክርስቲያን መዋኘት የሚያስችል ጥልቅ ውሃ ላይ ስትደርስ፣ ማንም አያልፋትም። ከእንግዲህ ቤተክርስቲያን የማትጠቅም ዘመን ያለፈባት አትሆንም። ለመዋኘት እስኪቻል ድረስ ውሃው ጥልቅ ሲሆንልን፣ ዓለም እዚህ እንዳለን ያውቃል።

መነጠቅን በተመለከተ ምን እንደሚሰማኝ ታውቃላችሁ? የእኛ አለመኖር ዓለምን ቅር የሚለው ይመስለኛል። እስከዚያ ድረስ መነጠቅ መፈጸሙን ዓለም እንደሚያውቅ እጠረጥራለሁ። ከዚህ ስንሄድ ግን ዓለም ባዶነት ይሰማዋል። ይሁ የእኔ እምነት ነው።

በማያያዝ ቁጥር 5፣ «በባሕሮች ያለው ሀብት ወደ አንቺ ይመጣል፤ የነገሥታትም ብልጥግና የአንቺ ይሆናል» ይላል። የአለማዊው ዓለም ብልጥግና ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል። ለእርሱ ክብር ሕዝቡ ሦስት ትልልቅ ነገሮች እንዲገነቡ እግዚአብሔር ወስኖ ነበር። የመጀመሪያው የሙሴ መገናኛ ድንኳን ነው። ሁለተኛው የሰለሞን ቤተመቅደስ ነው። ሦስተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ናት። ሌሎች ግንባታዎች መኖራቸውንም አውቃለሁ፤ ግን የትኛውም እነዚህ ሦስቱ ምድብ ውስጥ አይገባም። ከእነዚህ እያንዳንዱ መለኮታዊ ምሳሌ ነበረው፤ እያንዳንዱ መለኮታዊ ስጦታ ተደርጎለታል፤ እያንዳንዱ መለኮታዊ ዓላማ ነበረው።

እስቲ ለአፍታ ቢሆን የሰለሞን ቤተ መቅደስን ለማየት ጊዜ እንውሰድና ምን ማለቱ እንደ ሆነ ላሳያችሁ። ከዚያ ለቤተክርስቲያን የምጸልየውን ተመሳሳይነት እንመለከታለን።



## ቤተመቅደስን መገንባት

1ዜና መዋዕል 28 ታላቁ ቤተ መቅደስን ለመገንባት ዝግጅት ማድረግ በተያያዘ ዳዊት የተናገረውን ያቀርባል። ምን ያህል እግዚአብሔር ሥራውን እንደ መራው ለማሳየት ከዚህ ምንባብ አንድ ክፍል ለማየት እፈልጋለሁ።

> ከዚያም ዳዊት የቤተ መቅደሱን መመላለሻ፣ የሕንፃውን፣ የዕቃ ቤቶቹን፣ ፎቆንና የውስጥ ክፍሎቹን እንዲሁም የማስተሰርያውን ቦታ ንድፍ ለልጁ ለሰሎሞን ሰጠው። ደግሞም መንፈስ ቅዱስ በልቡ ያሳደረውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አደባባይ፣ በዙሪያው ያሉትን ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ዕቃ ቤቶችና የንዋየ ቅዱሳቱን ግምጃ ቤቶች ንድፍ ሁሉ ሰጠው። ቁጥር 11፡12

ዳዊት የቤተ መቅደሱን ንድፍ ያገኘው በመለኮታዊ መገለጥ ከእግዚአብሔር መንፈስ ነበር። ቀጥላችሁ አንብቡ።

> እንዲሁም የካህናቱንና የሌዋውያኑን አመዳደብ፣ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎት ሥራና ለአገልግሎቱ ስለሚጠቀምባቸው ዕቃዎች ሁሉ መመሪያ ሰጠው። ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉትን የወርቅ ዕቃዎች ሁሉ መጠን፣ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉትን የብር ዕቃዎች ሁሉ መጠን አሳወቀው፤ እንደየመቅረዙ አገልግሎት ዐይነት ለወርቁ መቅረዞችና ለቀንዲሎቻቸው የሚሆነውን እያንዳንዳቸውን የወርቅ መጠን፣ ለብሩ መቅረዞችና ለቀንዲሎቻቸው የሚያስፈልገውን የእያንዳንዳቸውን የብር መጠን። ቁጥር 13-15

ሌላው ቀርቶ ለአንዳንድ ነገሮች መሥሪያ የሚውል የወርቅና የብር መጠን በትክክል ለዳዊት ተነግሮት ነበር።

በእያንዳንዱ ሕብስተ ገጽ ጠረጴዛ የሚያስፈልገውን የወርቅ መጠን፣ ለእያንዳንዱ የብር ጠረጴዛ የሚያስፈልገውን የብር መጠን፣ በሹካዎቹ፣ ለጉድጓዳ ሳሕኖቹ፣ ለማንቆርቆሪያዎቹ የሚያስልገውን ንጹህ የወርቅ መጠን፣ ለእያንዳንዱ የብር ሳሕን የሚያስፈልገውን የብር መጠን፣ ለዕጣኑ መሠዊያ የሚሆነውን የጠራ ወርቅ መጠን እንዲሁም ክንፎቻቸውን ዘርግተው የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት የሚሸፍኑትን ከወርቅ የተሠሩትን የኪሩቤል ሠረገሎች ንድፍ ሰጠው። ዳዊትም ‹‹ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ባለው በእግዚአብሔር እጅ በጽሑፍ ተገለጠልኝ፤ የንድፉንም ዝርዝር እንድረዳ ማስተዋልን ሰጠኝ›› አለ። ቁጥር 16-19

ሹካዎች እንኳ ሳይቀሩ ንጹሕ ወርቅ የነበሩበት ምን ዓይነት ድንቅ ሕንፃ ነው። ንድፉ ሁሉ ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ ሁኔታ በእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠ ነበር። የእያንዳንዱ ዕቃ ትክክለኛ ቅርጽ፣ ንድፉ፣ ክብደቱና እያንዳንዱን ዕቃ ለመሥራት የሚያስፈልገው የወርቅ ወይም የብር ትክክለኛ መጠን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ነበር።

ንድፉን ካገኘ በኋላ ዳዊት የሚያስፈልገውን ነገር ማጠራቀም ጀመረ።

ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ለመላው ጉባኤ እንዲህ አለ፤ ‹‹እግዚአብሔር የመረጠው ልጄ ሰለሞን ገና ወጣትና ልምድም የሌለው ነው። ይህ ታላቅ ሕንፃ የሚሠራው ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር አምላክ በመሆኑ፣ ሥራው ከባድ ነው። እኔም ያለኝን ሀብት ለአምላኬ ቤተ መቅደስ የሚያስፈልገውን በብዛት አዘጋጅቻለሁ። 1ዜና 29፡1-2



እግዚአብሔር ዳዊትን የወደደበት አንዱ ምክንያት በሙሉ ልቡ መንቀሳቀሱ ነው። ዳዊት አንድ ነገር ማድረግ ከጀመረ፣ በግማሽ ልቡ አያደርገውም። አምልኮው ከሙሉ ልብ ነበር፤ ስጦታው ከሙሉ ልብ ነበር፤ መቀደሱ ከሙሉ ልብ ነበር። እርሱ እንዲህ አለ -

እኔም ያለኝን ሀብት ለአምላኬ ቤተ መቅደስ ለወርቁ ሥራ ወርቁን፣ ለብሩ ሥራ ብሩን፣ ለናሱ ሥራ ናሱን፣ ለብረቱ ሥራ ብረቱን፣ ለዕንጨቱ ሥራ ዕንጨቱን እንዲሁም ለፈርጥ የሚሆነውን መረግድ፣ ኬልቄዶን፣ ልዩ ልዩ ኅብር ያላቸውን የከበሩ ድንጋዮች፣ ማናቸውም ዐይነት የሚያምር ድንጋይና ዕብነ በረድ ይህን ሁሉ በብዛት አዘጋጅቻለሁ። ቁጥር 2

ይህን ማንበባችሁ ሀብታምነት እንዲሰማችሁ አድርጓልን? ያን ያነበብኩ ጊዜ ምን ዐይነት አስደናቂ አምላክ እንዳለን አስቤአለሁ። በእግዚአብሔር ዘንድ ስስት፣ ንፍገት፣ የአእምሮ ጠባብነት የለም። እርሱን በተመለከተ ማንኛውም ነገር እጅግ ብዙና ክብር ያለው ነው። ዳዊት የሰጠው የራሱ የሆነውን ነበር፤ ‹‹ለአምላኬ ቤት ካዘጋጀሁት የበለጠ ሰጥቻለሁ፤ የእኔ የግሌ ከሆነው ሀብት ሦስት ሺህ የወርቅ መክሊትና የኦፊር ወርቅ ለቅዱሱ ቤት ሰጥቻለሁ›› (3-4)።

ዳዊት በነበረበት ዘመን አንድ ንጹሕ የወርቅ መክሊት በዚህ ዘመን በትንሹ 800,000 ዶላር እንደሚያወጣ መገመት እንችላለን። ዳዊት የራሱ ሀብት ከሆነው 3,000 መክሊት ወርቅ ሰጠ። ይህ 2.4 ቢሊዮን ዶላር ያህል ነው። ያንን በተመለከተ ተገርማችሁ ታውቃላችሁ? ሕይወትን የጀመረው እንደ አንድ ትንሽ እረኛ ልጅ ነበር፤ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር በረከት የተነሣ በቢሊዮን ዶላር ወርቅ መስጠት ችሏል - እንግዲህ ይህ ሁሉ የብሩን ዋጋ ሳንጨምር ነው።

ከዚያም በፈቃደኝነት የሰጡ ሰዎችን አበረታታ። 5000 መክሊት ወርቅ ሰበሰቡ (ቁጥር7)። ይህም ተጨማሪ ቢሊዮን መሆኑ ነው። ሌሎች ነገሮችን ማለት ብሩንና የከበረ ድንጋዩን፣ ከውጭ የመጡትን የሊባኖስ ዝግባና ለሕንፃው የተጠረቡ ድንጋዮችን የእጅ ሥራዎችና ፈርጦችን ዋጋ ብታሰሉ ወጪው ከግምት በላይ

ይሆንባችኋል።

ምንም ቁጥ ቁጥ አልነበረም። ምንም ነገር ሁለተኛ ደረጃ መሆን አልነበረበትም። በትክክለኛው ንድፍ መሠረት እያንዳንዱ ነገር ጥራት ያለው ነበር። ከትንሹ ጀምሮ እስከ ትልቁ ነገር የሚያስፈልገው ሁሉ ተዘጋጅቶ ነበር። ለእያንዳንዱ የወርቅ መቅረዝ፣ ለእያንዳነዱ የወርቅ ሹካ፣ ለእያንዳንዱ የወርቅ ሳሕን፣ ለእያንዳንዱ ጎድጓዳ ሳሕን የሚያስፈልገው ትክክለኛ የወርቅ መጠን ተሰጥቶ ነበር፤ በመመሪያው መሠረት ተሠርቶ ነበር። ለምን? ምንያቱም ከዓላማው የተነሣ ነበር፤ ዓላማውም የእግዚአብሔር ክብር ነበር።

‹‹አካል›› መገንባት

ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ስዕል ነው። ወደዚህ ዘመን ፍጻሜ ስንቃረብ እግዚአብሔር ዓለም አይቶ የማያውቀውን ታላቅ ሕንፃ ያጠናቅቃል። የሰለሞንን ቤተ መቅደስ ፋይዳ ቢስ ያደርገዋል። ይህ ምን ዓይነት ሕንፃ ነው? የክርስቶስ አካል ነው።

በዚህ ትውልድ ዘመን ሕንፃውን ማጠናቀቅ የእግዚአብሔር ዓላማ እንደ ሆነ አምናለሁ። ያም ማለት የሰለሞንን ቤተ መቅደስ ለማጠናቀቅ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሀብት እንዳስፈለገ ሁሉ፤ በምድር ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ሥራ ለማጠናቀቅም የእግዚአብሔር ሕዝብ ሀብት ያስፈልጋል ማለት ነው።

በዚህ ጊዜ ከመንፈሳዊው ወደ ቁሳዊው ተሸጋግረናል። ወይስ እንደዚያ ነው እንዴ? ለመሆኑ ምን ታስባላችሁ? ስለ ወርቅና ብር መነጋገር መንፈሳዊነት እንዳይደለ ታስባላችሁ? እንደዚያ ከሆነ፣ ከሁሉም የበለጠ መንፈሳዊ ያልሆነ መጽሐፍ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ሊሆን ነው፤ አደባባዮቿ በወርቅ የተለበጡ በመሆናቸው አዲስቷ ኢየሩሳሌም ከሁሉም የበለጠ መንፈሳዊ ያልሆነች ቦታ ልትሆን ነው!

አድምጡ፣ የሰለሞንን ቤተ መቅደስ ለማጠናቀቅ የእግዚአብሔር ሕዝብን ሀብት እንደ ጠየቀ ሁሉ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን



ለማጠናቀቅም የእግዚአብሔር ሕዝብን ሀብት ይጠይቃሉ። ለቤተ መቅደሱ እንደ ሰጡ ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለቤተ ክርስቲያን በልግስና ለመስጠት ያስችላቸዋል።

የአሜሪካ ዜጋ ከሆንኩበት ምክንያት አንዱ ይህ እንደ ሆነ ታውቃላችሁ? ልትስቁ ትችላላችሁ፤ ግን እውነቴን ነው። በአንጻራዊ መልኩ ለዩናይድ ስቴትስ አዲስ የሆንኩ አንድ የብሪታንያ ሰው እግዚአብሔር ለአሜሪካ የተለየ ፍጻሜና ዓላማ እንዳለው ድምዳሜ ላይ መድረሴን የምነግራችሁ ከልቤ ነው። ለአንድ የብሪታንያ ዜጋ ያንን ማየት ቀላል አይደለም በምድር ታሪክ አንድም ሕዝብ አግኝቶ ከሚያውቀው በረከት የበለጠ እግዚአብሔር ይህን አገር በሀብት፣ በቴክኒዎሎጂ እንደ ባረከ፣ ሁላችንም እናውቃለን።

እግዚአብሔር ይህን ያደረገው የዩናይትድ ስቴትስን ሀብት ቴክኒዎሎጂና ችሎታ የእግዚአብሔርን ቤት ለማጠናቀቅ ጥቅም ላይ እንዲውል ስለ ፈለገ እንደ ሆነ አምናለሁ። እግዚአብሔር ለዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ያለው ፍጻሜ ይህ እንደ ሆነ ከልቤ አምናለሁ።

ያ እውን እንዲሆን እጸልያለሁ። የዩናይትድ ስቴትስ ሀብት ለእግዚአብሔር መንግስት ማወጅ ጀምሬአለሁ። በቁሳዊ ብልጽግና ተባርኮ ያንን እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ ራእይ ማጣትን የመሰለ አሳዛኝ ነገር የለም። የአብዛኞቹ ወጣቶች ሕይወት አሳዛኝ ገጽታም ይኸው ነው። ሁሉንም ነገር ለግላቸው ያውሉታል፤ ብዙ አግኝተዋል ራእይ ግን የላቸውም። ወገኖቼ፣ ብልጽግና በረከት ነው። ድህነት መርገም ነው። ራእይ የሌለው ብልጽግና ከንቱ ነው። ልሰጣችሁ የምፈልገው ራእይን ነው። አገልግሎታችሁን ለጌታ ለመቀደስ ፈቃደኛ ናችሁ? ከጸሎታችሁ ጋር ጨምራችሁ ሀብታችሁን፣ ስጦታችሁን፣ ችሎታችሁን፣ ለእግዚአብሔር መንግስትና ለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስያን ለመቀደስ ፈቃደኛ ናችሁ? ሌላው ሁሉ ነገር ሲጠፋ፣ ጸንተው ከሚቆሙ ነገሮች አንዱ ይህ ነው።

የማይናወጥ መንግሥት

አሁን ደግሞ መደምደሚያ ላይ አብረን ነቢዩ ሐጌን እንይ። በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት እግዚአብሔር ይህን በግልጽ አመልክቷል፤

> ይህንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ። ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ብሩ የእኔ ነው፤ ወርቁም የእኔ ነው ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ጸባኦት፤ የዚህ የአሁኑ ቤት ክብር ከቀድሞው ቤት ክብር ይበልጣል። ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ጸባኦት፤ በዚህም ቦታ ሰላምን እሰጣለሁ ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ጸባኦት። ሐጌ 2፡7-9

ታላቁን ዓላማ ማየት ቻላችሁ? ሁሉም ነገር ሲናወጥና ሲጠፋ፣ ጨለማው ይበልጥ እየጨለመ ሲሄድ፣ የሕዝቦች ጭንቀት እየከፋ ሲመጣ፣ ነገሥታት ገዦች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ብርሃን ይመለሳሉ። ለዚህ ዘመን ማክተሚያ እግዚአብሔር ላለው ዓላማ እንዲውል ሀብታቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን ያመጣሉ። ‹‹ለአሕዛብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት ወንጌል ለዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ከዚያም መጨረሻው ይመጣል›› (ማቴዎስ 24፡14)።

ይህ የመንግሥቱ ወንጌል፣ እንደ አዳኝ፣ ፈዋሽ፣ ነጻ አውጪ፣ አጥማቂ፣ የኢየሱስ ሙሉ ወንጌል፤ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይሰበካል። ከዚያም መጨረሻው ይመጣል።

እናዳምጥ፣ ንቁ እንሁን። እግዚአብሔር፣ ‹‹ብሩ የእኔ ነው፤ ወርቁም የእኔ ነው›› ይላል። ዲያብሎስ ገንዘብ ቢኖረውም፣ የሰረቀው ነው። ለመሆኑ የማን ነበር? የ እግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ሰበብ ያቀርባሉ። ያን ሰበብ ማቅረብ የነበረበት ዓለም እንጂ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆን አልነበረባቸውም። ለዚያ እኛ መብት አለን።

‹‹ብሩ የእኔ ነው ወርቁም የእኔ ነው።›› ‹‹የዚህ የአሁኑ ቤት ክብር፣ ከቀድሞው ቤት ክብር ይበልጣል።›› በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር፣ ‹‹ብርና ወርቁን ወደ ቤቱ አምጡ፤ ምን እንደማደርግበት ታያላችሁ›› ማለቱ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ለመፈጸም



የመንግስቱ ወንጌል መሰበክ ይኖርበታል። ምክንያቱም የሚመጣው መንግሥት፣ ከሕዝቦች፣ ከነገዶችና ከቋንቋዎች ሁሉ ነው (ራእይ 7፡9ይመ)። በሰው አስተያየት የተሸቃቀጠ ሳይሆን፣ ጳውሎስ እንደ ሰበከው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመግለጥ ወንጌል ለዓለም ሁሉ መሰበክ አለበት። ያኔ መጨረሻው ይመጣል። የእኔና የእናንተ ድርሻ ምንድነው? እንደ ካህናት በመንግሥቱ መግዛት ነው፤ በጸሎት መትጋትና ቤቱን በክብሩ ለመሙላት ራስን መለየት ነው። ድነት ካገኘሁ ሁለት ሳምንት በኋላ እግዚአብሔር ለእኔ ስላቀደው ነገር እግዚአብሔር ራእይ ሰጠኝ። ራእይ መሆኑን አላውቅም ነበር፤ ራእይ ምን እንደ ሆነም አላውቅም ነበር፤ ግን በጣም እውነት ነበር። በዚያ ጊዜ በሩቅ እንዳለ ተራራ ጫፍ ነበር። በእኔና በዚያ ተራራ ጫፍ መካከል በጣም ሰፊ ቦታ ነበር፤ ይሁን እንጂ ወደዚያ መሄድ ጀመርኩ።

ብዙ ጊዜ ማዕበል ነበር፤ ደመናዎች ይወርዱ ነበር፤ የተራራው ጫፍ ይጋረድ ነበር። አንዴ ሳይሆን ብዙ ጊዜ ከመንገዴ መውጣት ጀመርኩ። ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ፍጥረት የተነሣ ሁሌም ደመናዎቹ ይወገዱ ነበር፤ ፀሐይ ይወጣና እንደ ገና ያንን የተራራ ጫፍ ይገልጠው ነበር። በተሳሳተ አቅጣጫ ስሄድ አቅጣጫየን አስተካክል ነበር፤ እንደ ገና ወደ ተራራው ጫፍ መጓዜን እቀጥል ነበር። ይህ እኔን በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገድ እንድጸና እንጂ፣ ሌላ ምንም አይደለም። ይህ ባለ ራእይ መሆን ነው፣ መድረሻ ግብ መኖር ነው፤ እግዚአብሔር በሕይወቴ ሊፈጽመው የፈለገ አንድ ነገር መኖሩን ማወቁ ነው።

ለአያሌ አሥርት ዓመታት ክርስቲያን ነበርኩ፤ አሁን ባለሁበት ዕድሜ ደረጃ ላይ ሆኜ ይህ አስተሳሰቤን የገዛ ዋነኛ ዓላማ መሆኑን እናገራለሁ። ጳውሎስ፣ ‹‹ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን ሩጫዮንና የእግዚአብርን ጸጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎቴን እንድፈጽም›› ሲል ምን ማለቱ እንደ ነበር መረዳቴን አስባለሁ›› (የሐዋርያት ሥራ 20፡24)።

በአእምሮዬ ዓይን ያንን የተራራ ጫፍ አየዋለሁ፤ በጸሎት መንፈስ ሆኜ፣ ‹‹በእግዚአብሔር ጸጋ እዚያ እስክደርስ ድረስ አልቆምም›› እላለሁ።

እናንተስ አብራችሁን ትሆናላችሁ?

ለጌታ ክብር እንድታመጡ፤ በጸሎታችሁ መንግሥቱ እንዲመሠረት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ ጠላትን እንድታሸንፉ በክርስቶስ አካል ውስጥ ቦታችሁን እንድታውቁ፣ እናንተና የእናንተ የሆነው ሁሉ ንጉሣዊ ክህነትን ለመመሥረት እንዲጠቀምባችሁና የእግዚአብሔር መንግሥት ወደዚህ ምድር እንድትመጣ፣ የጸሎት መልስ የመቀበል ደስታን እንድታውቁ ጸሎቴ ነው።



# ስለ ደራሲው

ዴሪክ ፕሪንስ(1915-2003) ከእንግሊዛውያን ወላጆች ሕንድ አገር ተወለዱ በእንግሊዝ ባለው ካምብሪጅ በኢቶን ኮሌጅና ኪንግስ ኮሌጅ የግሪክና የላቲን ቋንቋዎች ምሁር ሆነው ተመረቁ ። ከተመረቁ በኋላ የጥንታዊና ዘመናዊ ፍልስፍና ፕሮፌሰር በመሆን በኪንግስ ኮሌጅ አስተምረዋል። ዴሬክ በካምብሪጅና በኢየሩሳሌም ባለው ሒብሩ ዩኒቨርስቲ ዕብራይስጥ፣ አረማይክና ዘመናዊ ቋንቋዎችን አጥንተዋል። ተማሪም፣ ፕሮፌሰርና እግዚአብሔርን በተመለከተ ምንም ማወቅ አይቻልም የሚል አመለካከት ያላቸው ነበሩ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በብሪታንያ ሕክምና ቡድን ውስጥ እያገለገሉ በነበረ ጊዜ ዴሬክ እንደ አንድ የፍልስፍና ሥራ መጽሐፍ ቅዱሥን ማጥናት ጀመሩ። ብርቱ በሆነ ሁኔታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመገናኘት ካመኑ ጥቂት ቀኖች በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ። ይህን ግንኙነት ምክንያት በማድረግ ሁለት መደምደሚያዎች ላይ ደረሱ፤ መጀመሪያ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው መሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው መጽሐፍ ቅዱስ እውነት፣ ጠቃሚ፣ ዘመን የማይሽረው መጽሐፍ ነው የሚል ነበር። እነዚህ ድምዳሜዎች ሳዘለቁታው የሕይወታቸውን አቅጣጫ ለወጡት፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንደ የእግዚአብሐር ቃል መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናትና ለማስተማር ራሳቸውን ሰጡ።

በ1945 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ከሠራዊቱ ከተሰናበቱ በኋላ ዴሬክ በዚያ የሕፃናት ማሳደጊያ መሥራች ከሆኑት ሊዲያ ክሪስተንሰንን አገቡ። እንደ ተጋቡ፣ ሊዲያ ያሳድጓቸው የነበሩ ስምንት ሴት ልጆች ማለትም ስድስት አይሁዳውያን፣ አንድ ፍልስጥኤማዊ አረብ፣ አንድ እንግሊዛዊ አባት ሆኑ። በ1948 የእስራኤል መንግሥት ሲመሠረት ቤተሰቡ እዚያው ነበር። በ1950 ዎቹ ዓመቶች ማለቂያ ላይ በኬንያ የአንድ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ዳይክተር በነበሩ ጊዜ ሌላ ልጅ በአባትነት ተቀብለዋል።

በ1963 ዓ.ም ባልና ሚስቱ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መጥተው በሲያትል ያለ አንድ ቤተክርስቲያን ፓስተር ሆኑ። በ1973 ዴሬክ ከ

Intercessors for America መሥራቾች አንዱ ሆኑ:: Shaping History through Prayer and Fasting የተሰኘው መጽሐፋቸው ለመንግሥታቸው ስመጸለይ ሳለባቸው ኃላፊነት በዓለም ዙሪያ ያሉ ክርስቲያኖችን አንቅቶአል:: የመጽሐፉ ሕቡዕ ትርጉም ሥራዎች በሶቪየት ኅብረት፣ በምሥራቅ ጀርመንና በቼኮዝላቫኪያ ለኮሚኒስት መንግሥታት ውድቀት መሣሪያ እንደ ነበር ብዙዎች ይገምታሉ::

ሊዲያ በ1975 ዓ.ም ሞቱ፤ በ1975 ዓ.ም ዴሬክ ሩት ቤከርን (ሦስት የማደጎ ልጆች ያሳድጉ የነበሩ እናት) አገቡ:: ሁለተኛዋ ሚስታቸውንም ያገኙዋቸው እንደ መጀመሪያዋ ሚስታቸው በኢየሩሳሌም ጌታን እያገለገሉ እያለ ነበር:: ሩት ከ1981 ጀምሮ ይኖሩ በነበረበት በኢየሩሳሌም ዲሴምበር 1998 ሞቱ::

በ2003 ዓ.ም እርሳቸው ራሳቸው በ88 ዓመታቸው እስከ ሞቱ ድረስ በመላው ዓለም በመጓዝ፣ የተገለጠ የእግዚአብሔር እውነትን በማካፈል፣ ስታመሙና ስተጎዱ በመጸለይ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር በዓለም ያሉ ሁኔታዎችን በተመለከተ ትንቢታዊ ዕይታን በማካፈል ዴሬክ እግዚአብሔር በጠራቸው አገልግሎት ጸንተው ኖረዋል:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ምሑርና መንፈሳዊ አባት ዓለም አቀፍ እውቅና ያተረፉት ዴሬክ ስድስቱን ክፍለ ዓለማትና 60 ዓመታት የሚሸፍን የማስተማር አገልግሎት መሥርተዋል:: 50 መጻሕፍት ደርሰዋል፤ 600 የኦዲዮ ትምህርቶች፣ 100 የቪዲዮ ትምህርቶች አሏቸው፤ ብዙዎችም ከ100 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል:: የትውልድ መርገምን፣ የእስራኤልና ትምህርተ አጋንንት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፋይዳን የመሳሰሉ ዐቢይ ሐሳቦችን አስመልክቶ አዲስ ፈር የቀደዱ መምህር ናቸው::

በ1979 የተጀመረው የዴሪክ ሬዲዮ ፕሮግራም ከአሥራ ሁለት ወደሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል፣ የሰዎችን ሕይወት መንካታቸውንም ቀጥለዋል:: ዋና ስጦታቸው የሆነው መጽሐፍ ቅዱሥንና ትምህርቶቹን በጣም ቀላል በሆነ መንገድ ማቅረባቸው በሚሊዮኖች



ሕይወት ውስጥ የእምነት መሠረት ለመጣል ረድተዋል:: ሁሉን አብያተ ክርስቲያናት የሚያቅፍና ከወገናዊነት የጸዳ አቀራረባቸው ለሁሉም ዘሮችና ሃይማኖቶች በዕኩልነት፣ ወቅታዊና ጠቃሚ በሆነ ሁኔታ ትምህርቶቻቸው እንዲታደስ አድርጓል፤ ትምህርታቸው ወደ ግማሹ የዓለም ክፍል መድረሱ ይታሰባል::

በ1902 ዓም፣ ‹‹ከ60 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር በእኔ በኩል የጀመረው ይህ የአገልግሎት ሥራ ጌታ እስኪመለስ ድረስ እንዲቀጥል ፍላጎቴ ነው፤ የጌታም ፍላጎት እንደዚህ እንደ ሆነ አምናለሁ›› ብለው ነበር:: በአውስትራሊያ፣ በካናዳ፣ በቻይና፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመን፣ በኔዘርላንድ፣ በኒውዚላንድ፣ በኖርዌይ፣ በራሺያ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በስዊዘርላንድ፣ በዩናይትድ ኪንግደምና በዩናይትድ ስቴትስ ያሉትን ዋና ዋና ሥራዎች ጨምሮ የዴሬክ ፕሪንስ አገልግሎት በዓለም ዙሪያ ባሉ ከሰላሳ በሚበልጡ የዴሪክ ፕሪንስ ቢሮዎች የዴሬክ ፕሪንስን ትምህርት ማሰራጨቱን፣ ሚሲዮናውያንን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን፣ ማኅበረ ምዕመናችን ማስልጠኑን ቀጥሏል:: እነዚህንና ሌሎች ዓለም አቀፍ ቦታዎችን በተመለከተ ወቅታዊ ምረጃዎችን ለማግኘት ----ይጎብኙ::

For more spiritual book join our official telegram channel
https://t.me/amharicsprituallbooks